t.me/bookshelf99

9

ሌላሠው የቀጠሮው ሰዓት ስለረፈደበት ልቡ ተሰቅሏል። ከሆስፒታል ወጥቶ ውስጥ ለውስጥ እየነዳ፣ ወደ ዋናው መንገድ ከመግባቱ በፊት ከተቃራኒ አቅጣጫ የመጡ መኪኖች ዘግተውበት ቆመ። የሁለቱ መኪኖች ሾፌሮች ወርደው በጋለ ስሜት ሲነጋገሩ እንደሚረፍድበት ስለገመተ ሲራክ ጋ ደውሎ ይቅርታ ጠይቀው።

የባለ መኪኖቹ ንግግር ወደ ስድብና ሙቅሙቅ ሲቀየር እሱም ከመኪናው ወረደ። አጠገባቸው ሲደርስ፣ ከፊትና ከኋላ መንገዱ ተጨናንቆ በሰው ተከበቡ። "ቀይ እና ምን ይጠበስ ነው የምትለው? እኔ ላይ ስለዘጋህ በሰዓት ደረስክ እንዴ? ... የሰው መንገድ ስለዘጋህ እኮ ያንተ አይከፈትልህም" አለ፣ ሰውነቱ ደልደል ያለ ሃይሉክስ ቶዮታ መኪና የያዘው ረጅም ሰውዬ።

"አቦ ዝም ብልህ ሰው ላይ አትደንፋ ... በትክክል መንዳት የማትችል ከሆነ ... አስተማሪ ቀጥረህ መማር ትችላለህ። ምን ... ሰሞኑን የገዛኸው መኪና ነው እንዴ? ራስህ ከሞን ገብተህ ጥልቅ ካልክ በኋላ ... ደግሞ ካንተ ብሶ ... የማነው ባካችሁ?" አለና ተጠጋው፣ ጠቆር ቀጠን ያለው ባለ አይሱዙው ሾፌር። የባለ አይሱዙው ረዳት ለጥል አቀብቁቦ ከሌላኛው ሾፌር አጠገብ ቀሚል።

"እሺ ... አሁን መንገዱን ትለቅልኛልህ ... ወይስ?" አለ፣ ረጅሙ ሰውዬ፣ እጆቹን ጨብጦ እየተጠጋው።

"ባለቅልህ ምን ታመጣለህ? ... ከፊለግህ ወደ ኋላ ወጥተህ ..." ብሎ ሳይጨርስ፣ የሃይላክሱ ባለመኪና በቦክስ ነረተው። ሁለቱ ተናንቀው ሲቆራቆሱ የአይሱዙው ረዳት ከየት መጣ ሳይባል፣ በያዘው የሌባ ገማ ሌላኛውን ሾፌር ጭንቅላቱ ላይ ሲዠልጠው ጭኸ ወደቀ። ሌላሠው ተንደርድሮ ረዳቱን ሲይዘው፣ ሌሎቹ የከበቧቸው ሰዎች ደግሞ ሁለቱን ለማለያየት ተረባረቡ። የተፈጠረውን ጣጣ ማብረድ ካቅም በላይ ሆነ። በዚህም ምክንያት ፖሊስ እስኪመጣ ድረስ ያዙኝ ልቀቁኝ ቀጠለ።

Brought to You by t.me/bookshelf99

ሌላሠው መኪናውን እንደ ምንም በጥግ በኩል አሳልፎ መንገዱን ቀጠለ። 'ሁለት በምክንያትና በመረዳዳት ሊነጋገሩ የሚችሉ ሰዎች፣ በጡጫና በርግጫ ለመግባባት መሞከራቸው ይገርማል። ስሜት፣ ማሰብን ሲገዛና ሲከልል ትልቅ ሰው ትንሽ ይሆናል። ሰሜቱ ያሸነፈው ሰውና ፍሬኑ ተበጥሶ መሪው የማይሰራ በፍጥነት የሚገሰግስ መኪና እንድ ናቸው' ብሎ አሰበ።

ከመኪናው በጥድፊያ ወርዶ ከሲራክ ጋር ለምሳ እተቃጠሩበት ቤት ገባ። ቀድሞት ደርሶ ኖሮ ቦታ ይዞ በተመስጦ ሲያነብ ደረሰ። ትከሻውን ነካ አደረገና እጁን ለሰላምታ እየዘረጋ፣ "ሄ-ይ፣ ወጣቱ ዶክተር ... በጣም ይቅርታ ... ከተማሪዎቹ ጋር አንላቀቅ ብለን ... ሳላስበው ጊዜው እንደ ሄደም ሳላውቅ አረፈድኩ። ታዲያስ ... ብዙ አስጠበቅሁህ እንዴ?" አለው።

"አይ፣ ኧረ አሁን ነው የመጣሁት። አንዳንዴ መንገዱም እኮ ያላሰብክበት ቦታ ይዘጋጋል። እንዴት ነው ... አማኑኤል ሰላም ነው?" አለ፣ ፈገግ ብሎ።

"አማኑኤልና ሰላም ... በሽበሽ ነው" አለና ኮቱን አውልቆ ወንበሩ መደገፊያ ላይ ሰቀለና ተቀመጠ። ቤቱ ብዙ ብርሃን የሚገባበትና መቀመጫዎቹም ዘርዘር ብለው የተሰናዱ ስለ ሆነ ቅልል ይላል። የበግ ጥብስና ሽሮአቸው ታዋቂ ነው።

ሲራክ ሁሌም መጽሐፍ ከእጁ አይለየውም። ሌላሠው ጥቁር አንበሳ ሊያስተምር በሄደበት ጊዜ ተዋውቀው በቀላሉ ነበር የተግባቡት። በሳምንት አንዴም ሁለቴም ለምሳ ወይ ለቡና መገናኘት ልማዳቸው ሆኗል።

"ምን እያነበብክ ነው?" አለ፣ ሌላሠው ከፊት ለፊቱ ዘግቶ ያስቀመጠውን መጽሐፍ ለማንሣት እጁን እየዘረጋ። መጽሐፉን ወደ እርሱ እየገፋለት፣

"የሲግመን ፍሩይድ ... ዘ ኢንተርፕሪቴሽን ኦፍ ድሪምስ (የህልም አተረጓጐም) ነው። ሰውዬው ነገሮችን የሚያይበት መንገድ ይገርማል። ችግሩ ... እዚህ አገር እንኳን የሚተረጐም ሕልም ይቅርና ገና የሚተኛበትም ደህና አልጋ አለመኖሩ ሆነ እንጂ" ሲል፣ ሁለቱም ሣቁ። ንግግሩን ቀጥሎ፣ "ሲርየስሊይ ግን እንዲያው እነ ፍሩይድና ዩንግ የፈጠሩት ሳይኮአናልይሲስ ምናምን የሚሉት ነገር እዚህ እኛ አገር ይሠራል ብለህ ታምናለህ? ማለቴ፣ ቲዎሪው አሪፍ ነው፣ ግን አንዳንዴ በልቶ ባልጠገበ ጎብረተሰብ ውስጥ እየኖርክ ... አለ አይደል ... ትንሽ ቅብጠት አይመስልብንም?" አለና ባቀላለፋቸው እጆቹ ማጅራቱን ደግፎ ወደ ኋላ ለጠጥ ብሎ ተቀመጠ።

"ባንድ በኩል ልክ ነህ ... ግን ደግሞ በመጀመሪያ ሁሉም ያገራችን ሰው እኮ በልቶ የማያድር ወይም ሕልም የለሽ አይደለም። ደግሞ ደሃስ ሕልም የለውም ያለው ማነው? እንዲያውም 'ደሃ በህልሙ ቅቤ ባይጠጣ ኖሮ' ሲባል አልሰማህም?" ሲል፣ ሁለቱም እንደገና ሳቁ። ሌላሠው ትንሽ አሰበና ንግግሩን ቀጠለ። "ግን በቁም ነገር ምናልባት እነ ፍሩይድ ወይም ዩንግ ከነበሩበት የዛሬ መቶ ዓመት አካባቢ ከነበረው

Brought to You by t.me/bookshelf99

አውሮጳ ይልቅ ዛሬ እኛ ያለንበት የኑሮ ደረጃ እኮ በብዙ መልኩ ቢሻል እንጂ አያንስም። ሳይኮአናሊሲስ ደግሞ እነርሱ በራሳቸው መንገድ በጊዜው የነበረውን የኅብረተሰባቸውን ስሜትና ሞንቀት ... አሳብና ጥልቅ የአእምሮ ጓዳ ለማየት የፈጠሩትና የሞከሩበት መንገድ ነው። ለምሳሌ፣ ፍሩይድ ሕልምና የምላስ ወለምታ ወደ ጥልቁና ስውሩ የአእምሮአችን ጓዳ የሚያደርሱ አውራ ጐዳናዎች ናቸው ብሎ ያምን ነበር። ይህ የእርሱ እይታ ነው ... ብዙ የማይስማሙ ሰዎችም አሉ።

"በሌላ በኩል ስታየው ደግሞ ምናልባትም የዓለምን አስተሳሰብ በከፍተኛ ደረጃ ከቀረጹ 'ፍልስፍናዎች' መካከል ማለት ትችላለህ የነፍሩይድ ሥራ ሊጠቀስ ይችላል። እስከ አሁንም ቢሆን ኪነጥበብ ብትል ፍልስፍና፣ ሳይኮሎጂ ብትል ሥነመለኮት እነርሱ ባቀረቡት ሥነልቦናዊ መላ ምቶች ብዙ ተቀርጸዋል። ከዛ በኋላ የመጡ ብዙ ሥነልቦናዊ መላ ምቶችና የተለያዩ የሰዎችን የስሜትና የነፍስ ሥቃይ ለማከም የተፈጠሩ ዘዴዎች ሁሉ ቢያንስ በከፊል ከዛው የተቀዱ ናቸው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ግን ደግሞ እንዳልኩህ እንደ ማንኛውም ቲዎሪ የራሱ ግድፈትና ጉድለት ይኖረዋል። ከዘመን ጋር የሚያረጁ ነገሮችም ያሉት ይመስለኛል" አለ። የሚታዘዘው ልጅ ስለ መጣ የሚበሉትን መርጠው ወሬያቸውን ቀጠሉ።

"እሱማ ልክ ነው ... ይገባኛል። ግን እዚህ አገር እንዴት ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል ሳስበው ተስፋ ስለሚያስቈርጠኝ ነው። ማለቴ የበሽተኛው ብዛት ፋታ አይሰጥህም። ክሊኒክ ከፍቼ ጥቂት ሰው ብቻ እያየሁ እንደ መጽሐፉ እኖራለሁ ካልክ ደግሞ ምን በልተህ ልትኖር ነው? ማለቴ ማን ይከፍልሃል? ጨክኖስ ነፍሴን መርምርልኝ... የልጅነት ውልግድግዴን አስተካክልኝ ብሎ ከፍሎ ለመታየት የሚመጣ ሰው እኛ ሀገር ይኖራል ብለህ ታምናለህ? የነፍሱን ጉዳይ ለማስመርመር ከሆነ አብዛኛው ሰው የነፍስ አባት አለው" አለ ሲራክ።

ጠረጴዛ ላይ ያለውን መጽሐፍ አንስቶ እያገላበጠ ወሬውን ቀጠለ። "አማኑኤልን ብትወስድ ለምሳሌ ... እዛ ቤት ያለው ችግር እንኳን ለሳይኮአናሊሲስ ለመድኃኒትም የሚበገር አይደለም። ዝም ብዬ ሳስበው እነዚህን መጽሐፎች እንደ ሥነጽሁፍ እያነበቡና እየተደሰቱ ከሰኞ እስከ ዓርብ ግን ብዙሃኑን ሕዝብ ባለው ነገር ማከሙ ነው የሚሻለው" ብሎ፣ በረጅሙ ተነፈሰና የሚሰጠውን መልስ ለመስማት ዝም አለ። ሲናገር እጁን የሚያወናጭፈው ሲራክ፣ ስሜት ውስጥ ገብቶ ሲያወራ ድምፁም ሳያስበው ይግላል።

"እንዴ እንደ እሱማ ባጭሩ ተስፋ መቁረጥ የለም ወጣቱ ዶክተር..." አለና መጽሐፉን ከሲራክ እጅ ተቀብሎ ማውጫውን በፍጥነት አየት አየት አደረገው። "ፍሩይድና የሱ ዘመን እኩዮቹ የሠሩትን ታላላቅ ሥራ የሠሩት ... ሁሉ ነገር ተመቻችቶላቸው አይመስለኝም። እንዲያውም በነርሱ ዘመን የመድኃኒትም ሆነ የሥነልቦና ዕውቀት የነበረበት ደረጃ ... ባጠቃላይ ሕክምና የነበረበት ሁኔታ አሁን እኛ ካለንበት በጣም ያነሰ ነበር። በርግጥ ከኛ ጎብረተሰብ አንጻር የዛን ዘመኑ አውሮጳ

Brought to You by t.me/bookshelf99

በብዙ የነቃና የሚያነብ ማኅበረሰብ ነበረ ሊባል ይቻላል። ምናልባትም ደግሞ እንደ ግለሰብ ስለ ኑሮና ስለ ገንዘብ ጉዳይ እንደኛ ብዙ ጭንቀት አልነበረባቸውም ይሆናል። ግን አንዱ ፈር ቀዳጅ የሆነ ሰው የሚጠበቅበት ነገር ... በአዲሱ መንገድ ላይ መጓዝ ብቻ ሳይሆን ... ራሱ የሚሄድበትን አዲስ መንገድም መንጥሮ ማዘጋጀት ነው።

"የህዝባችን ሥነልቦናና የውስጥ ሰብእና አወቃቀር ገና ያልተጠናና በግልጽ ያልተብራራ ጉዳይ ነው። በባህል፣ በእምነት፣ በአስተዳደጋችንና በኋላ ታሪካችን ላይ ተቀብረን፣ ድብቅ ሆነን እንኖራለን። ሁሉም ነገራችን መጥፎ ነው ማለቴ አይደለም። ግን ብዙ ነገሮች በስሜትና በአስተሳሰብ መዋቅራችን ላይ የጣሉት አሻራና የፈጠሩት ተጽእኖ ምን እንደሆነ እንኳ ገና በቅጡም አናውቀውም።

"የሚገርምህ እኮ እንኳን ለእኛና ለራሳቸው በዚህ ዘመን ላሉት ላውሮጳው ያኑና ላሜሪካኖቹም እነ ፍሩይድ ያሉት ነገር ሙሉ ለሙሉ አይሠራም። በሌላ በኩል ግን ለምሳሌ ስለ ሰው የሰብእና አወቃቀር፣ የውስጥ ግጭቶቻችንን ስለምናቻችልባቸው የማስታረቂያ ብልሃቶች (ዲፈንስ ሜካኒዝምስ) ... ስለ ንቁውና ስውሩ የአእምሮአችን ጓዳዎች (ኮንሺየስና አንኮንሺየስ ማይንድ) ... እንዲሁም የኋላ ግለ ታሪካችንና አስተዳደጋችን በዘንድሮ ኑሮአችን ላይ ሊያሳድር ስለሚችለው ተጽዕኖ ... የሰጡትን መላ ምቶች፣ ባብዛኛው ዘመንና ድንበር የማይከልላቸው ሁለገብ ሰዋዊ እውነቶች ናቸው።

"አሁን ባብዛኛው አውሮጳና አሜሪካም ብትሄድ ሳይኮአናሊሲስ ለሌሎች የማማከርና የቴራፒ ዘዴዎች ከማገዝ በዘለለ በዋናነት እጅግም አይሠሩበትም። ከጊዜ ጋራ አብሮ የሰፋም የሥነልቦና አወቃቀርና የነፍሱ ሕመም ትኩረት ይቀያየራል። ስለዚህ ያንዱ ዘመን ሥራ ለሌላ ዘመን ... ያንዱንም ባህል አተረጓጎም ለሌላው ባህል ... በቀጥታ እንጠቀምበት ብንል አይሠራም። እኛ አገርም በየሃይማኖቱና በባህሉ ውስጥ የተቀበሩ ብዙ ሥነልቦናዊ ሀብቶች ቢኖሩንም ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ተጠንተውና ተጽፈው ስላልተቀመጡ ብዙም አልጠቀሙንም" አለና፣ ለረጅም ጊዜ ሲያሸሞነሙን የቀየውን ጉርሻ ጎረሰ። የጀመረውን ሐሳብ ባይጨርስም ሲራክ የሚለውን ለመስማት ስለፈለገ ሌላ ጉርሻ ማሰናዳት ጀመረ።

"ይገባኛል እሱ ... ግን እስኪ እየው... ለምሳሌ፣ አሁን እኛ የአእምሮ ሐኪም ለመሆን የምንሰለጥንበት መንገድ ራሱ ለዚያ ዓይነት አስተሳሰብም ሆነ አኗኗር አያዘጋጅህም። አኔን ብትወስድ፣ ለምሳሌ፣ አሁን የጎንደር ዩኒቨርስቲ ነው የሚያስተምረኝ። ስለዚህ ልክ ሥልጠናዬን ስጨርስ ወይ ሄጄ እዛ አምስት ዓመት እሠራለሁ። አለበለዚያ ደግሞ ብዙ መቶ ሺህ ብር መክፈል አለብኝ። አሺ፣ እዛ ሄጄ ምን ማድረግ እችላለሁ?

"ከጠቢብ የተረፈ ወይም ለጻሎት የቀተ ውስብስብ እብየት በሮጌ መድኃኒት

Brought to You by t.me/bookshelf99

እንደዚህ የምታወራው እኩያ አስተሳሰብ ያለው ሰው አይኖርም ። ያው እንዳልኩህ ጥቂት ያረጁ መድኃኒቶችን እየሰጠህና ጊዜ ያለፈባቸውን መጻሕፍት እንደ ዳዊት እየደገምክ የሚያብደውን እያስተባበድክ ከመኖር ውጪ ። ለዚያውም አንተ ቀድመሃቸው ካላበድክ ማለት ነው ። አንዳንዴ የአእምሮ ሕክምናውን በቃ ለራሴ ሰውቀት ያህል ከተማርኩት ለምን ሌላ ነገር ሠርቼ አልኖርም ብዬ ሁሉ አስባለሁ ..." አለና ፣ ከፊቱ የተቀመጠውን ግማሽ ብርቱቀ አምቦ ውሃ ባንድ ትንፋሽ ጨለጠው ።

"ሲራክ ... ምንም ጥያቄ የለውም ፣ ነገሩ ከባድና አስቸጋሪ ነው ። በምንም መንገድ እኮ ቀላል ይሆናል አንልም ። ከባድ ስለሆነም ነው ሁሉም ሰው የማይሠራው ። ግን ደግሞ የማይቻለው ነገር ላይ ካተኰርክ ወይም ጉድለቱ ብቻ ጐልቶ ከታየህ ምንድነው ፋይዳው? ለምሳሌ ጎንደርን ብትወስድ ፣ ብዙ ሰዉ በኑሮው ችግረኛ ሊሆን ይችላል ። የሰዉ ሰብእናና የሥነልቦና ውስብስብነቱ ግን የፈለገ ሠለጠነ ከሚባለው ፈረንጅ ቢበልጥ እንጂ አይተናነስም ። አዲስ የሥነልቦና ቲዎሪና የአእምሮ ሕክምና ጐዳና መፍጠር ከፈለግህ ... እንደኛ አገር ሕዝብ በሥነልቦናውም ሆነ ባስተሳሰብ ደረጃው የበለጸገና የተወሳሰበ ፣ ያልተነካ ጥሬ የአእምሮ ሀብት ያለው ማኅበረሰብ የትም አታገኝም ። የተዘጋጀ ነገር ከጠበቅን ግን ምንም ሳንሠራ ልንሞት እንችላለን" አለ ሌላሠው ፣ ከባሻገር የሚያውቃቸው ሰዎችን ስላየ እጁን ለሰላምታ እያውለበለበ ።

"እሺ ቆይ ለምሳሌ አንተ እዚህ ለመኖር ብትችል ወይም ቢኖርብህ ... ምን ታደርጋለህ? ማለቴ አሁን ከምናወራው አንጻር?" አለ ሲራክ ፣ በያዘው ናፕኪን እጁን እየጠራረገ ።

"ቀላል አይደለም ። ሀም ... በመጀመሪያ የማደርገው ... ሀም... እኔ በምፈልገው ዓይነት የራሴን ክሊኒክ መክፈቴ የግድ ይመስለኛል ። ማዕከሉ በተቻለ መጠን ሌሎች ሳይካትሪስቶችን ፣ ሳይኮሎጂስቶችንና የማኅበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎችን ያካተተ እንዲሆን አደርጋለሁ ። የሥራ ትኩረቴንም በተለይ አገራዊ ፋይዳ ያላቸውና አሁን ውስጤ ያሉ ጥያቄዎችን የሚመልሱ ጥናቶችን ማድረግ ላይ ይሆናል ። የብዙ ሰዎችን ችግሮች በሚወክሉና የሕዝቡን ሥነልቦናዊ እንቀቅልሽ ለመረዳት ቁልፍ በሆኑ የተወሰኑ ኬዞች ላይ ብዙ ጊዜ ለማጥፋት አስባለሁ ።

"ከዛ በተጨማሪ ደግሞ ፣ መጻፍና ምናልባትም ሚድያ ውስጥ ገብቶ የሰዉን ስነልቦናዊ ንቃት መኮርኮርና ማሳደግ ይመስለኛል ዋና የትኩረት አቅጣጫዬ ። እኔ እንደማምነው ያበሻ ነፍስና ሥነልቦና ለረጅም ዘመናት ከምናስበው በላይ የቁሰለና መከራ የተሸከመ ነው ። ያለፈውን አርባና አምሳ ዓመት እንኳን ብታስበው ይዘገንንሃል ። ያ ሁሉ ያልታከመ ሕመም ያልተከፈለ የሥነልቦና ዕዳ ነው ማለት ይቻላል ። ነገሩ ያንድ ቀን ሥራ አይደለም በርግጥ ።

"ሌላ የማደርገው ደግሞ ከወጣት የሥነልቦና ባለሙያዎችና ተማሪዎች ጋር

Brought to You by t.me/bookshelf99

የቻልኩትን ያህል ጊዜ ማጥፋት ነው። ምክንያቱም አሁን የምናወራውን ነገር እኛ ብንጀምረውም የሚሠሩት እነሱ ናቸው ብዬ ከልቤ ስለማምን ነው። ግን ያው ገና ብዙ ነገር መልክ ስላልያዘልኝ ነገሩ ከምኞት ያለፈ ላይሆን ይችላል ...” አለና ከባሻገር ከሚሰማው ሙዚቃ ምት ጋራ ጭንቅላቱን እያነቃነቀ ሲራክን አጥልቆ ለማየት ሞከረ።

“ዶክተር ሌላ ... ያልከው ነገር ሁሉ አሪፍ ነበር፣ ችግሩ በጣም ትልቅ ኢንቨስትመንትና ሰፊ ጊዜ ይጠይቃል። ደግሞስ የት ጋ ጀምረህ የት ትጨርሰዋለህ? አብዛኛው ሰው እኮ ተንቀሳቃሽ ችግር ነው። ድብቅነታችን በጀ እንጂ እንደ እናንተ አገር ሰዎች ግልጽ ብንሆን ምን ሊፈጠር እንደሚችል አስበው ...” አለና ዝም አለ። ባጠገባቸው የሚያልፈውን አስተናጋጅ ጠርቶ የቀይ ጤፍ እንጀራ እንዲጨምርላቸው ጠየቀና በግራ እጁ ከሽኖ የያዛትን ጉርሻ እንደ ያዘ ንግግሩን በመቀጠል “እሺ ያሰብከው ሁሉ ተሳክቶና እዚህ መኖር ብትችል ... ትኩረት የምትሰጣቸው ዋነኛ ሐበሻዊ የሥነልቦናና የአእምሮ ችግሮች አሉ ወይስ ገና በሱ አቅጣጫ አልወሰንክም?”

ሲራክ በጉዳዩ ላይ ይዤንን ያህል ጠልቀ ሰምጧል ብሎ ያልገመተው ሌላሠው ውስጡ ደስታም አድናቆትም እየተሰማው፣ “በርግጥ ብዙ ነገር ጥያቄና የማወቅ ፍላጎት አጭሮብኛል። ለኔ ግን ጥቂት ነገሮች ሁሌም ዋና ናቸው። አንደኛ በጦርነትና በግጭት ብዙ እንደኖርን ሕዝቦች ይህ የፈጠረብን የሥነልቦና ጫናና የተቀበረ ሥቃይ ማጥናትና መረዳት ነው። ለምሳሌ፣ ባለፈው አርባና አምሳ ዓመት ብቻ የእርስ በርስ ጦርነቱ ... የቀይና ነጭ ሽብር እልቂቱና ያለፍንበት ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ሰቆቃ ... በሕፃናትና በሴቶች ላይ የተጫነው ጥቃትና ሥቃይ የፈጠረው ሥነልቦናዊና ሰብእናዊ ጫናን ማወቅ በራሱ የዕድሜ ልክ ሥራ የሚፈልግ ይመስለኛል። በተጨማሪም የድኽነትና የእጦት ተጽእኖው የሥጋ ብቻ ሳይሆን የነፍስ መቁሮቁዝና መጨራመት ሳይፈጥርብን የቀረ አይመስለኝም። ከወሲብና ከጾታ ግንኙነት አንጻር ታፍኖና ተሸፋፍኖ ስላለው አስተሳሰባችንና ስሜታችን ሳስብ ደግሞ ሌላ ያልተነካ ትልቅ ችግር ይታየኛል።

“በተጨማሪም በማኅበረሰባዊና ጋርዮሻዊ አስተሳሰባችን ውስጥ ተቀብሮና ተረስቶ ስለሚኖረው የእያንዳንዱ ሰው ግለሰባዊ ማንነት ብዙ ሥራ መሥራት ያለብን ይመስለኛል። እንደ አንድ ሰው የየሰዉ የማንነትና የሰብእና አረዳድ ጉዳይ። ደግሞም ... መሬቱ ውስጥ ካለው ሀብት ይልቅ በየሰዉ ውስጥ ተደብቀው ያሉ መልካም እሴቶች ይበለጣሉ ባይ ነኝ። ሰዉ ከችግሩ በላይና ከነችግሩ ደስተኛ ሆኖ መኖር የመቻሉ ምስጢር ... በእምነቱና በሃይማኖቱ ያገኘው ሥነልቦናዊ ጥንካሬ ... እንደቡና መጣጣት ያሉ በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ተሰባጥረው ስላሉ ደጋፊ ልምዶቹ ... ብዙ ነገር አለ ... ተቀፍሮም የሚያልቅ አይመስለኝም፣ ብዙ ሥራ ነው የሚታየኝ” አለና ትንሽ ተንጠራራ።

Brought to You by t.me/bookshelf99

"ዶክተር ሌላ ... እኔ ግን ይኼን ሁሉ ሳስበው ካቅሜ በላይ ይሆንብኛል። ለጊዜው የሬዝደንሲ ሥልጠናዬን መጨረስ ነው የሚታየኝ። ሌላው ከዛ በኋላ ይታያል ባይ ነኝ። ግን በጣም ታንክ ዩ ... ብዙ ነገሮችን ባላየሁባቸው አቅጣጫዎች ነው ያሳየኸኝ" አለ። ከማኪያቶው ውስጥ የጨመረውን ስኳር አማሰለና ማንኪያውን በሙዚቃዊ ምት ከስኒው ጠርዝ ጋ በቀስታ እያጋጨ፣ "በቃ፣ እናንተም መሄጃችሁ እየደረሰ ነው አይደል? ከዚህ በኋላ ምን ያህል ትቀያላችሁ?"

"እኔ እንኳ ትንሽ ብቀይም ደስ ይለኝ ነበር። ንጹሕ ግን ፈጽሞ አገሩን አትወደውም። ይሄንንም ያህል የቀየችው በስንት ልመና ለእኔ ብላ ነው። ደግሞ የልጆቹም ትምህርት ቤት ስለሚከፈት ከሦስት ሳምንት በኋላ የግድ መሄድ አለባቸው። እሷ ከፈቀደችልኝ እኔ አንድ ወር ምናምን ብጨምር ደስ ይለኛል። እዛ ያለው የሥራ ሁኔታ ከፈቀደልኝ ማለት ነው" አለ፣ ሐሳቡ ብትንትን ያለበት በሚመስል ድምፅ።

"ኡህ ... ከቤተሰብ ጋር ቀላል አይደለም። አንተ እንዲያውም በጣም ጎበዝ ነህ። ሳስበው እኔ ውጭ የምኖር ብሆን እዚህ ሀገር መጥቼ እዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ የምዳክርም አይመስለኝም። አላውቅም ... ግን አይመስለኝም። በነገራችን ላይ የምር ንጹሕ እሺ ብትልህ እዚህ መኖር ታስባለህ?" አለ፣ ፊቱን ሜምድድ አድርጎ።

"አድርጎልኝ ነው። ለኔ እዚህ መኖር ልገልጸው የማልችለው የሚሰጠኝ ደስታና ርካታ አለ። ምናልባትም አባቴ ከልጅነቴ ጀምሮ የፈጠረብኝ ተጽእኖ ሊሆን ይችላል። እዚህ ብኖር ምን ዓይነት የሕክምና ማዕከል ልከፍት እንደምችል ሁሉ ይታየኛል። የረጅም ጊዜ ሕልሜም ስለሆነ ሊሆን ይችላል። ደግሞ ግን እንዳልከው ይሄ ሁሉ ከቤተሰቤ በላይ ሊሆን አይችልም" አለ። ወደ ኋላ ደገፍ ብሎ ከሩቅ የሚመጣውን ሙዚቃ እያዳመጠ ጣራ ጣራውን እያየ፣ አንዴ ወደኋላ ደግሞ ወደፊት ርቆ እየሄደ በጊዜ ዥዋዥዌ ላይ ተመላለሰ። ሲራክም ከራሱ ሐሳብ ጋር እየታገለ ደጅ ደጁን እያየ በራሱ መንገድ ነጐደ።

"አንተ ግን እንዴት ነው ስለ ማግባት ምንም እቅድ ምናምን የለህም እንዴ?" አለ፣ ከገባበት የራሱ ሐሳብ ሲወጣ የሚያወራበትን ርእስ በመቀየር።

"ም...ን ...ባክህ ... ብታስብ ምን ፋይዳ አለው። ሴቱ ሁሉ እኮ የማይጨበጥ ጉም ሆነብን። ትንሽ ደህና ናቸው ያልካቸው፣ ጥቂት አብረሃቸው እንደ ቆየህ የሚፈልጉትንም የሚያውቁ አይመስሉም። አለ አይደል ... በቃ ልክ እንደገዙህ ዕቃ እንደገና ጠፍጥፈው ሊሠሩህ ይፈልጋሉ። እኔ እንኛ ... ግራ ይገባኛል ...አለ አይደል ... ደግሞ ገና ሠላሳም አልደፈንኩም እኮ... ለምኑ ነው ጭንቀቱ..." ብሎ፣ እጆቹን እርስ በርሳቸው አሻሸ።

የሚጠራ ስልኩን አየት አድርጎ ኪሱ ውስጥ መልሶ ከተተውና ንግግሩን በመቀጠል፣ "ሳስበው ሳስበው ግን አግብቶ መታሰርና የማልወጣበት ወጥመድ ውስጥ

Brought to You by t.me/bookshelf99

መግባት አልፈልግም መሰለኝ። አግብተው የተደሰቱ ብዙም ሰዎች አላውቅም ... ከራሴ ወንድም ጀምሮ ... ስለዚህ ማግባቱ ያንንም ያህል አያጓጓኝም። ብረር ... ክነፍ ... ሞክር ... ያዝ ... ልቀቅ ... ነው የሚለኝ ታስሮ የተለቀቀው ልቤ" አለ፣ ከመቀመጫው እየተቁነጠነጠ።

ሌላሠው ጭንቅላቱን እየወዘወዘ በአንክሮ ሲያዳምጠው ቆየና፣ "ያው እንደ ሁሉም ጥሩ ነገሮች ማግባትም የራሱ ችግሮች ሊኖሩት ይችላል። ሁላችንም የምናልፍበት ግራ መጋባትና መፍራት አለ። ግን ዋናው ማወቅ ያለብህ ... ሁሉንም ሴቶች ሳይሆን አንተ የምታገባው አንዲት ሴት ብቻ ነው። ያገሩን ሴቶች ሁሉ ችግር የራስህ ማድረጉ ፍራቻህን ያበዛል እንጂ ብዙም ጥቅም የለውም። አንተ እንዳልካቸው ዓይነት ብዙ ሴቶች ሊኖሩ ይችላሉ ... እንዳልኩህ ግን ሁሉም ያንተ ሚስቶች አይደሉም። ወጥመድ ላልከው ... ዩ ኖው ... እኔም እንዳንተ ነበር የማስበው። መጨፈር ... መደሰት ... ደስ ካለችኝ ልጅ ጋር ሁሉ መክነፍ ...መብረር ነበር ሕይወት የሚመስለኝ።

"ንጹሕ ባላሰብኩበት ጊዜ ወደ ሕይወቴ ስትመጣ ግን ... በሷ መታሰርን ነጻነት ሆኖ አገኘሁት። የእኔ የተሻለ ማንነት በርሷ ሰብዕና ውስጥ አብቦ ታየኝ። የመስጠትን ትርጉምና ለሌላ ሰው በመኖር ውስጥ ያለውን ደስታ ከእሷ ተማርኩ። በመክነፍና በመቀበል ካለው ደስታ ይልቅ በመስከንና በመስጠት የሚገኘው እርካታ በጣም እንደሚበልጥ ያወቅሁት ከሷ ጋር ስሆን ነው። ለኔም ያኔ እሷን ሳላገኝ ይህንን ሁሉ ብትነግረኝ ስቂብህ ነበር የምሄደው። ያው ይገባሃል፣ ማግባት ምንም ችግር የለውም እያልኩህ እንዳልሆነ። ግን ደግሞ ደስታው ይበልጣል ለማለት ነው። በዛ ላይ ልጅ ሲመጣ ደግሞ ለራስህ ከመኖር ባርነት ነጻ ያወጡሃል ... አለ አይደል ... ቀምሰህ ካላየኸው ምንም ቃል አይገልጸውም።"

"ዶክተር ሌላ ... ምናልባት አንተ ዕድለኛ ሆነህ ነው፤ ንጹህን የመሰለች ሴት ያገኘኸው። እስኪ እኛም የሚጥልልን እንጠብቃለና እንግዲህ" አለ። ዝም ብሎ የያዛትን ስንጥር እንጨት እየሰባበረና እየሰነጣጠቀ የማኪያቶው ስኒ ውስጥ እየወረወረ ሲጫወት ጥቂት ቆየና፣ "እኔ የምልህ የሚስጥር እናት እንዴት ናቸው?" ብሎ የጨዋታቸውን አቅጣጫ ቀየረው።

በዛችው ሰዓት ሌላሠውም ስለ ምስጢር ሲያስብ ስለ ነበር ደንገጥና ግርም ብሎት፣ "ደህና ናቸው ... አይ ቲንክ ... ብዙ ለውጥ አላቸው። ያው ነገሩ ጊዜ መውሰዱ አይቀርም" አለ በደፈናው ሲራክ ስለ ችግራቸው ምን ያህል እንደሚያውቅና ከምስጢርም ጋር ያላቸውን ቀረቤታና ጓደኝነት የቱን ያህል እንደሆነ እርግጠኛ ስላልሆነ።

"እሷ ደግሞ ትገርመኛለች፣ የሆነች በጣም ውስብስብ ያለች ልጅ ትመስላለች" አለ ሲራክ፣ ፊቱን በግዴለሽነት እንዳጨማደደው በማስመሰል።

Brought to You by t.me/bookshelf99

"ለምን እንደዛ አልክ? ያን ያህል ታውቃታለህ?" አለ፣ ሌላው ከወገቡ ስበር በማለት ወደ ሲራክ ቀረብ ብሎ። ለሁለት ወር አቁማ የነበረውን የተግባር ልምምድ ከአንድ ሳምንት ወዲህ ከሌላው ሥር በመሆን እንደገና መጀመሯን ሲራክም ያውቃል። ከሞቂት ቀን በፊት በወሬ በወሬ ተነሥቶ እሷም ስለ ሲራክ ያለችው ትዝ አለው።

"እም ... ብዙም አላውቃትም፤ ግን የተግባር ልምምድ ለማድረግ ከሞቂት ወራት በፊት ጳውሎስ ትመጣ ነበር። አንድ ሦስት ሳምንት ከኔ ሥር ነበር የምትሠራው። በርግጥ በጣም ጐበዝ ልጅ ናት ... ግን በቃ አንዳንዴ ሕመምተኛዬ ብትሆን ብዬ አስብና ምን ያህል ከባድ የእጅ ሥራ እንደምትሆን ይታየኛል። ብዙ ያልተፈቱና የተቀበሩ ሥነልቦናዊ ጓዞች ያላት ይመስለኛል። ብቻ ዝም ብዬ ሳያት ከወንዶችም ጋር ብዙ ችግር ያለባት ትመስላለች። ያየኔ አስተያየት ሊሆን ይችላል" አለ። ሳያስበው ያወራው ነገር በሌላው የምርመራ ወንበር ላይ ያስቀመጠው መስሎ ተሰማው። ጣራ ጣራውን እያየ የኮርኒሱን አራት ማእዘኖች መቀኑጠሩ ላይ አተኮረ።

"እንግዲህ እኔ ለጊዜው ያን ያህል ብዙም ያወቅኳት አይመስለኝም። ከናታ ጋር ግን ጥሩ ግንኙነት ያላቸው ይመስላሉ" ብሎ፣ በማጤን ዓይን ትኮር ብሎ ሲያየው ነገሩ ይበልጥ ያልተመቸው ሲራክ፣ "እስኪ መታጠቢያ ቤት ደርሼ ልምጣ" ብሎ፣ ድንገት ብድግ አለ።

ሌላው ደግሞ ለምን ስለ ጋብቻ ካወሩት ወሬ ጋር አያይዞ ሲራክ ያን ሁሉ ስለ ምስጢር እንዳለ ማሰላሰል ጀመረ። በተለይ 'በሽተኛዬ ብትሆን' የሚለው ሐሳብ ያዘለው ትርጉም ምን ሊሆን እንደሚችል የተለያዩ አማራጮችን ለመገመት ሞከረ። ሐሳቡን ከፍሎና ለመውጣት ተዘጋጅቶ ስለነበር ሲራክ ከመታጠቢያ ቤት እንደተመለሰ ወዲያው ተከታትለው ወጡ።

Brought to You by t.me/bookshelf99

10

ሌላሠው ከምሳ ተመልሶ አማኑኤል ሆስፒታል ሲደርስ ስምንት ከሩብ አልፎ ነበር። ከመኪናው ወጥቶ ወደ ሴቶች መኝታ ክፍል እየተጣደፈ ሄደ። ከነርሶች ጣቢያ ሲደርስ የዝናሽ አባት ገና እንዳልደረሱ ኃላፊ ነርሷ ነገረችው። ከእርሷ ጋር ሴቶች ሕመምተኞች በሚተኙበት ሰፊ አዳራሽ ውስጥ ወዲያ ወዲህ እያሉና አንዳንድ ሕመምተኞችን እያወሩ ጥቂት ቀዩ። ክፍሉ እንደ ጠዋቱ ብዙም ግርግር አይታይበትም። አብዛኞቹ ሕመምተኞች በያልጋቸው ላይ ተኝተዋል፤ ሌሎቹ ደግሞ ሰብሰብ ብለው ያወካካሉ።

ስምንት ተኩል ሲሆን አለመድረሳቸው ትንሽ ስላሳሰበው፣ "ሲስተርዬ ምናልባት ቀጠሮውን ረስተውት እንዳይሆን ..." አለ፣ ምንም እንኳን ግማሽ ሰዓት ማርፈድን ሁሉም የለመደውና የተቀበለው፣ ሲራክ እንደሚለው 'ያገሩ ደምብና ያበሻ መብት' መሆኑን እየጠላ የተቀበለው የቀጠሮ እውነታ ቢሆንም።

"ምን እኮ ... ሰዉም ሰዓት አያከብር። ደግሞ ማን ያውቃል በዚህ በፀሐይ ይሄኔ ከዛ ድረስ በእግራቸው ይሆናል የሚመጡት። እስኪ ለማንኛውም በር ላይ ዘበኞቹ አላስገባ ብለዋቸው እንዳይሆን። እዚህ ቤት ስንት ሜኮና አለ መሰለህ። ቀይ እስኪ እኔ ራሴ ልሂድና ስለ ማውቃቸው በር ላይ ቼክ ላድርግ ..." ብላ፣ ፊቷ የበታተነችውን መረቀት ሰብሰብ አድርጋ ጣደፍ ጣደፍ እያለች ወጣች። እሱ ደግሞ ወደ ቢሮ ገብቶ ቀን ያልመለሳቸውን ስልኮች መደዋወል ጀመረ።

ብዙም ሳይቆይ ኃላፊ ነርሷ አንኳኳታ ገባችና "አይገርምህም ዶክተርዬ፣ ልክ እንዳልኩት ሰውዬው በጊዜ ደርሰው ነበር። በር ላይ ጥበቃዎቹ አላስገባ ብለዋቸው ነው። እንዲያው አሁንስ ይሄ አገር ምን ይሻለን ይሆን? ውይ እኔ አይገባኝም፣ ደሃ ለምን በደሃ እንደሚጨክን።"

"የሕመምተኛ መጠየቂያ ሰአት ስላልሆነ ነው የከለከሉዋቸው?" አለ፣ ነገሩን ሙሉ ለሙሉ ስላልተረዳ።

Brought to You by t.me/bookshelf99

"የምን የበሽተኛ መጠየቂያ ሰዓት ዶክተር? ሰውዬው ዶክተሮቹ ቀጥረውኝ ስለ ልጄ ጉዳይ ሊያናግሩኝ ነው ቢሏቸውም ከቁብም አልቆጠሯቸውም። ያው የኔ ቢጤ የሥጋ ደዌ ሕመምተኛ ስለሆኑ ነዋ። ድኸነት ወንጀል የሆነበት ሀገር ... እንዲያው ተወኝ ባክህ። ለማንኛውም እዛኛው ቢሮ አስገብቻቸው እየጠበቁህ ነው። ዝናሽን አብረህ ነው የምታያት ወይስ ለብቻቸው ልታናግራቸው ነው ያሰብከው?" አለች፣ ነገሩ ግፍግፍ እንዳደረጋት በሚያሳውቅ ፊትና ድምፅ። የፀሐይዋ ግለት ሜንቅላት ይበጠብጣል።

"አይ መጀመሪያ እስኪ እሳቸውን ለብቻ እናናግራቸው። ከዚያ በኋላ እሷንም እንጠራታለን" አለና ተከታትለው ወደ ቢሮው ሄዱ።

በከፊል የተዘጋውን በር ከፍተው ሲገቡ የዝናሽ አባት በትራቸውን ደገፍ ብለው፣ ቁዝም እንዳሉ ከአንዱ ወንበር ጫፍ ላይ ተቀምጠዋል። እነርሱ ሲገቡ ደንገጥ ብለው የግዳቸውን ከመቀመጫው ብድግ እንደማለት አሉና፣ "ኖር ...ኖር" አሉ ድክም ባለው ድምፅ።

"ኧረ አይገባም አባት ... እንደምን አሉ?" ብሎ፣ ለመጨበጥ እጁን ሲዘረጋላቸው እንደ መሳቀቅ ብለው እጃቸውን ከፍ አደረጉ። ከሁለት ጣቶቻቸው በቀር በሥጋ ደዌ ሕመሙ የተነሣ ሌሎቹ ጣቶቻቸው ከግማሽ በላይ የሉም።

ከጨበጣቸው በኋላ ተቀመጠና፣ "በጣም ይቅርታ አቶ በድሉ ... በር ላይ ጥበቃዎቹ አላስገባ ብለው እንዳንገላቱዎ ሲስተር ነገረችኝ። ደግሞ በዚህ በፀሐይ እዚህ ድረስ ስለመጡ በጣም ነው የማመሰግነው" አለ፣ ቀስ እያለ ከላይ እስከታች እያጤናቸው።

"አዬ ምናለ ... እነሱም ሥራቸው አይዶል። መረኸት ካላመጣህ ብለው ነው አላስገባ ያሉኝ። እኔ ደግሞ ምንም መረኸት የለኝ ብላቸው ሊያምኑኝም አልቻሉም። ሰዉ እኮ ዘንድሮ ተጨካክኗል" አሉ፣ ስማቸውን እንዴት እንዳወቀ ገርሟቸው። ምን እንደሚሉ ሜንቅ ብሏቸው መሬት መሬት እያዩ ብትራቸውን እንደተደገፉ ጸጥ አሉ።

ዕድሜያቸው ከስልሳ ብዙ ባይዘልም ችግሩ ተደራርቦ ግርጅፍጅፍ ብለዋል። በሕመሙ የተነሣ ነርቮቻቸው ከጥቅም ውጪ ስለሆኑ፣ በጊዜ ብዛት በደረሰባቸው ትንንሽ ቁስለቶችና አደጋዎች አብዛኞቹ የእጅና የእግር ጣቶቻቸው ተቀራርጠው አልቀዋል። ያደረጉት ጫማ እግራቸውን ከተጨማሪ ጉዳት እንዲጠብቅና የማይሠሩ ጡንቻዎቻቸውን እንዲደግፍ ተብሎ በተለይ የተሠራ ነው። የጫማው ለየት ያለ ቅርጽ ደግሞ ሕመሙ በሰውነታቸው ላይ የፈጠረውን ጉዳት አጉልቶት ይበልጥ ገስቋላ አስመስሏቸዋል።

አድጎ ያልተቆረጠው ሸበቶ ሪዛቸው ... ፀሐይና ቊር የተፈራረቀበት ፊታቸው ላይ የተጋደሙት ብዙ መስመሮች፣ የሰሞን ድካማቸውን ብቻ ሳይሆን

Brought to You by t.me/bookshelf99

የዓመታት መከራቸውን ያስነብባሉ ። በሌላ በኩል ደግሞ ስልክክ ያለ ፊታቸው፣ ዘለግ ያለ ቁመታቸውና ሰፋ ያለ ትከሻቸው ተዳምረው ጽናትንና ትእግሥትን የተላበሰ ጥስቍልና ያልሰበረውን የውስጥ ማንነታቸውን ጥንካሬ ያሣያሉ ።

"እኔ ዶክተር ሌላሠው እባላለሁ ። የዝናሽ ሐኪም ነኝ ። ሲስተርን ያው አግኝተዋታል ብዬ ነው ። የርስዎ ስም አቶ በድሉ ነው አይደል?" ሲል ከመቀመጫቸው ብድግ እንደማለት ብለው "ልክ ነው ዶክተር ... ልክ ነው ፣ በድሉ ጫኔ ነው ስሚ" አሉና ወደ ኃላፊ ነርሷ ሁለት እጆቻቸውን ዘርግተው ፣ "አይ እሳቸውማ እመብርሃን የባረከቻቸው ብሩክ መላክተኛ ናቸው ። እሳቸው ባይመጡልኝ ኖሮማ እዛ ጠሐዩ ቲከካኝ መዋሌም አልነበር" አሉ ። ሰውነታቸው ትንሽ ዘና ሲል ፣ ተስተካክለው ተቀመጡ ። በትራቸውን በእግራቸው መሃል ሸጉጠው ፣ በሁለት እጃቸው ደገፍ አሉና ጉንጫቸውን አሳረፉበት ።

"እንግዲህ እርስዎን ለማግኘት የፈለግነው አንዳንድ ነገሮችን ስለ ዝናሽ ለማወቅና ከዚህም በኋላ ስላለው ሕክምናዋ ለማቀድ ነው ። እዚህ ከመምጣታቸው በፊት እርስዎ ለመጨረሻ ጊዜ ያዩዋት መቼ ነበር?"

"ቀየ ልጄ ... ዓመት ተሁለት ወሯ አልሆነም ብለው ነው ድንገት ብን ብላ ተጠፋች ። ፈልገን አስፈልገን ትናጣት በቃ እርማችንን ለማውጣት ምንም አልቀረን ነበር ። መቼም እሷ ወላዲት አምላክ አያልቅባት ... ቸሯ እናቴ..." አሉ ።

"ሰሞኑን መጥተው አይተዋት ነበር እንዴ?" አላቸው ፣ ወደ ሌሎቹ ጥያቄዎች ከመግባቱ በፊት ።

" መች ነበር ልጄ ... በእደም ለታ ... ሦስት አራት ቀን ቢሆነው ነው መሰል ። ይመስገነው ታምሩ አያልቅ እሱ ፣ ብዙ ለውጥ አላት ። የገባች ሰሞን ተነበረችው፣ ተመጀመሪያው ረገብ ሰከን ብላ ነበር ። ስለ ልጆቿም ሁሉ ጠየቀችኝ ። እሷ እኮ መድኃኒቷን ትትወስድና ይሄን ጫት ማመንዠህና መጠጡን ትትተው እንዴት ዓይነት ልጅ መሰልችዎ ። ግን በቃ ሻል ቲላት የሆነ እሚጠራት ጋኔን አለ መሰል ብን አድርጎ ያጠፋታል" አሉ ፣ አንዴ ሌላሠውን ፣ አንዴ ነርሷን እያዩ ።

"ልጆቿ ከእርስዎ ጋር ነው የሚኖሩት? ስንት ልጆች አሏት?" አለ ፣ ስለ ልጆቿ መጠየቁ የመሻል ምልክት መሆኑን በማሰብ ።

"ሁለት ናቸው ። አንዱ መጀመሪያ የዛሬ ስምንት ዓመት እመሙ ቲጀምራት ተአረብ አገር ቅሪት ሁናው የመጣችው ነው ። እሱ ያረብ ክልስ ቁርጥ አረቦቹን ነው እሚመስል ። ሁለተኛዋ ደግሞ አራት ዓመት ሊሆናት ነው መሰል እንዲሁ ብን ብላ ጠፍታ ከርማ ተመንገድ እርግዛ መጥታ ነው የወለደቻት ። ልጆቹም አበሳቸው በዛ እኮ ... ያለ እናት ያላባት ። እናቷ ታትሞት በፊት እሷ ነበረች ስንቱን ጉድ የተሸከመች ። ይኸው ዝናሽም ጐዳና ወጥታ የቀረች እሷ ተሞተች ወዲያ ነው ። እናቲቱ ነበረች የቤተሰቡ ማገር ምሰሶ ።

Brought to You by t.me/bookshelf99

"አሁንማ ማንም ሃይ ባይ ቢጠፋ ጊዜ ቤቱም ሊበተን አፋፍ ላይ ነው ያለ። እኔም ይኸው በልመና ቀኑን ሁሉ ትዋትር ይመሻል። ልጆቹንም አንድ የሚሲዮን ርዳታ ድርጅት እየረዳልኝ ነው ተማሪ ቤትም መሄድ የቻሉት።" እንደ እሳት የሚፋጅ ብሶታቸውን በረጅሙ እየተነፈሱ ዘከዘኩት። ሳያስቡት፣ ትኩስ እንባቸው በጉንጫቸው ላይ ክብልል ሲል ድምፃቸውም ተሳሰረና በዝምታ ተዋጡ።

ሌላሠው የሚለው አጥቶ በሐዘን ሲያያቸው ከጐናቸው የተቀመጠችው ታላፊ ነርስ፣ "አይዝዎ አባባ ... መቻል ነው እንግዲህ ምን ይደረጋል፣ እስኪ እኛም የቻልነውን እናደርጋለን። ሌሎች ልጆች የሉዎትም?" አለች።

ያነቃቸውን ሳግ ለመዋጥ ትንሽ ዝም ብለው ቀዩ። "የዝናሽ ታናሽ አለች። እሷም ሦስት እምቦቀቅላዎች አሏት። አረቄና ጠላ ቸርችራ ነው እምትተዳደር። ባሏም እማይረባ ሰካራም ቢጤ ነበር። እሷን ጥሎ ታንዲት ኮማሪት ቤት ጠቅልሎ ገብቷል አሉ። ሌላ አንድ ወንድ ልጅም ነበረኝ። እሱም ያኔ በጦርነቱ ጊዜ ወታደርነት ገብቶ ይሙትም ይኑርም አይታወቅ። መቼም በሕይወት ቢኖር እስታሁን አይጨክንም ብዬ እርሜን አውጥቻለሁ። እናቱንም የገደላት አንድም የሱ ሐዘን ነው። እንዲሁ እንዳለቀሰች፣ ደጅ ደጁን እንዳየች ወደ መቃብሯ ወረደች" ብለው፣ በጃኬታቸው ጫፍ እንባቸውን ጠራረጉ።

"እርስዎ እዚህ አዲሳባ ምን ያህል ኖሩ?" አለ፣ ሌላሠው የተፈጠረውን ጠንካራ ስሜት ለማርገብ በማሰብ የጥያቄውን መስመር እያዞረና ግለቱን እየቀነሰ።

"አዬ ቀየሁ ... አሁንማ አርባ ዓመት ሊሆነኝ ነው። ተገዥም ነበር የመጣሁ። መጀመሪያ ይሄን ቁምጥና እታከማለሁ ብዬ ነበር የመጣሁ። ኋላ ተክምናው በኋላ አገሬ ልመለስ ነበር። ወዲያው ለውጡ ቲመጣ አገር ሁሉ ተመሳቀለ። ብዙም ታይቀይ በሽታውም እንደገና አገረሸብኝና እዚሁ ትታከም ቀየሁ። ያኔ ሰውም እንዲህ አልበዛ መንደሩም ሁሉ ጫካ ነበር። እዚያው ዘነበወርቅ አካባቢ ተሰው ተጠግቼ ያገኘሁትን እየሠራሁ መኖር ጀመርሁ። ተሥስት ዓመት በኋላ እንደኔው ልትታከም መጥታ ባጋጣሚ ተዋወቅንና ተልጆቼ እናት ጋር እህል ውሃ አጣመረን። ይኸው መከራህ አይለቅ ብሎኝ እስታሁን እዚሁ እንከላወሳለሁ ... ለጉድ የፈጠረኝ ..." አሉ፣ ከሕመሙ ተርፎ የቀረ እጃቸውን አንዴ ወደ እነርሱ አንዴ ወደ እግዜሩ በአቤቱታ አይነት ከፍ ዝቅ እያደረጉ።

"ዝናሽ የመጀመሪያ ልጅዎ ናት?" አለች ነርሷ፣ እርሷም ስሜት ካዘሉ ጥያቄዎች ለመሸሽ ይመስል።

"አይ ወንዱ ነበር የመጀመሪያስ ... እሷ ተከታይ ናት።"

"እንዲያው ዝናሽ ወደ አረብ አገር ከመሄዷ በፊት ምንም እንዲህ ያለ ነገር ላሟትም አያውቅ? ሌላስ በዘመድ አዝማድ በቤተሰብ እንደሷ ያለ የአእምሮ ሕመም

Brought to You by t.me/bookshelf99

የሚያመው ሰው አለ?" ዓይኑን ከሳቸው ላይ ሳይነቅል የጥያቄውን መልስ መጠበቅ ጀመረ ።

"ኧረ ምንም ... እኔ እስተማው ቅ እብደት በኔም በናቷም ወገን እንዳለ አልሰማሁም ። እንግዲህ አገር ቤት ያለውን ማን ያውኣል ። ልጅቱ እንደኔት ያለች ጐበዝ ተማሪ ነበረች መሰለህ ። ሁሌ አንደኛ ነበር እምትወጣ ። ደግሞ ሁሌ ንቁ፣ ዓይነግቡ ቀንጆ ተጫዋች ነበረች ። ወደ ዓሥራአንድ ክፍል ትትደርስ ግን በቃ ጐረምሳው ሁሉ አላስወጣ አላስገባ አሳት ። በኋላ ታቅማ በላይ ቲሆን መሰለኝ ተማይሆኑ ልጆች ጋር ገጠመች ። ትምርቷንም ችላ ብላ ተሰፈር ኮልኮሌ ጋር ሆነ ውሎዋ ። ኋላ ያ ምንድነው እሱ ቴ ... ማትሪካ ነው? ያሰራሁለተኛ ክፍሉ ፈተና ... እሱን ስትወድቅ ጊዜማ በቃ ... ተያ በኋላ ለይቶላት እንዳይን ጠፋች ።

"ኋላ ፈጣሪ የኛንም ልመና የሰማን መሰለን ። በዚህም በዛም ብላ አረብ አገር ሄደችና እኛም ትንሽ እፎይ አልን ። ምን ያደርጋል ገና ትንፋሻችንን ሳንይዝ፣ ያልታደለች ... ዓመትም ታይሞላት አቅሷን ስታ ያን የመጀመሪያ ልጇን ቅሪት ሁና መጣች ። ተያ ወዲህ ይሄው ሰውም ሆና ሰው አልሆነች" አሉ፣ ወደ ታች የተዝረከረከ አሮጌ ጋቢያቸውን አጥፈው ከትከሻቸው ላይ እየደረቡ ። ሌሎች ጥያቄዎችን ከጠየቁዋቸው በኋላ ዝናሽ ተጠርታ ከአባቷ አጠገብ ተቀመጠች ።

ወደርሷ ዞር ብለው፣ ቀስ ባለ ድምፅ፣ "እንዴት ዋልሽ የኔ አበባ?" አሉና እጇን ሳብ አድርገው ሲስሟት፣

"ደህና ነኝ አባዬ" ብላ፣ እንዳቀረቀረች በጨረፍታ አየ ቻቸው ።

"አቡሻና ሚጢ ናቸው የላኩልሽ ..." ብለው፣ ከኪሳቸው አንድ ወረቀት አወጥተው እንደተጣጠፈ ሰዓት ። ፈጠን ብላ ተቀበለችና ከፍታ ለረጅም ጊዜ ፍዝዝ ብላ ስታይ ቀየችና፣ ድንገት እንባዋ ወረቀቱ ላይ ጠብ ጠብ አለ ። በዝምታ ሲያዩዋት የነበሩት ሌላሠውና ኃላፊ ነርሷም ሳያስቡት አይኖ ቻቸው ረጠቡ ።

"ምነው አበባዬ ... ምነው?" አሉ፣ አባቷ በተለያየ ቀለም የተሳሉ አበባዎችና ቀይ የልብ ቅርጽ የተሳለበት ወረቀት አይተው በትልልቅ ጽሑፍ የተጻፈውን የልጆቿን ደብዳቤ ማንበብ ስላልቻሉ ።

አንጀት በሚበላ በተሰባበረ ድምፅ፣ "ልጆቼ ... ልጆቼ ..." አለችና አውም ዝም እንዳለች እንባዋ መፍሰሱ ቀጠለ ።

ሌላሠው ዓይኑን ጨመቅ አድርገ ፊቱን ጠረግ ጠረግ አድርጎ፣ "ማየት ይቻላል?" አለ፣ ዝናሽ ወስጥ እያለፈ ያለውን ከባድ ስሜት ምን ማድረግ እንዳለበት ግራ ገብቶት ። ዝም ብላ እጇን ይርግታ ወረቀቱን ሰጠችውና አገጯን ለሁለት እጁ እንደ ደገፈች አቀርቅራ ትክዝ ብላ ቀረች ።

"እማማዬ በጣም እንወድሻለን ። ሁልጊዜ እግዚአለ እማዬን

Brought to You by t.me/bookshelf99

ጠብቃት እያልን እንጸልያለን። መቺ ትመጫለሽ። ሚጡ ላመትባል የተሰጣትን ቸኩሌት ላንቺ አስቀምጣልሻለች። አኔም ቀንጀ ስቦታ አስቀምጬልሻለሁ። ልንመጣ ነበረ። ልጆች አያስገቡም አለን አባባ። እማማዬ ሚጡና እኔ በጣም ናፍቀሽናል እሺ። ቶሎ ቶሎ ነይ።"

ይላል፣ ትልቁ ልጇ የጻፈላት ደብዳቤ። በልብ ቅርጽ ባሸበረቀው ወረቀት ላይ የማይነበብ ሙንሜርሜር ጽሑፍም አለ። እሱ ደግሞ የትንሿ ደብዳቤ መሆኑ ነው። ውስጡ የተሰማው'ን ስሜት እንደምንም ታግሎ ወረቀቱን ለኃላፊ ነርሷ ሰጠና ዝም አለ። ኃላፊ ነርሷ ካነበበችው በኋላ ስላላስቻላት ወረቀቱን ከሌላው ፊት አስቀምጣ ክፍሉን ለቃ ወጣች።

ው-ይይታቸው'ን ሲጨርሱ፣ ዝናሽን አበረታቶና የሚቻለው'ን አድርገው ቶሎ ወደ ቤት እንደሚልኳት ነግሯት ከአባቷ ጋር እንዲያወሩ ጊዜ ሰጧቸው። ጨርሰው ሲለያዩ ሌላው እግረ መንገዱን ይሏቸው ሲሄድ እንደሚችል ሲነግራቸው እምቢ አሻፈረኝ አሉ። ከብዙ መግደርደር በኋላ እሺ ብለው ይዟቸው ከግቢ ወጡ። የመኪናው ንጽህናና ፍጥነት ... የዶክተር ሌላው ደግነትና የልጃቸው ጤና እየተመለሰ መሆን፣ ተደግምረው የተፈጠረባቸው የተደበላለቀ ስሜት በሌላ ዓለም ው-ስጥ እየተንሳፈፉ፣ በሕልማቸው ወዳልታወቀ ስፍራ የሚወሰዱ መስሎ ተሰማቸው። እሱም በራሱ ሐሳብ ው-ስጥ ገብቶ ሲዋልል የስልኩ ጨኸት አነቃው።

"ሃሎ ... ሳንች እንዴት ነህ?" አለ፣ የመኪናው'ን ፍጥነት እየቀነሰ።

"ደህና ነኝ ዶክተር ... ማው-ራት የምትችልበት ሁኔታ ላይ ነህ እንዴ ያለኸው?"

"ኧረ እንዲያው በፈጠረህ ... ይሄንን ዶክተር የምትለው'ን ነገር ተው። አሁን እየነዳሁ ስለሆነ አጭር ነገር ከሆነ ስፒከር ላይ አድርጊህ ማው-ራት እንችላለን።" ጓደኛ ዶክተር አይባልም ቢለውም፣ አሻፈረኝ ብሎ አሁንም ዶክተር ብሎ ነው የሚጠራው። በሶሻል ዎርክ የጀመረው'ን ትምህርት እየጨረሰ ስለሆነ ለተግባራዊ ልምምድ ቦታ እየፈለገ ነው ያለው።

"እስኪ ወደ ፊት ቀስ እያልን እንለምዳለን። ለአሁን ግን ዶክተሩ ይሻለኛል" ብሎ ሣቀ አለና "በቃ አሁን ጊዜህን አልው-ሰድብህ። አንዱ የፐራክቲክሙን ጉዳይ እንዴት አደረክልኝ ልልህ ነበር። ሌላው ግን ቅዳሜ ላንድ ጉዳይ ወደ ሐዋሳ ስለምሄድ፣ ምናልባት ጠዋት ካልኖርኩ ብዬ ልነግርህ ነበር።"

"እንግዲህ ምን ይደረጋል ብቻዬን እሮጣለኋ ..." አለና፣ "አይ ስቀልድህ ነው ... ጓደኞቼ እንቦቦን ካልወጣን እያሉኝ ስለ ነበር እሱን ማድረግ እችላለሁ ... ስለዚህ አትጨነቅ። የተግባር ልምምዱን በተመለከተ ግን ጳው-ሎስ ተፈቅዷል። ሐሙስ እኔም እኖራለሁ። የክሊኒኩ ኃላፊ ነርስ ሲስተር ዘቢባ ትባላለች ... ከሷ ጋር ተነጋግረናል። ጠዋት ሁለት ሰዓት ተኩል የአእምሮ ሕክምና ክሊኒክ ከደረስክ ጥሩ

Brought to You by t.me/bookshelf99

ነው" አለ ፣ ረዘም ላለ ጊዜ መንገዱን ዘግቶ አላሳልፍ ብሎ ከፊቱ የተጋረጠውን ከባድ መኪና እየቀደመ ። ከሳንቾ ጋር የበለጠ ተቀራርበው በየሳምንቱ ቅዳሜ ላይ አብረው ይሮጣሉ ። በየመሃሉም ተገናኝተው ሻይ ቡና ማለት ጀምረዋል ... ከንጹሕና ከልጆቹ ጋርም አስተዋውቋታል ። ንጹሕ ታክሲ በምትፈልግበት ጊዜ ቋሚ ሾፌሯ ሆኗል ።

በቀለበት መንገዱ በኩል ከአለርት ሆስፒታል በፊት ያለው አደባባይ ጋ ሲደርሱ ወደ አቶ በድሉ ዞር አሉና ፣ "ወደ የት በኩል ነው የሚሄዱት አቶ በድሉ?" ሲላቸው ፣ እንደ መባነን ብለው ፣

"ወደ ቤት ነው ... ብዙም አይርቅ ኧረ ... እዚህ ተደረስሁ ይበላኛል ... የቀረውን በግሬ አዘግማለሁ ። እመቤቴ የማታ እንጀራን ትስጥዎ ዶክተር" ብለው ፣ እየተርበተበቱ አጉተመተሙ ።

"ኧረ ግድየለም ሰፈርዎ አደርስዎታለሁ ። እኔም እዛው አካባቢ ኗሪ ስለሆንኩ አይጨነቁ..." ሲላቸው ፣ ትንሽ ተግደርድረው ዝም አሉ ። አቅጣጫውን እየመሩት ወደ ቀሬ አቅጣጫ መሄድ ጀመሩ ። ልጠይቃቸው አልጠይቃቸው እያለ ልቡ ውስጥ ሲብላላ የነበረውን ጥያቄ እንደምንም ብሎ አወጣና ፣ "ይቅርታ አቶ በድሉ ፣ እዚህ አካባቢ ብዙ ከኖሩ ምናልባት ሰው ብጠይቅዎ ያውቁ ይሆን?" አላቸው ።

ደንገጥ ብለው ወደ እርሱ ዞር አሉና ፣ "ማንን ልጄ? እንዳልኩህ አርባ ዓመት ሊሆነኝ ነው እንግዲህ እዚሁ ሰፈር" አሉ ፣ ትንሽ እንደ መርበትበትም እያላቸው ።

"ወይዘሮ ተዋበች ቸኮል ። ጊዜው ቀየ በጣም ... ሠላሳ ዓመት እካባቢ ሳይሆን ይቀራል ብለው ነው ። እሳቸውም የሥጋ ደዌ ለመታከም ከጎጃም መጥተው ነበር እዚሁ የቀሩት ። እንዲያው ምናልባት ብዬ ነው" አለ ፣ ፊታቸው ላይ ያለውን ስሜት ለማንበብ እየሞከረና የሚሉትን በጉጉት እየጠበቀ ። የሥጋ ደዌ ሕመም አንዱ ጦስ በፊት ላይ ያሉ ጡንቻዎ ቻችንን የሚቈጣጥሩትን ነርቮች ሁሉ ከጥቅም ውጪ ስለሚያደርግ ፊትን ስሜት አልባ ግድግዳ ማስመሰሉ ነው ።

"እንጃ ልጄ ... ተዋበች ... ተዋበች ችኮል ... እስቲ ላጠያይቃ ... እንጃ ልጄ ... ስሙ አዲስ አይደለም ... ምን ሰፈሩ እኮ ባህር ሁኗል" አሉ ፣ ግራ እንደ ገባቸው ። ከሙቀቱ ጋር ተደማምሮ የመኪናዋ ጠረን ስለ ታመቀ በርሱ በኩል ያለውን መስኮት እስከ መጨረሻ ከፈተው ።

"በቃ እስኪ ያጠያይቁልኝ ... ከሰሙ ደግሞ ይነግሩኛል ። ለዝናሽም የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለን አይዝዎ እንግዲህ ። አሁን ምንም አትልም ። ይቺ ደግሞ ላንዳንድ ነገር ትሁንዎ ፣ ትንሽ ትረዳዎታለች" ብሎ ፣ ሁለት መቶ ብር በእጃቸው ሲያስጨብጣቸው ፣

"ኧረ ባዛኒቱ ይኼ ሁሉ ምንድነው? ኧረ ባክዎ ዶክተር ... ኧረ አያስፈልግም"

Brought to You by t.me/bookshelf99

ብለው ፣ በመግደርደር እየተርበተበቱ የሚያደርጉትን አጡ ።

"ግድ የለም አባባ ... ለዝናሽ ልጆችም የሚያስፈልጋቸውን ይግዙላቸው ። ምንም አይደለም" ብሎ ፣ ገንዘቡን እጃቸው ውስጥ እንዲቀይ አጥብቆ ያዘቸው ።

ወዲያው ቀና ብለው ወደ ውጪ ግራና ቀኝ አዩና ፣ ፊታቸው ላይ ያለው ድንጋጤ እየጨመረ ፣ "በቃ በቃ ዶክተር ... እየህ ድረስ በቂ ነው ...እይሂች ጋ መጣ ብሎ መከራዬን ነው እሚያበላኝ ። ቤት ኪራይም ይጨምሩብኛል ... ሌባውም ፍዳ ነው ። እዚሁ ያውርዱኝ" ብለው ፣ በፍጥነት የሰጣቸውን ብር ከደረት ኪሳቸው ውስጥ ለመወሸቅ ሲንደፋደፉ አሳዝነውት መኪናውን አቆመ ። ነገሩ ሙሉ ለሙሉ ባይገባውም በሩን ከፍቶላቸው ወርደው እየተገላመጡ ካንድ ስላች መንገድ ገብተው እስኪሰወሩ ድረስ ባይኑ ሸኛቸው ። በቅጡ እንኳ አልተሰናበቱትም ነበር ።

ለርሳቸው ዓይነት ሰው ከርሱ ጋር መታየቱ ይህንን ያህል መዘገ ያለው መሆኑ እንደ ገረመው ፣ መኪናውን አዙሮ ተመለሰ ። አራቱንም መስኮቶች ከፍቶ ነፋሱ በሁሉም አቅጣጫ በጥድፊያ እየገባ ሲወጣ አብዛኛውን የታመቀ አየር ጠራርጎ ቢያወጣውም ጠንከር ያለው የዝናሽ አባት ጠረን ግን ከመኪናው ውስጥ ሲንቀዋለል ቀየ ። ብዙ አሳቦችን ሲያወጣና ሲያወርድ ወደ ቤቱ የመጨረሻ መታጠፊያ መድረሱ እንኳ አልታወቀውም ነበር ።

"ልጆቼ ... ልጆቼ!" የሚለው የዝናሽ እናታዊ የሰቀቀን ድምፅና ወረቀቱ ላይ የተንጠባጠበው እንባዋ ደጋግሞ ፊቱ ላይ ድቅን አለበት ። ከብዙ ዓመታት በፊት እዚሁ ሰፈር ውስጥ ገነትና እናቷ ወይዘሮ ተዋበችም ይኖሩ እንደ ነበር ትዝ አለው ። ያጋጣሚው ነገር እንቆቅልሽ ሆነበት ። 'ሌላ ዘመን ... ሌላ አጋጣሚ ... ሌላ ሰው ... ሌላ ሁኔታ ... እንቆቅልሹ ተፈትቶ ፣ ውስጠ ነገሩ ተከፍቶ ቢታይ ፣ ሁሉም ነገር የቀደመው ነገር ግልባጭ ... ያለፈው ክስተት ድግግሞሽ ... 'ውሃ ቅዳ' መስሎ ተሰማው ። ሕይወት ራሷ ... የታቀደች አጋጣሚ... ሌላና ያው ... አዲስና ድጋሚ ... በግጭት ወስጥ ያለች ስምምነት ሳትሆን አትቀርም' አለ ለራሱ ... በሐሳቡም በድምፁም ።

Brought to You by t.me/bookshelf99

11

ሳንቾ ገና በጠዋት ነው ከእንቅልፉ የነቃው። በማያውቀው ደስታ ተሞልቶ ከመኝታው ላይ ፍንጠር ብሎ ወረደ። የአልጋ ልብሱን እንደ ነገሩ ለበስበስ አድርጎ፣ እየተንጠራራ መስኮቱን ወለል አድርጎ ከፈተው። ከአልጋው ፊት ለፊት ካለው ወለል ላይ ቁጥሩ ያልታወቀ 'ፑሽ አፕ' ሰርቶ ወደ መታጠቢያ ቤት ገባ። ቧንቧው ውኃ ስላልነበረው፣ በጆሪካን ተሞልቶ ከተጠራቀመው ወደ ሳፋው ውስጥ ገለበጠ። ሰውነቱን በቀዝቃዛ ውኃ በጠዋት መታጠብ ልማዱ ነው። ሌሊቱን ሞቆ ያደረው ገላው በረድ ሲልለት ሰውነቱ የበለጠ ቀለለው። ፎጣውን ትከሻው ላይ ጣል አድርጎ እየተንቀጠቀጠ ወደ መኝታ ክፍሉ ገባ። ብርዱ ጋብ እስኪልለት በፎጣው ተጥቀልሎ፣ አልጋው ጫፍ ላይ ተቀመጠና ማታ ይዞ የገባቸውን የስፖርት ጋዜጦች ሲያገላብጥ ቀየ።

ሰዓቱ አንድ ከሩብ ሲል ተነስቶ ለመውጣት ዝግጅት ጀመረ። ባለፈው ሳምንት ላይ የቅርብ ጓደኛው ከፈረንሳይ ይዛለት የመጣችውን ሹራብና ጂንስ ለብሶ፣ ወዲያ ወዲህ እያለ ሞከረው። ከቁም ሳጥኑ መስተዋት ፊት ቆመ። ከራት ለፊቱ ከሚያየው ፈርጣማ ጐፈሬ ወጣት ጋር እንዳማረባቸው ተስማሙ። ነጫጭ ጥርሶቹን ፈልቀቅ አድርጎ ፈገግ ሲል፣ ሰፋ ባለ ሻካራ ፊቱ ላይ ፀሐይ የወጣች መሰለ።

ወደ ኩሽና ገብቶ ትንሿ ባለ ሦስት ጉልቻ የጋዝ ምድጃው ላይ የሻይ ውኃ ጣደ። ተመላላሽ ሰራተኛው ከፍሪጁ ውስጥ በሰሃን ሰርተው ያስቀመጡትን የፍርፍር ቁሌት አውጥቶ ቀነሰና ከሻዩ ጎን ጣደው። ደርቀሽ ጨምሮ ፈጣን ፍርፍር ሰራ። ቁርሱን በቁመ፡ ቀማምሶ ለልጆቹም በሰሃን በሰሃን ድርሻቸውን ጠረጴዛው ላይ አስቀምጦላቸው እያፏጨ በሩን ዘግቶ ወጣ።

ከፈረንሳይ ከመጣችው ጓደኛው ጋር የያዘው የምላ ቀጠሮ እስኪደርስ ልቡ ተንጠልጥሏል። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን በሊሴ ገብረማርያም ስትማር ጠዋትና ማታ በታክሲ ሲያመላልሳት ነው የተቀራረቡት። ከጥቂት ዓመታት በፊት ወደ

Brought to You by t.me/bookshelf99

ፈረንሳይ ሀገር ከሄዶች በኋላ፣ ብዙ ጊዜ በወር አንድ ሁለት ጊዜ ሳትደውልለት አትቀርም። ማታ ላይ ደግሞ ሲስተር ዘቢባ ቤት የእራት ግብዣ ስላለው፣ ዛሬ ቀኑን ሙሉ መሥራት አይችልም። በለስ ቀንጭት በጠዋት ያገኛቸውን ሁለት የኮንትራት ሥራዎች ረፋዱ ላይ ጨረሰ፣ ጠቀም ያለ ብር ኪሱ አስገባ። ከዚያም እስከ እኩለ ቀን አካባቢ መስመር ገብቶ ሲሠራ ቆየ።

ከአትላስ ጆርባ ከሚገኘው የጓደኛው ወላጆች ቤት በሰዓቱ ደረሰ። ዘበኛው በሩን ከፍተውለት ገብቶ መኪናውን ግቢው ውስጥ አቆመና እያመነታ ወረደ። ሁሌም እዚህ ቤት ሲመጣ የቤቱ ግዝፈትና ግርማ ሞገስ፣ በርሱና በላዳ ታክሲው ላይ ትከሻውን ቸልሎ የሚያሾፍባቸው ይመስለዋል። ተወልውለው እያብረቀረቁ ግቢው ውስጥ የተደረደሩት ሉሎች መኪኖች ደግሞ ያንን እየሰመ የሚያላግጡበት። በረንዳ ላይ ሆና ስትቁነጠነጥ የነበረችው ጓደኛው ከሩጫ ባልተናነሰ ፍጥነት ወደ እርሱ መጣች። አጠገቡ ደርሳ አቅፋ ሰላም ስትለው፣ 'ይሄን የመሰለ ግቢ ውስጥ የተፈጠረች ይቺን የመሰለች ቄንጆ ልጅ አሁን እኔ ላይ ምን ያንጠላጥላታል?' አለ ለራሱ።

የተቀባችው ሽቶ መዓዛ እንኳንስ በሕይወት ያለን ሙታንን የመቀስቀስ ኃይል አለው። "ላንች ... ጊዜው እንዴት ነው የሚንቀራፈፈው። ደጋግሜ ደውዬልህ ነበር እኮ። ኡፍ ያቺ ስልክህ ላይ ያለችው ደረቅ ሴትዮ ... ምን አታጥል የሆነችው ናት በናትህ ... 'ደንበኛዬ ባካባቢው የለምና አትጨቅጭቂው' ምናምን ስትል እንዴት እንዳናደደችኝ ብታይ" ስትል ፈገግ አለና፣

"ኧር ዝም በያት ... ከጠዋት ጀምሮ እኮ አብራኝ ነበረች። ሰው ሲደውልልኝ በጣም ነው የምትቀናው" ሲላት፣ ንዴቷ ሁሉ ባንዴ ጠፍቶ መስቅ ጀመረች። እጁን እንደ ያዘችው ሽቅብ እያየች ስታወራው፣ 'ላሜርም አሜር አለው ለካ' ብሎ ውስጡ ደስ አለው። ወዲያው ደግሞ 'አይ ሰው መሆን ... አሁን ይህቺም የቁመት ልዩነት ብልጫ ሆኖ ነው' ብሎ፣ የራሱን ደስታ ታዘበ። ልጅቱ በቀጭን ሚጢጢዬ ሰውነቷ ላይ የሶስት ሰው ውበት ያንቀጠቀጣት፣ የእናቷ ግልባጭ ትመስላለች።

"በቁምህ ጁስ ነገር ቅመስ በናትህ ... በዛውም እነ ባቢም ስላሉ ሰላም ብለሃቸው እንወጣለን" ስትለው፣ ክብድ ብሎት እያመነታ፣

"ይሻላል ብለሽ ነው...?" ሲል፣ እጁን እንደ መጮተት በአንድ እጇ ሳብ እያደረገችው፣

"በጣም እኮ ነው የሚወዱህ ... ደበረህ እንዴ መግባቱ?" አለች፣ በሌላ እጇ ከሹራቡ ስር ያለውን የሸሚዙን ኮሌታ እያስተካከለችለት። 'እንኳን እነርሱ እንቺም ለምን እንደምትወጂኝ ሊገባኝ አይችልም' የሚል የውስጥ አሳቡን ዝም ለማስባል እየታገለና እያመነታ ተከተላት። የሳሎኑ በር ሲከፈት አይን የሚያጭበረብር ውበት ከተላበሱ የቤት እቃዎችና የግድግዳ ስዕሎች ጋር ፊት ለፊት ተጋፈጠ። በነርሱ

Brought to You by t.me/bookshelf99

የኮንዶሚንየም ሰፈር የርቀት አለካክ ህግ 'ከማዶ ያለው ብሎክ' በሚባል ርቀት ላይ ወላጆቿ ተቀምጠዋል። የተቀመጡባቸው ሶፋዎች እያንዳንዳቸው አንድ ጥሩ ላዳ ታክሲ ሊገዙ የሚችል ዋጋ አላቸው። ወደ ወላጆቿ አማተረና ቀም አለ። ከፊቱ ያለው ምንጣፍ ላይ መረማመድ የሰው ፊት የመርገጥ ያህል ስለ ዘገነነው ጫማውን ሊያወልቅ ጎንበስ ሲል፣ አሻፈረኝ ብላ እጁን ያዘችው።

አባቷን ከጨበጠ በኋላ እናትዬው በጉንጭ ለጉንጭ ግጭት ሳሙትና፣ "ሳንችዬ ... በቃ ሰሚር ከሌለች እኛ አንጠየቅም እንዴ?" አሉ፣ እጁን ሳይለቁ አይን አይኑን እያዩ ላቅ ብለው።

"ምን ... ሁል ጊዜም ለመምጣት አስባለሁ እኮ፤ አልሞላ ብሎኝ ነው እንጂ። እናንተም በጣም ቢዚ ትሆናላችሁ ብዬ ስለማስብ ..." ብሎ፣ ራሱን አከክ አከክ አድርጎ አሞነበሰ። ከጫካው ወጥቶ በከተማ መሃል እንደተገኘ የዱር አውሬ እጅና እግሩ ረዝሞ ተሳስረበት። እንደቄሙ ትንሽ አውርተው እንዲቀመጥ ቢጋብዙት አሻፈረኝ አለ። ሰሚራ ለመውጣት ተዘጋጅታ ቦርሳዋን ይዛ ከላይ ስትወርድ ውስጡ ተንፈስ አለለት። ሌላ ጊዜ ለመምጣት ቃል ገብቶ ተከታትለው ሲወጡ፣ ወላጆቿም የሳሎኑን በር አስወጥተዋቸው በረንዳው ላይ ጐን ለጐን ቆሙ።

የሳንቾ አሮጌ ላዳ መኪናም መስላ የማትታያቸው አባቷ፣ "አንቺ ሰሚር ... ወይ ባይሆን ለምን የኔን ወይም የናትሽን መኪና አትይዙም?" አሉ በጎርናና ድምጻቸው። በፒጃማቸው ላይ የደረቡትን የቤት ቤት ካባቸውን ሰብሰብ አድርገው የምድር ወገብ ከመሰለ ወገባቸው ላይ በማሰሪያው ሸብ አደረጉት። የሰውነታቸው ግዝፈት አስገምጋሚ ድምጻቸው የሚሰራበት ፋብሪካ ይመስላል።

"ኖ ... ባ-ቢ ... ዋናው ቁም ነገሩ ያለው እኮ ... በላዳ መሄዱ የሚሰጥህ የልጅነት ትዝታና ነጻነት ላይ ነው። ከፈለግህ አንተ ና ና ተሳፈር" ብላ ስትስቅ፣ ሚንቅላታቸውን ወዘወዙ። "በሉ መልካም ቀን ... ደህና ዋሉ" ብላ ቦርሳዋን የኋላ ወንበሩ ላይ ጣል አድርጋ እጁን አውለብልባ ገባች። ሚስታቸው ትከሻ ላይ የጫኑትን እጃቸውን አንስተው አጸፋውን መለሱላት።

"ደግሞ ቀስ ብላችሁ ንዱ" ሲሉ እናቷ፣ በፈገግታ እጁን ሳም አድርጋ ወደ እርሳቸው መልሳ ዘርጋችላቸው።

ከግቢ እንደወጡ፣ "ምንድነው ምላ ያሰኘሽ?" አለ ትንሽ ዘና ብሎ።

"የገል ጥብስ ... ያ ቤት ምን ነበረ ስሙ ... ያኔ የምንበላበት ቦታ ..."

"ጊርጊሮ?"

"አዎ ... በናትህ እሱ ቤት አለ አሁንም?"

"ቦታ ቀይረዋል ... ቀይ እንደውም ሌላ ቦታ ላሳይሽ። ጥሬ ሥጋ መሞከር ትፈልጊያለሽ?"

Brought to You by t.me/bookshelf99

"በልቼ አላውቅም እኮ ... ቢያመኝስ?" ብላ ስታመነታ፣

"ትታከሚያለሻ ... ደግሞ ምንም ጣጣ የለውም የታከመ ሰጋ ነው። እንዲያውም አዲስ ሰው ሲበላው ሥጋው ነው የሚታመመው ..."

"ኧረ ባክ ..." ብላ ሳቀችና፣ "እንሞክረዋ ... አይገድለን። ለነማሚ ግን አንናገርም እሺ" ስትለው፣ 'አንቺው ካልተናገርሽ እኔማ በምን አቅሜ' አለ በሆዱ። "እንዲያውም ላባትሽ ነው የምነግራቸው። ልጅዎ አንድ የበሬ ሽንጥ ጨርሳ እዳ ውስጥ ከተተችኝ ብዬ"

"እሱማ እንድበላለት ነው የሚፈልገው እኮ። እንደሱ ብለህ ብትነግረው የወርቅ ሜዳሊያ ነው የሚሸልመኝ። እሱ ራሱ እኮ አንድ ቁጥር ቀራጭ ነው።

"እሱን እናያለን ... አበላልሽ ታይቶ" አለ። በተጋጩ መኪኖች ምክንያት መንገዱ ስለተዘጋጋ መንገድ ቀይሮ ውስጥ ውስጡን አሳብሮ ከምሳ ቦታው ደረሱ። ምሳ፣ ቡና ሲሉ፣ ከሰዓት በኋላው ሳይታወቃቸው ነበር ያለቀው። የማታ የእራት ቀጠሮው እየደረሰ ስለነበረ፣ እንዳሰቡት አብረው ቀይተው ፊልም ለማየት አልቻሉም። ወደ ቤቷ አድርሷት ሲመለስ፣ ለረጅም ጊዜ በልቡ ውስጥ አፍኖ ያቀየው ስሜት እንደገና ሲያገረሽበት ተሰማው። ከሁሉም ጋር ተግባቢና ጓደኛ ስለሆነች ለርሱ ያላት ስሜት ምን እንደሆነ በትክክል ሊያውቅ አልቻለም። ስለዚህ ከውስጡ ልውጣ ልውጣ ስሚለው ፍላጎቱ ፊት ሊሰጠው አልፈለገም። እሷ እንኳን ብትወደው ቤተሰቦቿ የማይገፉ ተራሮች መስለው ታዩት።

እሷን አድርሶ ሲመለስ፣ ማታ ሲስተር ዘቢባ ቤት ይዞ የሚሄደውን ኬክ ገዝቶ አፓሬ አካባቢ ወደሚገኘው ኮንዶሚኒየሙ በቀጥታ ነዳ። ሲገባ ልጆቹ ጮን ለጮን ተቀምጠው እያጠኑ ነበር። ይዞ የሚሄደውን ኬክ ፍሪጅ ውስጥ ከተተና ያመጣላቸውን ጥብስ አካፍሎ አቀረበላቸውና ግንባራቸውን ሳም ሳም አድርጎ ወደ መኝታ ቤቱ ገባ። ትንሽ ማረፍ ስለ ፈለገ፣ በሩን መለስ አድርጎ ጫማውን ብቻ ወለቅ ወለቅ አድርጎ አልጋው ላይ ጋደም አለ። ስለ ውሎው እያሰበ ሽለብ እንዳደረገው፣ የጥልና የለቅሶ ድምጽ ሰምቶ ወደ ሳሎን ሲሄድ፣ ያክስቱ ልጆች አንገት ላንገት ተናንቀው ይደባደባሉ።

"እንዴ ምንድነው እሱ? አቁሙ ብያለሁ፣ ሁለታችሁም ቁጭ በሉ እዛ ሶፋ ላይ" ብሎ ሲያንባርቅባቸው፣ በመካከላቸው መብረቅ ገብቶ የለያያቸው ያህል ተነጣጠሉ። ፈንጠር ፈንጠር ብለው በእልህ እያለከለኩ ቁጭ ቁጭ አሉ።

ታናሽዬው ከድር ገና ሳይጠየቅ እንባው ዱብ ዱብ እያለ፣ "ራሷ ናት መጀመሪያ የተጣላችው ... እኔ ምንም ሳለደርጋት" ሲል፣

ታላቅ እህቱ ሃሊማ ደግሞ፣ "የበላበትን ሣህን አንሳና አጥበህ አስቀምጥ

Brought to You by t.me/bookshelf99

ስለው፣ የሴት ሥራ አልሠራም ብሎ እንደ ልማዱ ሊሮጥ ሲል ... እዚህ ገረድ የለህም አንሣት ስለው ... አላቅልሽም ከፈለግሽ ራስሽ እጠቢ ብሎ ሣህኑን መሬት ላይ ወርወሮ፣ ሊሮጥ ሲል ነው ይገር የመታሁት" ብላ፣ እልህ እየተናነቃት የራሷን ታሪክ አቀረበች። ዕድሜያቸው ሰባትና ዘጠኝ ነው።

"አንተ ለምንድን ነው የበላህበትን የማታጥበው?" አለ ሳንቾ፣ ወደ ከድር ዞሮ።

"እኔ ጥናት አለብኝ ነው ያልኳት ..." ብሎ፣ አቀረቀረ።

"ዝም በለው የሴት ሥራ ነው ... ራስሽ እጠቢ ነው ያለው። ደግሞ መኝታ ቤቱን ሁሉ እያቀሸሸና እያዝረከረከ ተው ስለው ይሳደባል። አልጋ ማንጠፍ ... እም ... ቤት ማጽዳትና ዕቃ ማጠብ የሴት ሥራ ነው ... እያለ ... ደግሞ በቀደም 'ገረድ' ብሎ ተሳድቦ ወደ ውጭ ሮጧል" ብላ፣ ሳግ እየተናነቃት አለቀሰች።

"እሺ በቃ ዝም በይ ... ይሄስ ውሸት ነው?" አለ ሳንቾ፣ ቁጣው እየጨመረ። አንገቱን አቀርቅሮ ዝም አለ። "ተናገር እንጂ ... በመጀመሪያ እሷ ታላቅህ እንደሆነች አታውቅም? የምን መወጣጠር ነው። ማነው ደግሞ እቃ ማጠብና ቤት ማጽዳት የሴት ስራ ነው ብሎ ያስተማረህ። በል አሁን ተነሳና ይቅርታ ጠይቅ ..."

ጎንበስ ብሎ ቀየና፣ "ራሷ ናት ጥፋተኛ ... ምን አድርጌ ነው ይቅርታ የምጠይቃት?" ሲለው፣ ሳንቾ የጎዴት ሳቅ ሳቀ።

"እሺ አሁን ሁለታችሁም ኑ" ብሎ፣ ጠረጴዛ ላይ ያለውንና መሬት የወደቀውን ሣህን አንስቶ፣ ወደ ጓዳ አስከትሏቸው ገባ። ሁለቱም ካጠገቡ ፀጥ ብለው ቀሙ። ሣህኖቹን አጣጥቦ ማድረቂያው ላይ ደረደረና ኩሽናውን እያጸዳ ሻይ ጣደ። "ከድር ... እኔ ወንድ ነኝ ሴት?" አለው ጠጋ ብሎ።

"ወንድ" ብሎ አጉተመተመ እንዳቀረቀረ።

"እና ዕቃ ስላጠብኩ ምን ሆንኩኝ? ወንድ ስለሆንኩኝ ዕቃው አልታጠብም አለኝ?" ሲለው ቀና ብሎ አይኑት በእፍረት ዝም አለ። "አየህ ሥራ ጾታ የለውም። ከዛሬ ጀምሮ እዚህ ቤት የሴት የወንድ የሚባል ነገር የለም። እንዲያውም ሁሉንም ሥራ በየተራ ነው የምትሰሩት። ልክ እንደ አንተ ሃሊማም መጫወትና ማጥናት ትፈልጋለች። እማማ ሲመጡ የሚሠሩት እኛ የማንችለውን ሥራ ብቻ ነው። እሺ ... አሁን ጊዜ የለኝም፤ የቀረውን ማታ ስመለስ ወይም ነገ እናወራለን። አሁንስ እህትህን ይቅርታ መጠየቅ ትፈልጋለህ?" ሲለው

"ይቅ...ር...ታ" አለ በሃፍረት ድምፅ፣ ፊቱን ከመሬቱ ላይ ሳይነቅል።

እንዲተቃቀፉ ካደረገ በኋላ "በሉ አሁን ወደ ጥናት። ከዛ በፊት ሂድ ስልኬን ከታክሲ ውስጥ አምጣልኝ" ብሎ ላከው። ትንሽ ቀየት ብሎ ሻይን ቀድቶ ከመጣላቸው ኬክ ጋር ከፊት ከፊታቸው ሲያስቀምጥላቸው በደስታ ተፍነከነኩ።

Brought to You by t.me/bookshelf99

ወደ ጓዳ ተመለሰና የራሱ ሻይ ውስጥ ትንሽ ፈጣን ዱቄት ቡና ጨምሮ እያማሰለ ምስጢር ጋ ደወለ ።

"ሂይ ሰኢዶ ... አልተነሣሁም እንዳትለኝ ብቻ ... እየመሸ ኮ ነው?" ሳንቾ የሚለው ስም ብዙም ስለማይጥማት ፣ ሰኢዶ ብላ ነው የምትጠራው ። ሚች አክስቱ ብቻ ነበረች ሰኢዶ የምትለው ። ከምስጢር ጋር ከተዋወቁ ጥቂት ሳምንታት ቢሆንም በፍጥነት ነው ተግባብተው የተቀራረቡት ።

"ይቅርታ በናትሽ ... እዚህ ስንጐዳጐድ እኮ ጊዜው ከነፈ ። አሁን ልወጣ ነው በቃ ... የት እንገናኝ?" አለ ፣ ወደ መኝታ ክፍሉ እየሄደ ።

"ለምን እኛ ሰፈር ሮቤራ ቡና አንገናኝም? ሁለታችንም ከምንነዳ ካልደከመህ ያንተን መኪና ይዘን እንሂድ?"

"ጥሩ ... በቃ አንድ ሠላሳ ደቂቃ ከሰጠሽኝ ደርሳለሁ ። እነ ዶክተር ጋ ደውለሽላቸው ነበር እንዴ?"

"አይ አልደወልኩም ... ለምን አንተ አትደውልላቸውም? በቃ አታርፍድ ግን እሺ?"

"እየወጣሁ ነው ... አሁን እደርሳለሁ" ብሎ ፣ ስልኩን ዘጋ ። "በሉ እኔ አንድ ቦታ እራት ስላለኝ መሄዴ ነው ። ድንገት ከቀየሁ ግን ራታችሁን በልታችሁ መተኛት ትችላላችሁ ... እሺ?" ሲል ፣ ሁለቱም ባንድ ድምፅ "እ-ሺ" አሉ ። መጣላታቸውን ረስተው እየተሣሣቁ ኪካቸውን ለመጨረስ እየተጣደፉ ነው ። በመገረም ሜንቅላቱን ነቅንቆ 'አይ የልጅ ጥል' ብሎ ፣ ወደ መኝታ ቤቱ ተመለሰ ።

በችኮላ ልብሱን ለውጦ ፣ ፍሪጅ ውስጥ ያስቀመጠውን ኬክ ይዞ ወጣ ። ሌላሠው ጋ ሲደውል ከቤት ወጥተው ሚክሲኮ አካባቢ መድረሳቸውን ንጹሕ ነገረችው ። ሮቤራ ሲደርስ ታክሲውን አቆመና ምስጢር ሳታየው ከጐኗ ቀስ ብሎ እጁን ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጎ በወፍራም ድምፅ ፣ "እዚህ ቤት አትምጭ አላልኩም ነበር" ሲላት ፣

"ማሚዬ ..." ብላ ፣ በድንጋጤ ተስፈንጥራ ብድግ ስትል ሣቁን ለቀቀው ።

"ሂ ...ዛ ... ምንድነው አንተ እንደዚህ ሰው ማስደንገጥ ። ቀልቤን ገፈፍከኝ እኮ ። ደግሞ ማርፈድህ አንሶህ ነው ..." ብላ ፊርጣማ ትከሻው ላይ በጨበጠችው እጁ መታችው ። ጆሮዋ ላይ ያደረገችውን የሙዚቃ ማዳመጫ አውጥታ ቦርሳዋ ውስጥ ጨምራ ሰላም ተባባሉ ።

"ው ይይይይ በናትሽ ... አንቺ ግን ምንድነው እንደዚህ ማማር ... ወላሂ ... ለኛም ሞራል መጠንቀቅ አለብሽ እኮ ... ደሞ ቁመታችንን እንዴት ነው የጨመርነው? ... ማንን ለማሳጣት ነው?" አለ ፣ እጁን እንደ ያዘ ካጠገቧ ቀሞ ቁመቱን ከሆነው በላይ አሳጥሮ እየቀለደ ።

Brought to You by t.me/bookshelf99

"አቤት አቤት ... የምን ማጋነን ነው ... የምር የምር ግን ... ቁመቱን ግን አስብበት ... እስኪ እስኪ" ብላ ጮኑ ቀም ስትል፣ ካደረገችው ረጅም ታክ ጫማ ጋር በደንብ በልጣዋለች። በትከሻዋ ገፋ እያደረገችው፣ "አይ ሰኢዶ ዛሬስ የምር ተበልጠሻል ... እንግዲህ መከባበር ያስፈልጋል። ዛሬ አለባበስህ አልተቻልክም ... የ-ም-ር። ሽቶው ደግሞ የላቀ ነው ... ማን እንበለው?" አለች ዓይኖቿን ዘጋ አድርጋ ሽታውን እንደሚያጣጣም በረጅሙ ወደ ውስጥ እየሳበች። ለሽታና ለሽቶ፣ ለድምፅና ለሙዚቃ ስል ስሜት አላት።

"እኔ እንጃ ... ስሙን ለናንተ ትተነዋል ... የኛ ሥራ ከብልቃጡ እስኪያልቅ መነስነስ ነው። አንዱ ጓደኛዬ ነው ባለፈው ከጣሊያን ያመጣልኝ ... አዛሮ ነው አዝራሮ ያለኝ ባክሽ ... ምን ለውጥ አለው ብለሽ ነው" ሲል ትከሻውን ደገፍ ብላ ሣቋን ለቀቀችው።

"ሁሉም ሰው እንዳንተ የማያካብድ ቀለል ያለው ቢሆን እንዴት ጥሩ ነበር" አለችና ኮሌታውን ትንሽ አስተካክላለት፣ "በል በል አሁን እንሂድ ... ሰአቱ በጣም ሄዷል..." ብላ ወጡ።

"ምንድነው ደግሞ የተሸከምሽው?" አለ፣ በፈስታል የያዘችውን ነገር እየተቀበላት።

"አይ ትንሽ የተቀላ ቡና ... ያው ቤቱ እንዳይለምድብን።"

"እንዲያውም ሙች ... ቡና ይዘሽ ከሄድሽ በጣም ነው የሚለምድብሽ ... ካሁን በኋላ ከዛ ቤት ላትጠፊ ትችያለሽ። እንዳይለምድብሽ ከፈለግሽ ኬክ ነው መድኃኒቱ" ሲል፣

"ምን እዚህ ሰፈር ... ኬክ ከየት ይመጣል? እንዲያውም ካልከስ ይልመድብኝ ... ሲስተርዬ እኮ ነፍሴ ናት። እናት ነገር የሆነች ሰው ..." አለች፣ በሩን ከፍቶላት ስትገባ። ከኋላ ወንበር ላይ ያስቀመጠውን ኬክ አየችና እየሣቀች፣ "አጅሬው ተነቃብህ ... ለካ የጫንከውን ሜነህ ነው ኬክ ምናምን የምትለው። ጮበዝ ልጅ ነህ ግን ... ማሰብህ ይበቃል" አለች፣ ትከሻውን መታ መታ እያደረገች። ለመሣቅ ትንሽ ነገር ይበቃታል።

የለበሰችው ጥልቅ ድምቀት ያለው ጥቁር ቀሚስና ፍንትው ያለ ውሃ ሰማያዊ ጃኬት ተፈርፍሮ ከተበተነው አጭር ጸጉሯ ጋር የቀይ ጠይም መልኳን ይበልጥ አስውቦታል። ፍልቅልቅ ብላ ስትሥቅ ደግሞ የብርሃን ፈላሽ የተደፋባት ትመስላለች። ውበትን ለመካብ ቃላትአጥሮት የማያውቀው ሳንቾ ደግሞ ሲያደንቃት አፈር ብላ፣ "ውይ በቃ የምን ችክክ ማለት ነው" አለችና ቀንጠጥ አደረገችው።

"የምር የምር ግን ... እኔና ፉንጋ ታክሲዬ አንቺን ሜነን ለእራት ስንሄድ

Brought to You by t.me/bookshelf99

የሚለማንን ክብር ብንገልጽ ችክ ማለት ይባላል? ... አላህ ቀንጅ ሰውና ምርጥ የጥራጌ ክትፎ ባይፈጥር ኖሮ ሕይወት ምንኛ አሰልች ትሆን ነበር" ብሎ፣ ዓይኑን በዘገ አድርጎ፣ ጉንጩን በሣቅ ሞልቶ በጐን አየት ሲያደርጋት፣

"መጎቻካ ሆነሃል እኮ ሰኢዶ ... እስኪ በቃ አሁን አፍህን ዘግተህ አርፈህ ትነዳ" አለች ፊቷን በመኪናው መስተዋት እያየች። እቤት ባክስቱ ልጆች መካከል ስለ ተፈጠረው ጥልና ምን እንዳደረገ ነገራት። በሴት ልጆች ላይ ካስተዳደግ ጀምሮ ስለሚደርሰው ጫናና ሚዛን ያጣ ኃላፊነት፣ በትምህርት ቤትና በውጪም ስለሚደርሰው ተጨማሪ አድልዎና ፈተና በዚያው አንስተው አወሩ። ትንሽ ከመነታች በኋላ ከኮሌጅ ጀምሮ እየተከታተለ ወድጄሻለሁ እያለ ስለሚከታተላት ልጅ የተወሰነ ነገር ነገረችው።

"እና ምን ሆነ መጨረሻ ላይ ... አቆመ መከታተሉን?"

"አዪ ምን ያቆማል ... ባሰበት እንጂ ..."

"ለመክሰስ ምናምን አልሞከርሽም?"

"ወይ መክሰስ ... ያልደረስንበት ቦታ አልነበረም ... ትምህርት ቤትም ለራሳቸውም እየፈሩት ይሁን አላወቅም ዝም ብለው ማስጠንቀቂያ እየሰጡ እንደ ቀለደብኝ ጨርሶ ወጣ። እኔ ሁለተኛ ዓመት ስደርስ ነበር እሱ የተመረቀው። ከጨረሰ በኋላ እንኳ ግቢ እየገባ ሲያስፈራራኝ ... እስክ ቤት እየተከተለ ሲነዘንዘኝ ምንም ላደርግ አልቻልኩም። በኋላ ከእናቴ ጋር ሆነን ብንከስም ፍርድ ቤቱም ምንም ሊያደርግ አልቻለም። አንድ እንደ እሱው ማን አለብኝ ባይ ባለስልጣን አጎት አለው። ፖሊሶቹም የማን ዘመድ መሆኑን ሲያውቁ፣ በቃ አይተው እንዳላየ ነው የሚሆኑት።"

"እናስ መጨረሻ ምን ሆነ?" አለ፣ የነገሩ ፍጻሜ እያጓጓው፣

"በኢሜልና በስልክ እያስፈራራኝ የሱ ብቻ መሆኔንና በፈለገ ቀን የራሱ እንደሚያደርገኝ ይነግረኛል። በቃ እንዴት እንደሆነ አላውቅም የምወጣበትንና የምገባበትን ሁሉ ያውቃል ነው የምልህ። ሲለው አንድ ቀን ጠልፎኝ ስለሚጠፋ እንድዘጋጅበት ይነገረኛል። ማሰብ ትችላለህ ... የገዛ ጥላዬን እንደ ሽሽሁ ነበር የምኖረው። ማታ ላይማ በተአምር ለብቻዬ አልወጣም። ከዛ ላለፈው ዓመት ከዘጠኝ ወር ጠፍቶ ነበር። ውጪ ሀገር ሄዷል ሲሉ ሰምቼ እፎይ ብዬ ነበር" አለችና ከለፈው አንድ ወር ጀምሮ እየደወለ እንዳስቸገራትና እንደሚከታተላት ልንገረው አልንገረው ብላ አመነታች።

"እና ... አልሄደም?" አለ ፊቱን ወደሷ ዞር አድርጎ እያያት

"እኔ ምን አውቃለሁ ... ካለፈው ወር ጀምሮ ደሞ መደወል ጀምሯል። ስልክ ቁጥሬን ቀይሬ ነበር። ማን እንደሚሰጠው አላውቅም። አንዳንዴ የትና

Brought to You by t.me/bookshelf99

ከማን ጋር ምን ስሠራ እንደ ዋልኩ ሁሉ ዝርዝሩን ጨምሮ ቲክስት ያደርግልኛል። በታ ያ የጠፋው ፍርሀቱ ሁሉ እንደገና አገርሽቶብኛል ... ለማሚ ደግሞ ልነግራት አልፈለኩም። ብታይ እንዴት እንደምትፈራው" አለች፣ ፍርሃት በተሞላ ፈት ሰውነቷን ስብስብ፣ ፊቷን ሙምትርትር አድርጋ።

"ምናይነቱ ሳይኮ ነው በናትሽ ... ጤነኛ ነው ግን? ለመሆኑ ሥራ ይሠራል ... ስለርሱ ምን ያህል ታውቂያለሽ?" አለ፣ እነ ሲስተር ዘቢባ ሰፈር ስለ ደረሱ መንገዱን በጥንቃቄ እያየ። ልቡ በወፈው እንደ ተያዘ ስላወቀች፣

"ታሪኩ ብዙ ነው፣ ሌላ ጊዜ እጨርስልሃለሁ። ቆይ ሲስተር ጋ ልደውልላት መሰለኝ ... ደርሰናል ... በዛኛው መንገድ ጋ ይመስለኛል ..." ብላ፣ ስልኳን አውጥታ መደወል ጀመረች።

መኪናቸውን አጥር ሥር አቁመና ከንዱን ያዝ አድርጋ፣ የውጭ በሩ ጋ ሲደርሱ፣ ከሲስተር ዘቢባ ጋር ተከታትለው ገቡ። በአንድ ሺህ ካሬ ሜትር ግቢ ውስጥ የተሠራው ትልቅ ቤት፣ በአበቦችና በተለያዩ ባርኾች ተከቦ፣ ትንሽ ቤተ መንግሥት ይመስላል።

"ሲስተርዬ ... ው-ይ-ኔ እንዴት ያምራል ግቢያችሁ ... አረፈድን እንዴ?" ብላ ተቃቀፉ።

"የኔ ቀንጆ ታንክ ዩ ... ደግሞ እንዴት እንዳማረብሽ ... ትፍ ትፍ ... ካይን ያውጣሽ ልጄ ... ምንድነው ደግሞ ይሄ የተሸከማችሁት?" ብላ፣ የያዙትን ዕቃ ተቀብላ ተከታትለው ገቡ። ወደ ሳሎኑ ሲገቡ ከፍ ያለ ጣሪው፣ ሰፋፊ መስኮቶቹ፣ በቀለምና በመጠን ከቤቱ ጋር ተዋሕደው፣ በጥራትና በዓይነት የተሰካኩት የቤት ዕቃዎች ቦታ ቦታቸውን ይዘው ቀልብን ይስባሉ። ቀድሞ የደረሰውን ሲራክንና የሲስተር ዘቢባን ባል ሰላም ብለው፣ ሳንቾ ፈንጠር ብሎ ሲቀመጥ፣ ምስጢር ደግሞ ከሲስተር ዘቢባ ጋር ተያይዛ ምግቡ ወደ ተደረደረበት ጠረጴዛ ሄደች።

"ሲስተርዬ ወይኔ ... ቤታችሁ ... በጣም ነው የሚያምረው ... እኔ አልሄድም እዚሁ ነው የምኖረው ..." ብላ ስትሥቅ፣ ጉንጯን ያዝ አድርጋ፣

"አግኝቼ ነው አንቺን የመሰለች ልጅ ... የኔ ቀንጆ ... ወደድሽው? ታንክ ዩ" አለች፣ የሷም ፊት በፈገግታ ተሞልቶቀ። የምግቡ ሽታ ቤቱን አውዶታል። በቀስታ የተከፈተው በመግሪያ ብቻ የተቀነባበረው ሙዚቃ ደግሞ ቤቱ ውስጥ ደስ የሚል ሞቅ ያለ ድባብ ፈጥሯል። ከባሻገር የዶክተር ሲራክና የአቶ ሲራጅ ወሬ ጐልቶ ይሰማል። አልፎ አልፎ ሰረቅ እያደርገ ምስጢርን ቢያያትም፣ እሷ ግን ቀልቧ ሁሉ ሌላ ቦታ ነበር። ሳንቾ ደግሞ ከገባ ጀምሮ አገጉበሶ ስልክ ያወራል።

እነ ሌላሠው ከሲስተር ዘቢባ ቤት ሲደርሱ ላንድ ሩብ ጉዳይ አካባቢ ነበር። ሕፃናቱ አርሴማና ዲንሳ ያመጡትን ቸኮሌትና ስኦታ ካልያዝን ብለው ስላስቸገሩ ንጹሕ እየረዳቻቸው የበረንዳ ደረጃውን ወጡ። የቤቱ በራፍ ላይ ሲደርሱ

Brought to You by t.me/bookshelf99

ሲስተር ዘቢባ አስገባቻቸው። ንጹሕ እንደ ገባች ከአንድ ጥግ ላይ ከተሠየመው ጥቁር ፒያኖ ላይ ዓይኗ አረፈ።

"እስኪ ወደ እዛ እለፉ ... እዛች ሶፋዋ ላይ አረፍ በሉ። ሲራጅ ... ተዋወቃቸው ... ሁሉ የሚገራልህ ዶክተር ሌላው ማለት እሱ ነው። ያው በቲለቭዥንም አይተኸዋል አይደል?" አለችና ልጆቹ የተሸከሙትን ስጦታ ተቀብላ፣ እቅፍ አድርጋ ስማ ስታመሰግናቸው፣ በደስታ እየቦረቁ ወደ እናታቸው ሮጡ።

"ሙኒር ... የት ሄደች ልጄ ... አንቺ ሙኒራ ..." ብላ ተጣራች ሲስተር ዘቢባ። ከላይ አንዲት ቀንጅዬ ልጅ እየተንደረደረች ስትወርድ "ይሄው ዶክተር ሌላው ..." ስትላት፣ እንደ ማፈር ብላ ስትሸኮረመም አንገቷን እቅፍ አድርጋት "እ--ን--ዴ የምን መሸኮርመም ነው። ይሄው ቤትሽ ድረስ መጣልሽ ... በይ ሰላም በያቸው እንጂ" አለቻት። ወደ ሌላው ዞራ፣ "አድናቂህ ናት ... እሷም ሳይካትሪስት ነው መሆን የምትፈልገው። ሙኒራ ማለት እሷ ናት" ስትለው፣

"ኦህ ታዲያስ ... ብዙ ነገር ነው ስላንቺ የሰማሁት ..." አለና፣ እንደቀሙ ትንሽ አወራት። ሁሉንም ሰላም ካለች በኋላ፣ የእናቷን አንገት አቅፋ እግሯን እያወዛወዘች ቀመች። ዕድሜዋ አሥራ ስድስት ሲሆን የአሥራ አንደኛ ክፍል ተማሪ ናት።

"ዛሬ ብዙ ጥያቄ መመለስ ሳይኖርባችሁ አይቀርም። እንዴት ዓይነት ጂኒየስ ልጅ መሰለቻችሁ። ብዙ ጥያቄዎቿን እኛ እንኳን ልንመልሳቸው አንደርስታንድ ለማድረግም አልቻልንም" አለ፣ አባቷ አቶ ሲራጅ፣ አንዴ ሲራክን አንዴ ሌላውን እያየ።

"አ-ባ-ቢ ..." ብላ ቄጣ ስትል፣ ሰቀ ዝም አለ።

"በጣም ደስ ይላል ...ብራቮ ሙኒራ" አለ ሲራክ።

ምስጢርና ንጹሕም አጠገብ ላጠገብ ተቀምጠው የሞቀ ወሬ ይዘዋል። ሳንቾ ሁለቱን ሕፃናት ባንድ ላይ ታቅፎ ተራ በተራ እየኰረኰረ እያሣቃቸው ነወደ ጥግ ይንጫጫሉ። እነርሱም ራቱን በእጃቸው እየሸፈኑና እየኰረኰሩት ሲጫወቱ፣ እጃቸውን በአፉ ለመንከስ አስመስሎ፣ "አሀም... አሀም..." እያለ፣ ሲያስጮሃቸው የሌሎቹንም ቀልብ ሳቡ።

ሲስተር ዘቢባ ከባሻገር ካለው ጠረጴዛ ላይ የተዘጋጀውን ምግብ ቃኘት ቃኘት አድርጋ፣ ወደ ተሰበሰቡት እንግዶች መጣችና፣ "ኦልሬዲ በጣም መሽቷል ... ሳይርባችሁም አይቀርም ... በሉ እንግዲህ ተነሡና እየበላን እንጫወት። ከዛ በፊት ግን ይሄ ራት የተዘጋጀው አንድም እርስ በርስ በደንብ እንድንተዋወቅ ነው። በተለይ ሳናስበው ተጀምሮ እያደገ የመጣውን የጳውሎስ ክሊኒክ ቡድናችንን ለማጠናከር" ስትል፣ ሁሉም በደማቁ አጨበጨቡ። "ደግሞ በጣም የምንወደው ዶክተር ሌላው

Brought to You by t.me/bookshelf99

እም...ም ባለቤቱም ንጹሕዬና ልጆቻቸው፣ አገራቸውን ሊያገለግሉ መጥተው አሁን መሄጃቸው ስለደረሰ፣ እነሱንም አመስግነን ለመሸኘትም ነው።

"እኔ መቼም ስለ ዶክተር ሌላው ተናግሬም አልጨርስም ... ለሕመምተኞች ... ለተማሪዎችና ለስታፍ ሁሉ ያሳየኸውን ምላሌነትና ፍቅር፣ ምን ያህል እንደምናደንቅህና እንደምንወድህ እንድታውቅ እፈልጋለሁ። የኛ ምኞት እዚሁ ጠቅልላቸሁ እንድትመጡና እንድትኖሩልን ነው" ስትል፣ አሁንም ሁሉም እየጮሁ አጨበጨቡ። "በሉ እንግዲህ ከነንጹሕ እንጀምራለን ዶክተር አንተም ተነሥ ... እናንተ ጀምሩልን..." ብላ፣ አስነሥታቸው፣ ወደ እጅ መታጠቢያ ክፍሉ መራቻቸው።

ምግቡን እየበሉ የተለያዩ ወሬዎችን በተናጠልና በአንድነት ሲጫወቱ ቀዩ። ሌላው ከሲስተር ዘቢባ ልጅ ከሙኒራ ጋር የደመቀ ወሬ ይዟል። ንጹሕና ምስጢር ደግሞ አንድ ጥግ ይዘው ብዙ እንደሚተዋወቁ ወሬያቸውን ቀጥለዋል። ሲራክ ከመጣ ጀምሮ ከአቶ ሲራጅ ጋር የያዙትን ፖለቲካዊ ሙግት ቀጥለው ሞቅ ያለ ክርክር ውስጥ ገብተዋል።

ሲስተር ዘቢባ አንዴ አንዱ ጋ ደግሞ ሌላው ጋ እየሄደች ጨዋታ አድማቂ ጆክር ሆና፣ እንዲበሉ ባናት ባናቱ ምግቡን ትጨምራለች። የተዋጣለት ራት ነበር። ምግቡ ጋብ ብሎ ትኩስ ነገርና ጣፋጮች ሲቀርቡ፣ ሲስተር ዘቢባ እንደገና አጨበጨበችና፣ "እኔ ግን አንድ ጥያቄ አለኝ፣ በናንተም ዘንድ ተቀባይነት ካገኘ ... በሞብጨባ ትደግፉኛላችሁ" ስትል፣ የሁሉም ዓይኖች ወደሷ ተሰበሰቡ።

"በመካከላችን በጣም ጐበዝ ሙዚቀኛ እንዳለ ሰምተናል። እንደምታዩት የሙዚቃ መሣሪያው ደግሞ ተጫዋች እየጠበቀ ስንት ጊዜው። በርግጥ ካንድ በላይ ሙዚቀኞች እንዳሉ እናውቃለን። ግን ፒያኒስት ንጹሕ አንድ ሙዚቃ እንድትጫወትልን ለምን በሞብጨባ አንጋብዛትም" ስትል፣ ሁሉም እየጮሁ ሲያጨበጭቡ አፍሪ አገኘበሰች። ሲስተር ዘቢባ አጠገቧ መጥታ እጇን ይዛ ወደ ፒያኖው ስትወስዳት ሞብጨባው ቀጠለ። ቀስ እያለች ጀምራ እየደመቀ የሚሄድ ለስለስ ያለ ሙዚቃ ተጫውታ ስትጨርስ ሞብጨባው ቀለጠ።

ሙኒራ አጠገቧ ቀማ አጨዋወቷን እያየች ስታዳምጥ ቀየችና፣ "ወይኔ ታድለሽ ... እንደዚህ አሪፍ ሲጫወት ማንንም አይቼ አላውቅም። በጣም ጐበዝ ነሽ" አለችና አቀፈቻት።

ለእናቷ የቀረበውን ሞብጨባየሰማችው ትንሿ አርሴማእኔም ካልተጫወትኩ ብላ በትንንሽ ጣቶቿ አባቷ ያስተማራትን ሙዚቃ ባሞሩ ተጫወተች። ሁሉም በደማቁ ሲያጨበጭቡላት ሮጣ አባቷ ላይ ተጠመጠመች። "ጐበዝ የኔ ልጅ ... በጣም ጐበዝ" ብሎ፣ ግንባሯን ሳም ሲያደርጋት የበለጠ ፈነጠዘች።

ሲስተር ዘቢባም ብድግ አድርጋ ታቀፈቻትና፣ "የኔ ቀንጆ ማነው ያስተማረሽ?

Brought to You by t.me/bookshelf99

እም...ም ባለቤቱም ንጹሕዬና ልጆቻቸው፣ አገራቸውን ሲያገለግሉ መጥተው አሁን መሄጃቸው ስለደረሰ፣ እነሱንም አመስግነን ለመሸኘትም ነው።

"እኔ መቼም ስለ ዶክተር ሌላው ተናግሬም አልጨርስም ... ለሕመምተኞች ... ለተማሪዎችና ለስታፍ ሁሉ ያሳየኸውን ምሳሌነትና ፍቅር፣ ምን ያህል እንደምናደንቅህና እንደምንወድህ እንድታውቅ እፈልጋለሁ። የኛ ምኞት እዚሁ ጠቅልላቸሁ እንድትመጡና እንድትኖሩልን ነው" ስትል፣ አሁንም ሁሉም እየጮሁ አጨበጨቡ። "በሉ እንግዲህ ከነንጹሕ እንጀምራለን ዶክተር አንተም ተነሥ ... እናንተ ጀምሩልን..." ብላ፣ አስነሥታቸው፣ ወደ እጅ መታጠቢያ ክፍሉ መራቻቸው።

ምግቡን እየበሉ የተለያዩ ወሬዎችን በተናጠልና በአንድነት ሲጫወቱ ቆዩ። ሌላው ከሲስተር ዘቢባ ልጅ ከሙኒራ ጋር የደመቀ ወሬ ይዟል። ንጹሕና ምስጢር ደግሞ አንድ ጥግ ይዘው ብዙ እንደሚተዋወቁ ወሬያቸውን ቀጥለዋል። ሲራክ ከመጣ ጀምሮ ከአቶ ሲራጅ ጋር የያዙትን ፖለቲካዊ ሙግት ቀጥለው ሞቅ ያለ ክርክር ውስጥ ገብተዋል።

ሲስተር ዘቢባ አንዴ አንዱ ጋ ደግሞ ሌላው ጋ እየሄደች ጨዋታ አድማቂ ጆከር ሆና፣ እንዲበሉ ባናት ባናቱ ምግቡን ትጨምራለች። የተዋጣለት ራት ነበር። ምግቡ ጋብ ብሎ ትኩስ ነገርና ጣፋጮች ሲቀርቡ፣ ሲስተር ዘቢባ እንደገና አጨበጨበችና፣ "እኔ ግን አንድ ጥያቄ አለኝ፣ በናንተም ዘንድ ተቀባይነት ካገኘ ... በሞብጨባ ትደግፉኛላችሁ" ስትል፣ የሁሉም ዓይኖች ወደሷ ተሰበሰቡ።

"በመካከላችን በጣም ጐበዝ ሙዚቀኛ እንዳለ ሰምተናል። እንደምታዩት የሙዚቃ መሣሪያው ደግሞ ተጫዋች እየጠበቀ ስንት ጊዜው። በርግጥ ካንድ በላይ ሙዚቀኞች እንዳሉ እናውቃለን። ግን ፒያኒስት ንጹሕ አንድ ሙዚቃ እንድትጫወትልን ለምን በሞብጨባ አንጋብዛትም" ስትል፣ ሁሉም እየጮሁ ሲያጨበጭቡ አፍሪ አጐነበሰች። ሲስተር ዘቢባ አጠገቧ መጥታ እጇን ይዛ ወደ ፒያኖው ስትወስዳት ሞብጨባው ቀጠለ። ቀስ እያለች ጀምራ እየደመቀ የሚሄድ ለስለስ ያለ ሙዚቃ ተጫውታ ስትጨርስ ሞብጨባው ቀለጠ።

ሙኒራ አጠገቧ ቀማ አጨዋወቷን እያየች ስታዳምጥ ቀየችና፣ "ወይኔ ታድለሽ ... እንደዚህ አሪፍ ሲጫወት ማንንም አይቼ አላውቅም። በጣም ጐበዝ ነሽ" አለችና አቀፈቻት።

ለእናቷ የቀረበውን ሞብጨባ የሰማችው ትንሿ አርሴማ እኔም ካልተጫወትኩ ብላ በትንንሽ ጣቶቿ አባቷ ያስተማራትን ሙዚቃ ባሞሩ ተጫወተች። ሁሉም በደማቁ ሲያጨበጭቡላት ሮጣ አባቷ ላይ ተጠመጠመች። "ጐበዝ የኔ ልጅ ... በጣም ጐበዝ" ብሎ፣ ግንባሯን ሳም ሲያደርጋት የበለጠ ፈነጠዘች።

ሲስተር ዘቢባም ብድግ አድርጋ ታቀፈቻትና፣ "የኔ ቀንጆ ማነው ያስተማረሽ?

Brought to You by t.me/bookshelf99

በጣም ግሩም ሙዚቃ ነው" አለቻት ፣ በእንግሊዝኛ ።

"እባባና እማሚ" ብላ ፣ በደስታ እየተፍነከነከች ሲስተር ዘቢባን ግምጥ አድርጋ ሳመቻት ። አጸፋውን ስማ ስታወርዳት ሮጣ ወደ ሳንኦ ሄደች ። ከዛ ቡና እየተቀዳ ፣ ሁሉም ተሰብስበው የጋራ ወሬ ተጀመረ ።

"በጣም በጣም ግሩም ራት ነው ። መቼም ለማመስገን ቃል የለንም ..." ሲል ሌላሠው ፣ ሁሉም መስማማታቸውን በየራሳቸው ቃል አከታትለው ገለጹ ።

"ቤታችሁን በጣም ነው የወደድኩት ፣ ቃላት ከሚገልጸው በላይ ያምራል" ሲል ሲራክ ፣ አቶ ሲራጅ ቀበል አድርገ ፣

"ይኼ ሁሉ የዘቢባ ሥራ ነው ... ይሄው ሠላሳ አንድ ዓመታችን ከተጋባን ። ሁል ቀን እንዳስገረመችኝ ነው ። እዚህ ቤት ውስጥ የምታዩትም ሆነ ደጅ ያለው ሁሉ የሷ የእጅ ሥራ ነው ። ሆስፒታል ለሚያውቃት ነርስ ብቻ ትመስለዋለች ። እንደሷ ዓይነት ሁለ ገብ የሆነ ሰው እኔ በበኩሌ አይቼም አላውቅም ። አላህ እንዴት ቢወደኝ ነው እንደሷ ዓይነት ሚስት የሰጠኝ ብዬ ሁልጊዜ እደነቃለሁ" ሲል ፣ እንደ ማፈር ብላ ተሸኮረመመችና ፣

"አይ ሲራጅ አንተ መቼም በጣም ታበዛዋለህ ..." ስትል ፣ ምስጢር አጠገቧ ያለችውን ሲስተር ዘቢባን እቅፍ አደረገቻት ።

"ወይኔ ... በጣም ነው ደስ የምትሉት ። ለኔ ከሁሉም ይልቅ ከዚህ ሁሉ ዓመታት በኋላም እንደናንተ የሚዋደድና የሚከባበር ሰው መኖሩን ማየቱ ራሱ ካይምሮዬ በላይ ነው ። በ-ጣ-ም ነው ደስ የምትሉት ... በውነት ... ታድላችሁ" አለች ፣ ዓይኗ እምባ እያቀረረ ።

ሲስተርም በተራዋ እቅፍ አድርጋት ፣ "የኔ ቆንጆ ... ታንክ ዩ ..." አለች ።

ለጥቂት ጊዜ ሁሉም ነገር ጸጥ አለ ። ድንገት ከተፈጠረው ዝምታ በኋላ አቶ ሲራጅ ፣ "ቀይ እኔ ምለው ታዲያ ለምን አንድ ነገር አትጀምሩም አብራችሁ? ዶክተሮች አላችሁ ... ነርስ አለ ... ሳይኮሎጂስት ... ሶሻል ወርከር ... መድሃኒትና የህክምና መገልገያ አስመጭ ብትፈልጉ እኔ አለሁ ። ምን ያህል ሰው እኮ በናንተ ሙያ የሚረዳው አጥቶ እየተቸገረ እንዳለ ብታውቁ ። ግን ቢያንስ አስቡበት ። ይህን የመሰለ ወዳጅነት ወደ ሥራ ቢቀየርና የሆነ እናንተን ሰብስቦ አንድ ላይ የሚቋጥር ሐሳብ ቢገኝ ምን ዓይነት ትልቅ ሥራ መሥራት እንደምትችሉ ይታየኛል" አለ ።

ሁሌም ዕድሎች በቀላሉ የሚታየውና የቢዝነስ ራእዮችና ሐሳቦች የማያልቁበት ሰው ነው ። ከተወሰኑ አመታት በፊት በትንሽ የጀመረው የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያዎች አስመጪ ድርጅቱ ዛሬ በሚሊዮን የሚቆጠር ብር የሚያንቀሳቅስ ሆኗል ።

Brought to You by t.me/bookshelf99

"ጥሩ ሐሳብ ነው፣ ግን መጀመሪያ ዶክተር ሌላና ንጹሕዬ ... ምን ያስባሉ ነው ጥያቄው" አለች፣ ሲስተር ዘቢባ።

ሌላሠው ወደ ንጹሕ ዞር አለና፣ "ዋና አለቃዋ እሳቸው ናቸው እንግዲህ ..." ብሎ፣ እያያት ሲሥቅ፣

"ምን ወደኔ ትገፋለህ ... ራስህ ነህ እንጂ ..." አለች፣ ባይኗ ቄጣ ብላ።

"ሐሳቡ ጥሩ ነው። እስኪ ዛሬ ሐሳቡ ተወልዱል ... ትንሽ እንተኛበት" አለ፣ ነገሩን ለማርገብ የሚስቱን ዓይን አንብቦ። ነገሩን ይበልጥ እንዲያስቡበት የፈለገው አቶ ሲራጅ፣

"ካሜሪካ ጋር ሲነጻጸር በርግጥ እዚህ አገር ብዙ የማይመች ነገር ሊኖር ይችላል። ... ግን ደግሞ እናንተ እዚህ ብትሠሩ የምትፈጥሩት ልዩነት ቀላል አይመስለኝም። ትንሽ ከተሠራ ደግሞ ምንም ያልተሠራበት ሀገር ስለሆነ፣ እንደ ቢዝነስ ራሱ በጣም ትልቅ ዕድል ያለው ነገር ይመስለኛል" አለና፣ እጁ ላይ የቀረችውን ኩኪስ ጦረሰ።

በጉዳዩ ላይ ትንሽ ካወሩና ከተጨዋወቱ በኋላ ሲስተር ዘቢባ፣ "ታዲያ የመሄጃችሁ ቀን ተቁረጠ እንዴ?" አለች።

"እኔና ልጆቹ የዛሬ ሳምንት አካባቢ ነው ለመሄድ ያቀድነው። ሌላ ግን አንዳንድ መጨረስ ያለበት ነገር ስላለ ምናልባት አንድ ወር ለመጨመር እያሰበ ነው።"

"ውይ ብቻሽን ሁለት ልጆች ይዘሽ አይከብድም ያን ሁሉ መንገድ?" አለች ምስጢር፣ የታቀፈችውን ዲንሳን ግንባሩ ላይ ሳም እያደረገች።

ንጹሕም ትከሻዋን ሰበቅ አድርጋ ሌላ አማራጭ አለመኖሩን ለመግለጽ፣ "ምን ይደረግ እንግዲህ የልጆቹም ትምህርት ቤትና የኔም ሥራ ስላለ መሄዱ ግድ ነው" አለች።

በዚህ መሃል ልጆቹም እንቅልፋቸው እየመጣ ስለ ሄደ፣ ሌላሠው ሰዓቱ ሦስት ሰዓት ከሩብ መሆኑን አይቶ፣ "ሲስተርዬ እንሂድ መሰል ... ልጆቹም እንቅልፋቸው ሳይመጣ አልቀረም። እኛ ብዙ ብንቆይም ደስ ባለን ነበር" አለ፣ አርሴማን ከሳንቾ ላይ ተቀብሎ እየታቀፉት።

ከሙኒራ ጋር በሌላ ጊዜ በደንብ ሊገናኙ ተነጋግረው፣ እንድትደውልለት ስልኩን ሰጣት። ዲንሳም ምስጢር ላይ ተኝቶ ስለነበር እንደ ታቀፈችው እነ ሌላሠው መኪና ውስጥ አስገብታላቸው፣ ከንጹሕ ጋር ከተቻለ ከመሄዱ በፊት ሊገናኙ ተስማምተው ስልክ ተለዋወጡ።

ሲራክ ያለ ወትሮው ብዙም ሳያወራ ዝም ብሎ ነበር ያመሸው። ነገሩን ልብ

Brought to You by t.me/bookshelf99

ያለችው ሲስተር ዘቢባ ከሁሉም ቀድሞ ተሰናብቶ ሲወጣ፣ "ዶክተር ሲራክ፣ ምነው ዛሬ ድምፅህም አልተሰማም። እኔም ከሲራጅ ጋር ጨዋታ የያዛችሁ መስሎኝ ዝም አልኩህ። ለመሆኑ ራት በደንብ በላህ? ትንሽ አገልግል ነገር ልሰርልህ ባክህ?" አለች፣ ዓይን ዓይኑን እያየች።

"አዎ ሲስተርዬ፣ በደንብ ነው የበላሁት። ግሩም እራት ነበር። አገልግሉ ይቅርብኝ ግዴለሽም። ትንሽ ደክምክም ስላለኝ ነው እንጂ፣ በጣም ነው ኢንጆይ ያደርኩት። ከጋሽ ሲራጅም ጋር ብዙ ተጫወትን እኮ" አለ፣ ጃኬቱን እያስተካከለና የግዱን ፈገግ ለማለት እየሞከረ።

የምስጢር ከሳንቾ ጋር ባንዴ ይህን ያህል መቀራረብ ከንክኖታል። ሰላም ከለችው በኋላ ዞር ብላም እንኳን ስላላየችው፣ ነገሩን አውቃ እንደምታደርገው ነው የወሰደው። 'እኔን ለማስቀናት ሊሆን ይችላል' የሚል ሐሳብ ልቡን አውኮታል። 'ምኗ ነኝና ነው ልታስቀናኝ የምትሞክረው?' ብሎ ሐሳቡን መለስ ለማድረግ ቢሞክርም፣ ውስጡ የተፈጠረውን ቀዝቃዛ ንዴት፣ ስርጐ ከገባበት የልቡ ንቃቃት ውስጥ ጠራርጎ ሊያወጣው አልቻለም። በተለይ መኖሩን እንኳ ከቁም ነገርም የቆጠረችው ስላልመሰለው፣ ልቡ ከፊል በንዴት ከፊል በቅናት ሲጨስ ተሰማው።

Brought to You by t.me/bookshelf99

12

ሲራክ ከሲስተር ዘቢባ ቤት ከወጣ በኋላ፣ ከአያት ሰፈር እስከ ካዛንቺስ ድረስ ያለው መንገድ ባዶ ስለ ነበር ፍጥነቱን ጨምሮ ከነፉ። ከውስጡ ያለውን ጫጫታ ለማርገብ፣ መስኮቶቹን አውርዶ ሙዚቃውን ከፍ አድርጎ ለቀቀው። አልፎ አልፎ መሪውን በእጆቹ ይመታና፣ 'ሺት ... መምጣት አልነበረብህም ሲራክ ... ቀይ እኔ አይደለሁም ብቻ' ይልና ደግሞ ተመልሶ ከት ብሎ በራሱ ይሥቃል። ደግሞ እንደገና "እና፣ ምን እንድታደርግህ ፈልገህ ነው? ሲራክዬ የኔ ፍቅር ብላ ዓይን ዓይንህን እያየች አጠገብህ ትቀመጥልህ?' ይልና ራሱ ላይ እንዳጠፋ የቤት አሽከር ይጮህበታል።

መገናኛ አካባቢ ሲደርስ፣ ባዶ ቤት ገብቶ ከመደበር በዚያው ወደ ክለብ ሄዶ ሊያመሽ አሰበና መልሶ ተወው። ጎሊናን ወይንም ውዳሴን ደውሎ ካንዳቸው ጋር ለመቆየት አሰበ። ሰዓቱን ሲያይ የመሸ መሰለው። ሌላ ምንም ሐሳብ ስላልመጣለት ዝም ብሎ ወደ ቤቱ መንዳቱን ቀጠለ። ግቢ ሲደርስ መኪናውን አቆመና ከኋላ ወንበር ላይ ኮቱንና ቀን የጀመረውን ጋዜጣ ይዞ ወደ አፓርታማው አመራ። የሚኖርበት አፓርትመንት ከካዛንቺስ ወደ አራት ኪሎ መታጠፊያ ላይ ይገኛል። ጨለማና ጸጥታ እዋጠው ባዶ ቤት ሲገባ መጮህ አማረው። መብራቶቹን አበራርቶ ቲቪውን ከፈተና ሶፋው ላይ እንዘሞ ብሎ ተቀመጠ።

ቲቪውን በግማሽ ልቡ እያየ ማምሻውን ሁሉ ተዘግቶ የቀየውን ስልክ ከፈተው። ብዙ የጽሑፍ መልእክቶች ተግተልትለው ወጡ። አብዛኞቹ ከጎሊናና ከውዳሴ የተላኩ ናቸው። ጎሊና ደግ፣ የዋህና ለስላሳ ልጅ ናት። ሲራክ ከፍቅረኝነት ይልቅ ለሕይወቱ የማያውቀውን የእናት ፍቅር ይዛ የመጣችለት ተንከባካቢው ስለምትመስለው፣ እንድትርቀው አይፈልግም። ወደ ሁለት ዓመት ያህል አብረው ቢሆኑም፣ ጓደኝነታቸው ሲግል ሲቀዘቅዝ፣ አቅጣጫና መድረሻው ለሁለቱም እንቆቅልሽ ሆኗል። ሲራክ ሙሉ ተስፋዋን የጣለችበትና ሁለንተናዋን የሰጠችለት የመጀመሪያ ፍቅሯ ነው። ከእርሱ በቀር በዓለም ላይ ሌላ ወንድ ያለም

Brought to You by t.me/bookshelf99

አይመስላትም ።

ውዳሴ በታወቀ የሕግ አማካሪ ቢሮ ውስጥ ጠበቃ ሆና የምትሠራ በአንድ የሸኝት ፓርቲ ላይ የተዋወቃት ወጣት ናት ። ከጎሊና ጋር ተጋጭተው ለሦስት ወር በተከራረፉበት ወቅት ነበር ከውዳሴ ጋር ተቀራርበው ወዳጅ የሆኑት ። ከጎሊና ጋር መልሰው ከታረቁ ወዲህ ሁለቱን አቻችሎና አራርቆ መኖሩ ራሱ ከባድ ሥራ ሆኖበታል ።

በዚህ መሃል ምስጢር ጳውሎስ ሆስፒታል ለተግባር ሥልጠና መጥታ ካያት ወዲህ ደግሞ ልቡ ወደ እርሷ ሸፍቷል ። የምታሳየው ቸልታ የንቀት ስለሚመስለው እልህ ውስጥ ገብቷል ። ለብቻው ሲሆን ብዙ ያቅድ ይፎክርና አጠገቧ ሲደርስ ፣ ለምን ጌታውን እንዳየ ውሻ ሙራውን እንደሚቁላ አይገባውም ። ነገሩ የሚፈጥርበትን ብስጭት ለማርገብ ለራሱ የሚያቀርበው ምክንያት ፣ ለምስጢር ያለው ስሜት የእውነተኛ ፍቅር ምልክት ስለሆነ የርሱ እጣ ፋንታ እሷ መሆኗን ለራሱ እየተናዘዘ ውስጡን በተስፋ ይሞላል ።

ፒጃማውን ቀይሮ ከፍሪጁ ውስጥ ያላበው ቢራ አውጥቶ ሲጐነጭ ውስጡ ረገብ ያለለት መሰለው ። እዛው ሶፋ ላይ ጋደም እንዳለ ካጠገቡ ያለውን ጋዜጣ እንደነገሩ ማገላበጥ ጀመረ ። ዓይነ ሥጋው ጋዜጣው ላይ ያፍጥጥ እንጂ ልቦናው ግን አሁንም ጥቁር ቀሚስና ብሩህ ወሃ ሰማያዊ ጃኬት ለብሳ ከሳንቾ ጋር እየተፍለቀለቀች ስትሥቅ የነበረችውን ምስጢርን ደጋግሞ አመጣበት ። "ኡ ፍፍፍ ..." ብሎ ምስሏን ከፊቱ ለማስወገድ ይመስል ፊቱን በቀኝ እጁ ከላይ እስከ ታች ሞገለቀና በቅናት የተቃጠለ ጨጓራው ላይ ቀዝቃዛ ቢራውን ችለሰበት ። ጋዜጣውን ከፊቱ ወርወር አድርጎ ቲቪው ላይ ላይ አፍጥጦ ልቡ እዛና እዚህ ሲረግጥ ቀየ ።

ብዙም ሳይቆይ ስልኩ ጮኸ ። ጎሊና ነበረች ። ትንሽ አመንትቶ አነሣው ። "ሄይ ሂሉ ... አም ሶሪይ ... አንድ ስብሰባ ስለ ነበረኝ ስልኬን ዘግቼው ነበር ... የመሸ ስለ መሰልኝ ነገ ልደውልልሽ ነበርኮ ..." ብሎ ፣ ቀበጣጠረ ። በመደወሏ ውስጡ ደስ ብሎታል ።

"እንዴ እኔ ኮ በሜንቀት ልፈነዳ ነበር ። ትናንትም እኮ እደውላለሁ ብለህ ቴክስት አድርገህ በዛው ጠፋህ ... በደህና ነው? ዛሬ ደግሞ አክስቴ ጋእራት እንሄዳለን ተባብለን አልነበረም? ... ረሳኸው እንዴ?" አለች ፣ ናፍቆትና ሜንቀትን በሚያሳይ ድምፅ ።

"አህ ማይ ጋድ ... በናትሽ በጣም ይቅርታ ... ኮምፕሊትሊይ ነው የረሳሁት ። ሰሞኑን በቃ በጣም ቢዚ ሆኜ ቀልቤ ሁሉ ጠፍቷል ። በጣም ብዙ ነገር እየረሳሁ ተቸግሬያለሁ ። እሺ የት ነሽ አሁን?" አለ ፣ ትንሽ ጸጸት እየተሰማው ።

"እኔማ አሁን ካክስቴ ቤት ወጥቼ ወደ ቤት እየሄድኩ ፣ ካዛንቺስ አካባቢ ነኝ ። ድንገት ቤት ገብተህ ከሆነ ብዬ በዛው ላልፍ ነበር ። ሰላም ብለውሃል ደግሞ ...

Brought to You by t.me/bookshelf99

ያው በሥራ አሳብቤልሃለሁ ። መኪና ስላልያዝኩ ከሣራ ጋር ነኝ ። ትዝ ትልሃለች ከዝኔ ናት?"

"ኦህ ያ ... ደህና ናት?" አለ ፣ በትክክል ባያስታውሳትም ። "በቃ እከሳለሁ የኔ ፍቅር ... እዚህ አካባቢ ከሆንሽማ ጥሩ ነው ፤ ጐራ በይ ። እኔም ገና መግባቴ ነው ። እንዲያውም ወደ ቤትም ለምን እኔ አላደርስሽም?" አለ ፣ ድብርቱ ሁሉ ባንዴ እየጠፋ ።

"መጣሁበቃ ... አምስት ደቂቃም አይወስድብኝ" አለች ፣ እየተፍለቀለቀች ።

ጎሊና በአንድ ትልቅ የውጭ ድርጅት ውስጥ አካውንታት ናት ። ለወላጆቿ ብቸኛ ልጅ ናት ። ከሳሎን እስከ ኩሽና ያለው ዕቃ የተሟላው በጎሊና እገዛ ነው ። በሳምንት ቢያንስ አንድ ጊዜ እየመጣች ፍሪጁን ሞልታ ፣ ቤቱን መልክ መልክ አስይዛለት መሄድ ደስ ይላታል ። ሲራክ ደግነቷንና የዋህነቷን ቢወደውም 'ጥልቅ የሆነ ፍልስፍናና የሕይወት አተያይ የላትም ... አግብቶ ከመውለድ የዘለለ የሕይወት ዓላማ አይታያትም' ብሎ ስለሚያስብ ትንሽ አብረው ሲቆዩ ስልችት ይለዋል ። ለርሱ ደግሞ አግብቶ መውለድ እስራት እንጂ የሕይወት ጥሪ ወይም ትልቅ ተግባር መስሎ አይታየውም ።

ውዳሴ ይህንን ሁሉ ከሚያስበው በላይ የምታሟላ መስላ ትታየዋለች ። ተከራካሪ ፣ አንባቢ ፣ ማንኛውም ወቅታዊ የሆነ የዓለም ሁኔታ የማያመልጣትና ስለ ብዙ ነገር ከማንም ጋር ማውራት የምትችል ልጅ ናት ። ማሸነፍ በሐሳብ ብቻ ነው ብላ ስለምታምን ተከራክረው ሳይጣሉ የሚለያዩበት ጊዜ ጥቂት ነው ። ሁለቱም እልከኛና መበለጥ የማይወዱ ስለሆኑ አንድ ቤት ውስጥ ለመኖር እንደማይችሉ ልቡ ያውቀዋል ። ተፎካካሪ ጓደኛ እንጂ ተንከባካቢ ሚስት ልትሆነኝ አትችልም ብሎ ስለሚፈራ ሩቅ መንገድ አብረው ሲሄዱ አይታየውም ።

ጎሊና ደርሳ በሩን ሲከፍትላት ፊቷ ሁሉ ጥርስ በጥርስ ሆኖ የያዘችውን ዕቃ መሬቱ ላይ አስቀምጣ ተጠመጠመችበት ። እንቅ አድርጋ ላመችውና ፣ "አንተ ግን ጨካኝ ነህ ... ሰው ይናፍቀኛል እንኳን አትልም? ሲሩ ግን ልክ አይደለህም ..." አለችው ፣ እንደ ማኩረፍ ብላ ።

"ሂሉ ሙች ፣ ስለማላስብ እኮ አይደለም ። ያው ምን ታውቂው የለ ... እኛ ወንዶች ባንዴ ካንድ በላይ ነገር ማሰብም ማድረግም አልፈጠረብንም ። ሄይ ፣ ደግሞ ... ዩ ሉክ ጎርጂየስ ... ኧረ ኧረ ... በጣም ነው ያማረብሽ" ብሎ ፣ እንደገና እቅፍ አደረጋት ። "ደግሞ ይሄ ሁሉ የያዝሽው ጓዝ ምንድነው? ሣራ ሄደች እንዴ?" አለ ፣ በፈስታል ያለውን ዕቃ ከመሬት እያነሣ ።

"አዎ ... ይመሽብኛል ብላ ሄደች ። ሰላም ብላሃለች ። ድንገት እቤት ካገኘሁህ ብዬ ካክስቴ ቤት አገልግል አሳስርኩልህ ። ብታይ በጣም አሪፍ ድግስ ነበር ። ቀይ አምጣው ፍሪጁ ውስጥ ላድርግልህ ። ትንሽ ትቀምሳለህ?" አለችና ፣

Brought to You by t.me/bookshelf99

ጃኬትና ያንገት ልብሷን ሶፋው ላይ ጣል አድርጋ እንደ ልማዷ ፍሪጁንና ሳሎኑን ማስተካከል ጀመረች ።

"ውይ በቅርብ ነው ራት የበላሁት ሂሉ" አለና ፣ ወደጓዳ ገብቶ የሻይ ውኃ ጣደና ለራሱ ሌላ ቢራ ይዞ መጣ ። "ቢራ ለምን አትሞክሪም? ግሪን ቢራ ነው ... አንድ እኮ ምንም አይልሽም ... የሜክሲኮው ቅዱሱ ነው ። "

"ውይ ጀመረህ ደግሞ ... በናትህ ይበቃሃል አንተም ... ስንተኛህ ነው ግን?" አለች ። ብላው ብላው ልታስቀመው ሰላልቻለች ተስፋ ቈርጣለች ።

"ግና መግባቴ እኮ ነው ... በቃ በጣም ተቃጥዬ ስለነበር አንድ ለጥም ... ይችኛዋ ደግሞ ለጨዋታ ..." አለ ። ሶፋው ላይ ከአጠገቧ ቁጭ አለና ጉንጯ ላይ ሳም አደረጋት ። የሆነ ያልሆነውን እያወሩና እየተላፉ ትንሽ ቀዩ ። እጆቹን በወገቧ ዙሪያ አድርጎ ወደ እርሱ ስቦ ጠበቅ አድርጎ ሲስማት ፣ እርሷም እጆቿን በአንገቱ ዙሪያ ጠምጥማ አጸፋውን ሳትሰስት መለሰችለት ።

ትንፋሻቸው እየጋለ ሲሄድ ለስለስ ባለ ድምፅ ፣ "በናትሽ ካሁን በኋላ በጣም መሸቷል ... ለምን እዚሁ አታድሪም? ...ፕሊስ ..." አለ ፣ መልሱ ምን እንደሆን ቢያውቀውም ። ደረቱ ላይ ልጥፍ እንዳለች ጸጉሯን ደጋግሞ እየሳመ ።

ካንገቷ ቀና ብላ ዓይን ዓይኑን እያየች ፣ "አንተ...!" አለች ፣ እጇን በሸሚዙ ቁልፎች መሃል አስገብታ ደረቱ ላይ እያንሸራሸረችና ቀንጠጥ እያደረገችው ።

"ምና...ለበት? በቃ መሸ ጓደኞቼ ጋ ነኝ ምናምን በያቸው" አለና ፣ የአፍንጫዋን ጫፍ ከዛም ዓይኖቿን ሳም ሳም አደረጋቸው ። እንደ ምንም ከእቅፉ ውስጥ ወጥታ ብድግ አለች ። ጸጉሯን አስተካከለችና ሰዓቷን አየት አደረገች ።

"የምርህን ነው እንዴ አንተ ልጅ ... እንዲያውም በጣም መሸቷል አሁን ልሂድ ፣ በል ሽኝኝ" ብላ ፣ ቁልቁል ስታየው ዓይኖቹን እንደ ጨፈነ ዝም አለ ። ልብሷን አስተካከለችና ጃኬቷን ደርባ እንደገና አጠገቡ ቁጭ አለች ።

"አይ ፕሮሚስ ... ሰሞኑን በሰራው እንጫወታለን ... ዛሬ ግን መሄድ አለብኝ ። ደበረህ እንዴ?" አለች ፣ ትንሽ ጨነቅ እያላትና ፊቱን ወደ እርሷ ልታዞር እየሞከረች ።

"ዛት ኢዝ ፋይን ... ኢት ኢዝ ኦኬይ ... በቃ እንዳይመሽብሽ እንግዲያውስ ..." ብሎ ፣ ብድግ አለ ። የቀረችውን ቢራ ጨለጠና ጂንስና ቲሸርት ቀየረ ። የቀዳ ጃኬቱን ጣል አደረገና ሽቶውን ላመል ያህል ነስነስ አደረገ "እንንቀሣቀስ?" ሲላት ፣

"ለሽኝት ነው ለአዳር? ዘነጥክሳ?" ስትለው ፣

"የሚሆነው አይታወቅም ፣ የሚጠልፈን ከተገኘ ... የእኩለ ሌሊት ሲሳይ" አለና ሣቀ ።

Brought to You by t.me/bookshelf99

"ደረቅ ነገር እኮ ነህ ... ይሄን ሽቶ እንዴት እንደምወደው ... ውይ...ይ..." ብላ ፣ ደረቱ ላይ ልጥፍ አለች ። እሷን ቄራ አካባቢ ካለው የወላጆቿ ቤት ጥሎ ፣ ወሎ ሰፈር አካባቢ ሲደርስ ሰዓቱን ሲያይ አምስት ሰዓት ከሩብ ይላል ። ከመንገዱ ዳር ሰዎች ወጣ ገባ የሚሉበት ላውንጅ ባር አይቶ ፣ መኪናውን አቁሞ ገባ ። በሙዚቃና በመጠጥ የቀለጠው ቤት በደብዛዛ ተለዋዋጭ ባለ ቀለም ብርሃኖች ተሞልቶ ፣ ይምሽ ይንጋ አያስታውቅም ። አይኖቹን ጨፈን ከፈት አድርጎ ካንድ ጥግ አካባቢ ካገኘው ባዶ ወንበር ላይ ተቀመጠ ።

ያዘዘውን ቀዝቃዛ ቢራ ሁለት ጊዜ እንደተጐነጨ ፣ ከፊት ለፊቱ ካለው ጠረጴዛ ላይ ከተቀመጡ ልጆች መሃል አንዲት ወጣት ወዳለበት መጥታ ፣ "ከመተከዝ መደነስ አይሻልም ብለህ ነው?" ብላ ፣ ለዳንስ ስትጋብዘው ሳይግደረደር ተነሳ ። የለበሰችው ጥቁር ቀሚስና ሰማያዊ ጃኬት መሆኑን ያስተዋለው ተመልሰው ሲቀመጡ ነበር ።

"ህም ... ይገርማል" ሲል

"ምኑ...?" አለችው ፈጠን ብላ ።

"አለባበስሽ በጣም ያምራል" ሲላት ፣

"አንተ ግን ከቤት ፎርፈህ የወጣህ የሃይ ስኩል ተማሪ ነው የምትመስለው?" ስትለው ፣ ሜንቅላቱን ወዘወዘና ፣

"እንዴት አወቅሽ?" አላት ሳቅ ብሎ ።

"ልብስህ ... ቢራ አጠጣጥህ ... አደናነስህ ... ጨቅጨቁ ነገር ትመስላለህ" ብላ ፣ በሹፈት አይነት ሳቀችበት ።

"አንቺ! በጣም ... ደፋር ቢጤ ነሽ" ብሎ ፣ ቢራውን ወደ እርሷ እያስጠጋ ፣ "እሺ የተከበሩ መምህርት ... ተማሪዎችዎ ከኮሌጅ የተመረቁ ሥልጡን ከተሜ እንዲመስሉ ፣ የቢራ አጠጣጥ ያስተምሯቸው" አለ ፣ ድምጹን እንደ ራድዮ ትምህርት አድርጐ ። ቢራውን ወደሱ መልሳ ገፋችው ። ከኪሱ ውስጥ ሲጋራ አውጥቶ ሊለኩስ መለኮሻውን ሲፈልግ ፣ እንደገና ከት ብላ ስትስቅ ፣ ምነው በሚል አይነት የሲጋራውን ፓኮ እንደ ያዘ ቀና ብሎ አያት ።

"ቀይ ..." ብላ ፣ ከቦርሳዋ ውስጥ ፓኮ ሲጋራ አወጣችና "ይሄንን ሞክረው ..." ብላ ሰጠችውና የያዘውን ኒያላ ተቀብላ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠችው ። ጠጋ አድርጎ ሲያነበው 'ፊሊፕ ሞሪስ' ይላል ። ሳቅ ብሎ ከውስጡ አንዲት ሲጋራ አወጣና መለኮሻ ፍለጋ ኪሱ ውስጥ ሲገባ ፣ እሳቱን ከፊቱ ገጭ አደረገችለት ።

"ታንክ ዩ ... ምን ... ለነርሱ ነው የምትሰሪው? ይሄም ኒኮቲን ያም ኒኮቲን ... ምንድነው ልዩነቱ?" አላት ። የለኮሰውን ሲጋራ ፊቷ ላይ አቦነነውና የሲጋራውን ፓኮ መለሰላት ።

Brought to You by t.me/bookshelf99

"አይ ሊጠፉ የተቃረቡ የዱር አራዊቶቻችንን ከምታጨስ ብዬ ነው" ብላ፣ ሞሱን በእጁ ከፊቷ ላይ አራገበች ፈዛዛ ፈገግታ እያሳየችው።

"ሆ ሆ ... ምን ልጋብዝሽ?" አለ፣ እሱም ፈገግ ብሎ። ነገረ ሥራዋ ደስ ብሎታል።

"እኔንጃ ... ለጊዜው ቶኒክ ነገር ..." ስትለው፣ የባስ ግራ ገባችው። ከትንፋሿ መጠጣቷን አውቋል። ትንሽ እንዳወሩ ካጠገባቸው የነበሩ ብዙ ጐረምሶች መካከል ብጥብጥ ተነስቶ ጫጫታው በዛ።

"ቦታ ብንቀይርስ?" ሲላት ትከሻዋን ሰበቅ አድርጋ፣

"ደስ እንዳለህ ... ያው አውቀሃል ... አይደል?" አለችው ፈገግ ብላ።

"ያ ያ ..." ብሎ፣ ተያይዘው ወጡ። ጎልፍ ቮልስዋገን መኪናው ውስጥ ገብተው ፍጥነቱን ጨምሮ እየነዳ፣ " እሺ ... ታዲያስ ... ሥራ እንዴት ነው?" አላት፣ ዞር ብሎ በጨረፍታ አየት እያደረጋት። ለመኪናው ያስገጠመላት ሰፊ ሞስ ማውጫ የሚፈጥረው ነጮድጓዳማ ድምፅና አካባቢውን ሁሉ በነሜ የብርሃን ጸዳል የሚሞላ መብራቷ በውስጡ ጥንካሬና ጉልበትን ይሰጠዋል።

"ሥራ ምን ይሆናል ብለህ ነው ... ሠሪ ካልደከመውና አሰሪው ካልደኸየ በቀር" ብላ፣ ፈገግ አለች። "ይቅርታ ... ቅድም የሃይ ስኩል ተማሪ ትመስላለህ ስላልኩህ" ስትለው፣ ዣቅ አለና፣

"ተገኝቶ ነው" ሲላት፣ እሷም ሳቀች።

"መኪናህን በጣም ነው የወደድኳት"

"እኔንስ?" አለ፣ ሙዚቃውን እየቀየረው።

"ገና ፀባይህ ታይቶ ነዋ ... አት ሊስት ... በጣም አሪፍ ኮሎኝ ነው የተቀባኸው" ስትለው፣ ዞር ብሎ አያትና ፈገግ አለ።

"ግን ለሆነ ሚሽን የተጣደፍክ ትመስላለህ" አለች፣ ሞልቀቅ ባለ ድምፅ።

"ምን ሚሽን አለ ብለሽ ነው ... ሽሽት ነው። የምሬን ነው ... አለባበስሽ ምርጥ ነው ... ተመችቶኛል" ብሎ፣ በእጁ ሞኗን መታ አደረገና፣ "ትንሽ ክለብ መቀየት እፈልጋለሁ ... ራት ነገር መብላት ትፈልጊያለሽ?" አለ፣ ፍጥነቱን ቀነስ እያደረገ።

"በቅርብ ነው የቀማምስኩት ... አሁን ምንም አላሰኘኝም። ታንክ ዩ ግን" አለችው። ቦታ መረጡና የሙዚቃ ማጫወቻውን ድምጹ-ደላቂ 'ሳብዉፈር' እስከ መጨረሻ ለቅቀት በባዶው አስፋልት ላይ በረሩ።

Brought to You by t.me/bookshelf99

"ሲራክ እባላለሁ ... ያንቺስ?" አላት፣ ከሙዚቃው ጋራ ባንገቱ ለመደነስ እየሞከረ።

እሷም ከሙዚቃው ምት ጋር ጭንቅላቷን እያወዛወዘች፣ "ሉሲ" ስትለው፣ ፊቱን ወደሷ አዞረ።

"ካም'ኦን ... ባልጠፋ ስም የስንት ሚልዮን ዓመት አሮጊት ዐፅም ምን ያደርግልሻል? ... ሌላ ሞክሪ ... አንቺን የመሰለች ቀንጂት ሉሲ ልትሆን አትችልም" ሲላት ከሙዚቃው ጋር የበለጠ እየተወዛወዘች፣

"እ-ና-ቴ-ን- ሉሲ ነው" አለች፣ ግድም ሳይሰጣት ድምጿን እየጎተተች።

"ወይ ጉ--ድ ... ሌላ ሞክሪ ስልሽ ... አለበለዚያ ... እኔ ሻል ያለ ስም ላወጣልሽ ነው። ሉሲ ብሎ ስም አፍ ላይም ይቀፋል። በናትሽ ... ሙዚየም ያለሁ መሰለኝ" ሲል ሣቋን ለቀቀችው።

"እስኪ ሞክር ..."

"በቃ 'ሚስጥር' ብዬሻለሁ መብቱ ከተሰጠኝ ... 'ሚስጥር' እንዴት ነው?"

"ይደብራል" ስትለው ያልጠበቀው ስለ ነበር ዞር ብሎ፣

"ለምን?" አላት በመገረም እያያት።

" ሚስጥር አልወድም ..."

"ኡሁሁ ...ሁ፣ እኔ ግን ሳይሽ ... ስምሽም፣ ኑሮሽም፣ ሁለመናሽ ሚስጥር ነው የሚመስለው። ሰው የሆነውን የሚጠላ ... ላልሆነው የሚንጠራራ አስቸጋሪ እንስሳ ነው ይላሉ ሳይንስ ያልተማሩ የባህል ምሁራን ..." አለ፣ ሙዚቃውን ቀነስ እያደረገ።

"ጆማሪ ሳይኮሎጂስት ነገር ነህ መሰለኝ። እስኪ መርምረኝ በናትህ" ስትለው በውስጡ 'ይቺን ይወዳል ሲራክ' አለና ከት ብሎ ሣቀ።

"ለምርመራውም ለምኑም እኮ መጀመሪያ በስሙ ላይ መስማማት ያስፈልጋል። ወይ ሚስጥር ሁኚ ወይ ደግሞ ... ሚስጥራዊ ስምሽን ንገሪኝ ... ሉሲ ግን አትበይኝ ... ዘፈን ነገር ይመስለኛል ... የሆነ የማንም ነጫጭባ ስካራም አርክዮሎጂስት ያወጣው ስም ..." ብሎ፣ ለራሱም ያልገባውን ነገር ቀበጣጠረ።

"እሺ ደስ ይበልህ ... 'ሚስጥር' ሆኜልሃለሁ ለጊዜው ... አንተስ ሲራክ የሌሊት ስምህ ነው?" አለች፣ በውስጧ 'ይቺ ጩጬ የዋዛ አይደለችም ... ወይ የመጽሐፍ መሸገር ናት ወይ የምር የገባት ሳትሆን አትቀርም' ብላ እያሰበች።

"ሲራክ ... የዘወትር ስሜ ነው ... እኔ ቀንና ሌሊት አልቀያየርም ... ሲራክ ሁሌም ሲራክ ነው" ሲላት፣ ቀጭን ሣቋን ለቀቀችው።

Brought to You by t.me/bookshelf99

"አቤት አቤት ... አልተሰማም ... ይሄኔ ...ገረመው ... ወርቅነህ ... ወይ ድጋፌ ምናምን ይሆናል እውነተኛው ስምህ። ሲያዩህ ምንም ሲራክ አትመስልም" ስትለው፣ የመንጃ ፈቃዱን አውጥቶ ሰጣት። ገርሟት አየት አደረገችውና ተቀበለችው።

"ዶክተር ሲራክ ... አይ ላ-ይ-ክ ኢት ... ዶክተር ለመሆን ጨዉ ነገር ትመስላለህ። የምን ዶክተር ነህ ግን? ... በናትህ የከብት እንዳትለኝ። ወይስ ይዘህ የምትዞረው?" ብላ ስትሥቅበት፣ መንጃ ፈቃዱን ተቀበላትና ትከሻዋ ላይ ላመል ያህል በካርዱ መታ አደረጋትና ኪሱ ውስጥ መለሰው።

"ብራቮ ሚስጥር እንዴት አወቅሽ?" ብሎ በፉጨት ከመዘቃው ጋር ለማዜም ሞክሮ ሲያቅተው፣ "ዱክትርናውስ የራሴ ነው። ከጠዋት እስከ ማታ በሁለት እግር የሚሄዱ ከብቶች ሳክም ነው የምውለው።"

"ዶሮ ስታባርር ነዋ የምትውለው። የዶሮም ሐኪም እንዳለ አላውቅም ነበር። የምር የዶሮ ዶክተር ነህ?"

"ብሆን ይሻለኝ ነበር ... የሾን ሰው ከማከም እነሱን ማከም ላይሻል አይቀርም። ከብዙ ሰው እኮ ዶሮቹ ይሻላሉ። ሰው ማለት ታክሞ የማይድን በሽታውን በመደበቅ የተካነ ሥልጡን ከብት ነው። ሁለት እግር ያለው ከብት ደግሞ ዶሮ ብቻ አይደለም።"

"ዶክተር ፍልስፍናም ይሞክራሉ ማለት ነው? እኔ እንኳን ለቀልድ ነበር ... ሁሉንም ነገር አታምርር እንጂ። ግን የምር የምን ዶክተር ነህ?"

ከክለቡ ፊት ለፊት ማቆሚያ እየፈለገ፣ "የሰው ... የሰው ሜንቅላት ... እንዳንቺ ነካ ያደረጋቸውን ሰዎች ሳይ ነው የምውለው" አለና፣ መኪናውን አቀመ። "ስለዚህ ሚስጥር በሚለው ተስማማን?" አለ፣ ለመውረድ በሩን እየከፈተ፣

"ይሁንልህ ... እና፣ የእብድ ሐኪም ነኝ ነው የምትለኝ? እኔ ግን እናንተም ጤነኛ አትመስሉኝም። አክስቴ ለብዙ ጊዜ አማኑኤል ተኝታ ነበር።" ያደረገችው ረጅም ታክ ያለው ጫማ እንዳያደናቅፋት ከንዱን ይዛው ወደ ውስጥ ገቡ። ከአንድ ጥግ አካባቢ ቁጭ ብለው የሚጠጡትን አዘው ትንሽ በነገር ሲቀራቀሱ ቀዩ። ከዛም መጠጡን በላይ በላዩ አየጨመሩ፣ ሲጨፍሩ ቀይተው ወደ ዘጠኝ ሰዓት ላይ እየተወለካከፉ ተደጋግፈው ወጡ። መኪናውን እንዴት ነድቶ እቤት እንደ ደረሱና ከዛ በኋላ ያደረጉት ሁሉ ትዝ አይለውም።

ጠዋት ላይ ሜንቅላት የሚከፍል ራስ ምታት ሲቀሰቅሰው አዲዕ 'ምስጢር' ጉኑ አልነበረችም። ደንገጥ አለና እዕ በተኛችበት አቅጣጫ ሲያይ ጥቁሩ ቀሚዕና ሰማያዊ ጃኬቷ ወንበሩ ላይ ተዝረክርኮ ተበትኗል። ሌላኛዋ የሆስፒታዕ ምስጢር ትዝ ስትለው ፊቱን በሁለት እጹ ሸፍኖ፣

Brought to You by t.me/bookshelf99

"ኡፍፍፍ ... ወደዛ... ሲረሲት አታውቅም እንዴ ይቺ? ምን በጠዋቱ ትነጅሰኛለች" አለ ጮክ ብሎ ፣ እዛው በጀርባው እንደ ተኛ ጣራ ጣራውን እያየ ። እጁ ላይ ያለውን ሰዓት ሲያየው አንድ ተኩል ይላል ። ከመታጠቢያ ቤት የሚወርደውን የውሃ ድምፅ ሲሰማ 'ይቺ ደግሞ ምን በሌሊት ያንቀዠቅዣታል?' አለና ገልበጥ ብሎ ፊቱን ትራሱ ውስጥ ቀብሮ ራስ ምታቱ እንዲሄድለት እየተመኘ በደረቱ ለጥ አለ ። ትንሽ ቀየት ብሎ ድንገት ጀርባው ላይ ቀዝቃዛ እጅ ሲያርፍበት ደነገጠ ።

"ኡፍፍፍ ... እስኪ ግንባሬ ላይ በፊጠረሽ ... ራስ ምታቱ ሊገድለኝ እኮ ነው" አለ ፣ ዓይኖቹን እያጨናበሰ በፍጣ ተጠቅልላ ከፊል ርቃኗን ያለችውን ልጅ እያየ ። በሁለት እጁ ግንባሩን ከዛም ፊቱን ስትይዝለት "ኡፍ ደስ ሲል ... አንቺ ግን ምን ብረቷ ነሽ ... አይደክምሽም ... ምንም ራስ ምታት ምናምን የለም?"

"ሥራችን ነው ለምደነዋል ... ይሄ ለኔ ገነት ነው ። ስንት ዓይነት ሰው እንደሚያጋጥመን እኮ አንተ አታውቅም ። አንዳንዱ ትውከታም ... ካልተደባደብኩ የሚለው ብትል ፣ ስንት ዝተታም የወንድ አውሬ አለ መሰለህ ። የፈለገውን አድርገ እንደ ቀሻሻ ዕቃ ዞር ብሎ የማያይህ ... የገዛህ የሚመስለው ... ባለ ትዳሮቹማ በቃ የሰው ምራቄ ... ቅል ሜንቅላቶች ናቸው ... ኧረ ስንቱ" አለች ፣ ግንባሩን በቀስታ እያሻሸችለት ። ማታ ካያትም የበለጠ ቆንጆ ሆና ታየችው ። መከራ በጠገበ ፊቷ ላይ የሐዘን ድባብ ይነበባል ። ስትሥቅ ደግሞ ፊቷ ላይ የተከመረው ሐዘን እንደ ምትሐት ብን ብሎ ይጠፋል ። "አሁን ሽሮ ፍትፍት ነገር በበረዶ ፣ ቋ ካለ ቀንጆ አቦል ቡና ጋር ብታገኝ እኮ ... አ-ዲ-ዎ-ስ ራስ ምታት ነበር" ስትለው ፣ ማታ ጎሊና ያመጣችለት ምግብ ትዝ አለውና ግንባሯ ላይ ሳም አድርጓት ፍንጥር ብሎ ተነሣ ። ያገኘውን ልብስ ጠለቅ ጠለቅ አድርጎ ፣

"ሳይሻል አይቀርም ... እስኪ ምን እንዳለ እንይ" አለና ወደ ፍሪጁ ተንደረደረ ። ተከትላው ወደ ኩሽና ገባች ። ዱቄቱን በዛ አድርጎ ቡናውን ጣደና የምግቡን ሣሕን ከፍሪጅ አውጥቶ ሲከፍተው ግድግዳውን ደገፍ ብላ በዝምታ ስታየው ቀይታ ፣

"ማናት ልጄ እንደዚህ ከሽና አገልግል የምትቋጥርልህ?" አለችው ፣ በሹፈት ዓይነት ወደ እርሱ ጠጋ እያለች ።

"ምን ባክሽ ማታ ያክስቴ ልጅ ናት ይዛልኝ የመጣችው ። ቤታቸው ድግስ ነበር ... መሄድ ስላልቻልኩ ልከውልኝ እግረ መንገዷን ጥላልኝ አለፈች" አለ ። ለምን መዋሸት እንዳስፈለገው አስቦ በራሱ ተናደደ ።

"ያክስት ልጅ አያሳጣህ ። ብዙ ያክስት ልጆች አሉህ?"

የጎሪጥ አየት አደረጋትና ፣ "እሺ ከገርል ፍሬንዶቼ አንዱ ናት ... ስሟ ትዝ አይለኝም ። ሰው መዋሸት አይችልም ማለት ነው በቃ?" አለ ፣ ትከሻውን ከንፈቱ በላይ ከፍ አድርጎ ።

Brought to You by t.me/bookshelf99

"እንደሱ ይሻላል ። የሷን ፍትፍት ለኔ ቁርስ እንደ ጋበዝከኝ ትነግራታለህ ወይስ ... ከነ ዶክተር ምንትሴ ጋር በላነው ... እንዴት ይጣፍጣል ነው የምትላት?"

"የሆነ ደረቅ ነገር ነሽ ግን ... እስኪ ወሬውን ተይና ቡናውን ቅጂልን ... የሴት ወጉን ሞክሪ ... በጠዋት የተፈረካከሰ ሜንቅላቴን አትነርቺው በናትሽ ..."

"አይ ወንዶች ..." ብላ ፣ በጨበጠችው እጁ እንደ ቀልድ ጀርባውን ደለቅ አደረገችው ። ስኒው የት እንዳለ ጠይቃው ወተት አሙቃ ቡናውን ቀዳችና ቀዝቃዛ ፍትፍቱ ላይ ዘመቱበት ።

"ለምን ግን ሚስጥር አልከኝ?" አለች ፣ ረሃቡ ጋብ ሲልላቸው ቡናውን ፉት እያለች ፣

"በቃ ... ሚስጥር ሚስጥር ስለምትሽቺ ... ሚስጥር ነገር ስለመሰልሽኝ ... ለምን ይመስልሻል አንቺ?" አለ ፣ እውነቱን ልንገራት አልንገራት ብሎ እያመነታ ።

"ያው ወንዶች እኮ ያው ናችሁ ... ምን የተለየ ነገር አላችሁ ... ወይ ሚስጥር የምትባል በጣም የምትወዳት ጓደኛህ ጫር ብላሃለች ... ወይ ደግሞ በፍቅሯ የምትንገበገብላት ሚስጥር ተብዬ ሚስጥራዊ ልጅ ትኖራለች ። እሷን ካላገኘህ ... ሞደፊክ ነገር ፈልገህ ... የራስህን ሚስጥር ፈጥረህ ... ከሸሌ ጋር ማደር ነዋ ። ማታ በስካር ነፍስህ ጠፍቶ እሷ መስዬህ ነው መሰል 'ሚስጥርዬ ... ማሬ ወተቴ ... ቅብጥርጥርሴ ... አንድ ዕድል ስጪኝ ... እኔ ኮ ነፍሴ እስኪወጣ ነው የምወድሽ' ምናምን እያልክ የሆነ ያልሆነ ነገር ስትዘበዝብ ነበር" ብላ ፣ በትዝብት ዓይነት እያሾፈች ስታየው ፣ እንደ ማፈር ብሎ ለራሱ ያዘጋጀውን ፍትፍት አጐረሳትና ቡናውን ፉት አለ ።

"ልክ ነኝ? "

"ልክ ሁኚም አትሁኚም ... እኔ ማታ ስወጣ አንቺን የመሰለች ልጅ አገኛለሁ ብዬ አላሰብኩም ። የኔን ተይው አንቺ ግን ለምን ..." ብሎ ፣ የጀመረውን ዐረፍተ ነገር ሳይጨርስ ፣

"እኔ ምን ዓይነት ልጅ ነኝ?" ብላ ፣ አቋረጠችውና እጁ ውስጥ የገባውን እንቁላል ገምሳ አጎረሰችው ። " ገብቶኛል ... ለምን ወደዚህ ህይወት ገባሽ ... መውጣት አትፈልጊም ወይ ... ብ-ላ-ብ-ላ ... ለማለት ከሆነ ብዙ ጊዜ የሰማሁት ፣ የሰለቸኝና የሚያስጠላኝ ዘፈን ነው ። እሱንም እንዝለለው" አለችው ፣ የቀረውን እንቁላል የመሃሉን አውጥታ ነጩን ትንሽ ትንሹን በጥርሷ ሸራርፋ እየበላች ።

"አኬይ ፣ ኦኬይ ... እሺ ... ግን ቢያንስ እውነተኛ ስምሽን ማወቅ እችላለሁ?" አለ ፣ ይቅር በሚል አይነት ሁለት እጆቹን እያነሳ ።

"ምን ለውጥ አለው? ... እውነተኛ ስሜ እውነት ሊወራ በማይችልበት ሁኔታ ትርጉም አይኖረውም ። በለጡ ... አልማዝ ... ሰብለ ወንጌል ... ብልህ ምን

Brought to You by t.me/bookshelf99

ይጠቅምሃል። ለጊዜው አንተ የሰጠኸኝ ተስማምቶኛል ... ሚ-ስ-ጥ-ር ሆኜ ልቀይ"

የበሉበትን ካነሣሡ በኋላ፣ ሁለተኛ ቡና ቀድቶ ቲቪውን ከፈተና ሶፋው ላይ ቁጭ አለ። እሷ ደግሞ ወደ መኝታ ቤት ገብታ ልብሷን ለባብሳ መጣች። አዲሷ 'ሚስጢር' ተሰናብታው ከወጣች በኋላ በመስኮቱ በኩል ቀሞ ግቢውን ለቃ እስክትወጣ ባይኑ ሸኛት። ስልክ ቁጥር አለመለዋወጣቸው ትዝ ሲለው ትንሽ ቆጨው። እዛው እንደቆመ ከውዳሴ ጋር ጠዋት አራት ሰዓት ላይ ያለውን ቀጠሮ አስታወሰና 'ኡፍፍፍ ምን ጣጣ ነው ባካቹ ... ማረፍ አልተቻለም እኮ" ብሎ ትንሽ ለመተኛት ወደ መኝታ ቤቱ ተመለሰ። ከራስጌው ኮመዲኖ ላይ ስልኩን ብድግ ሲያደርገው ከሥሩ የታጠፈ ብጣሽ ወረቀትና የተጠቀለለ ገንዘብ አገኘና ደንግጥ ብሎ ወረቀቱን ከፈተው

"በጣም አመሰግናለሁ ትንሹ ዶክተር። ጨዋና ደግ ሰው ትመስላለህ። ፍትፍቱና ቡናው ይበቃኛል፣ ገንዘቡ ይቅር። እውነተኛ ስሜን ማወቅ ከፈለግህ ደውል 0912 ... ኤስ ኤስ"

ይላል። የጅ ጽሑፏም እንዳነጋገሯ ሞልቀቅ ያለ ሲሆን ጥርት ባለ እንግሊዘኛ ነው የጻፈችው። "አሞበርባሪ ...እንኳን ሌላ ልንጨምር ... ያሉትንም መቀነስ አቅቶናል" አለ። አንድ ሲጋራ አውጥቶ ለኩሰና በተረፈችው የክብሪት እሳት ወረቀቷን አቃጠላት። የቀረችውን የክብሪት እንጨት ይዞ ሲጋራውን እያቦለለ ፈገግ አለ። አልጋው ላይ በጀርባው እንደ ተንጋለለ ጣራ ጣራውን እያየ፣ ከውስጡ ጋር ሲናጀስ ብዙ ደቂቃዎች እንደ ዋዛ ወደ ኋላ ፈሰሱ።

Brought to You by t.me/bookshelf99

13

ሌላው ሰኞ ቀኑን ሙሉ ባለቤቱ ንጹሕ ወደ አሜሪካ ይዛ የምትሄዳቸውን ዕቃዎች ሲገዙ ዋሉ። ማታ ላይ ደግሞ እናቱ የመሸኛ እራት አዘጋጅተው ስለነበር ቀኑ ሳይታወቅ አለቀ። አንድ ወር ከነርሱ ተለይቶ መቅረቱን መቀበል አቅቷት ከብዙ ክርክር በኋላ ነው በመቆየቱ የተስማማችው። ማክሰኞ በጠዋት ከቤት ወጥቶ እንደ ልማዱ ትንሽ ለማሰብና ለማኪያቶ ካልዲስ ሄዶ ቁጭ አለ። የሲስተር ዘቢባ ባል አቶ ሲራጅ ያነጣው የክሊኒክ ሐሳብ ከአእምሮው ሊጠፋ አልቻለም። ንጹሕ የማትስማማበት ሐሳብ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ለክሊኒክ የሚሆን ሁነኛ ቦታ ማግኘትና የፈቃድ ማውጣት ሂደቱ ተራራ መስሎ ታየውና ነገሩን ከጭንቅላቱ ለማውጣት ሞከረ።

ጳውሎስ እንደ ደረሰ የሐኪሞች የጠዋት ስብሰባ ስላልነበረ በቀጥታ ወደ ክሊኒኩ ገባ። ከርሱ ቢሮ ፊት ለፊት ካለው የነርሶች ቢሮ ሲደርስ፣ ሲስተር ዘቢባ ከምስጢርና ከእናቷ ጋር የደራ ወሬ ይዘው ደረሰ። ጨዋታቸውን ገታ አድርገው፣ ሲስተር ዘቢባ የርሱን አለባበስ በማድነቅ የጀመረችው ወሬ መንደርደሪያ ሆኖ መሣሣቅ ጀመሩ። ወዲያው ሳንቾም ሲቀላቀላቸው ጨዋታው የበለጠ ደመቀ። በሳምንት ሁለት ቀን ጠዋት ለሶሻል ወርክ ዲግሪ የልምምድ ስራ ለማድረግ ጳውሎስ መምጣት ከጀመረ ወር አለፈው።

"ዛሬ ትንሽ በጊዜ መውጣት ሳይኖርብኝ አይቀርም፣ ሲስተርዬ። የንጹሕ ጉዞ እሑድ ስለሆነ አንዳንድ የማግዛት ነገር አለኝ" አለ።

"አይ ምንም አይደል ... ዛሬ በቂ ሬዚደንት ዶክተሮች ስላሉን እነሱ ያዩዋቸዋል። ዶክተር ሲራክም እኮ በዚህ ወር እዚህ ነኝ ሲል ነበር። ለካ ከነገ ወዲያ ነው ወሩ የሚጀምረው የኔ ነገር ..." ስትል፣

"ጥሩ ... እንግዲያው እኔና ወይዘሮ ኤደን መጀመር እንችላለን ... በሩ

Brought to You by t.me/bookshelf99

ተከፍቶ ይሆን እንዴ?" አለ፣ አንዴ ወደ ሲስተር ዘቢባ፣ አንዴ ወደ ወይዘሮ ኤደን እያየ ።

"የምንረዳህ ነገር ካለ ... ለጉዞ የሚገዙ ዕቃዎች መገዛዛት ምናምን አለች፣ ቁልፎቿን ከኪሷ ውስጥ እየፈላለገች ።

"ኧረ ምንም ... ብዙም እኮ አይደለም ... ያው ከዚህ ሲኬድ አለ አይደል አንዳንድ ለወዳጅ ቤተሰብ ምናምን የሚሆን ስጦታ" አለ፣ ነገሩን ቀለል እያደረገ።

"ግን፣ ኤኒ ታይም ንገረን ... ቆይ ልክፈትልህ በሩን" አለችና፣ ብዙ ቁልፎች ያነገተውን የቁልፍ መያዣ እያቅጨለጨለች ተነሣች ። ተከታትለዋት ወይዘሮ ኤደንና ዶክተር ሌላሙ ሲወጡ ምስጢር ከኋላው ነካ አድርጋው፣

"ዶክተር ሌላ ... አንድ ጊዜ" ስትለው፣

"እ...ሺ" ብሎ ወደርሷ ዞረ ።

"ማሚና እኔ አንድ ልናወራህ የምንፈልገው ጉዳይ ነበር ። ከማሚ ጋር አንድ ግማሽ ሰዓት ካወራችሁ በኋላ ጆይን ላደርጋችሁ እችላለሁ?" አለች፣ እጁን እያፍተለተለች ።

"ሹ--ር ... ወደ ሦስት ተኩል ላይ ግቢያ ... ምን በሰላም ነው?" አለ፣ ፈገግ ብሎ እጁን ኪሱ ውስጥ እንደከተተ ።

"ኧረ በጣም ሰላም ነው ...በጣም በሰላም ነው... በቃ አልያዝህ" ብላ፣ ተመልሳ ከሳንቾ ጋር ወሬ ጀመረች ።

ወይዘሮ ኤደን ፍክት ያለ ባለ ጎብረ ቀለም ቀሚሳቸውና የያዙት ቀይ ቦርሳ ደስተኛ አስመስሏቸዋል ። ጸጉራቸውን ቀይ ቡኒ ቀለም ተቀብተውት ከባለ ታክ ቀይ ጫማቸው ጋር የበለጠ አድምቋቸዋል ። ተጫኗቸው የኖረው ድብርት እየተነሣና የጭንቀታቸው መጠን እየረገበ በመጣ ቁጥር የሰብእናቸው መልክ እየተመለሰ ነው ። ተከታትለው ሲገቡ፣ ባዶ ወና ያደረውን ክፍል የተቀቡት ሽቶ ናኘበት ። ያደሩና የተራረፉ ካርዶችን አንድ ላይ አስተካክሎ ከጮን ወዳለው ጠረጴዛ ላይ እያስቀመጠ፣

"እንዴት ከረሙ ታዲያ? በጣም አምሮብዎታል" አለ፣ ከልብ የሆነ ፈገግታ እያሳያቸው ።

"አመሰግናለሁ ... አመሰግናለሁ ዶክተርዬ" አሉ፣ እጅ እንደ መንሳት ብለው ።

"መጀመሪያ ሳይዎት ከነበረው ብዙ ለውጥ ያለ ይመስለኛል ... ለእርስዎ እንዴት ነው?" አለ፣ ሁኔታቸውን እያጠና ።

Brought to You by t.me/bookshelf99

"ውይ ዶክተርዬ እሱማ ምን ቃል አለው? የቀንና የማታ ያህል ነው ለውጡማ ... ቢያንስ እንቅልፌ ደህና መሆኑ ራሱ አይበቃም እንዴ? ደግሞ ወጣ ወጣ ማለትም ጀምሬያለሁ እኮ። እላዬ ላይ እንደ ክምር የተጫነብኝ ጨለማ እኮ ነው ብድግ ያለልኝ። አንተን ላከልኝ እሱ ... መቼም አያልቅበት" አሉ፣ ዓይን ዓይኑን እያዩ። ላይ ድቅን ማለታቸውስ?"

"በጣም ቀንሷል።"

"እም...ም ... በጣም ጥሩ ነው፣ ከፍ ያለ ድምፅ ሲሰሙ ተደናግጦ የመደንበሩ ነገርስ ትንሽ ቀነሰ?" አለ፣ ካርዳቸውን ወደ ፊትና ወደኋላ እያገላበጠ።

"እ...ሱ ሙሉ ለሙሉ አልጠፋም ... ግን እንደ ፊቱ ማልቀስ የለም ... ለብቻዬም ጭብጥ ብዬ ጨለማ ክፍል አልቀመጥም። ምግብም ቢሆን በጣም ተሻሽያለሁ ... ትንሽ ኪሎስ ሳልጨምር ቀረሁ ብለህ ነው" አሉ፣ ሰውነታቸውን አየት እያደረጉ።

"በጣም ጥሩ ነው። መድኃኒቶቹስ ... ምንም ችግር አልፈጠሩብዎም?" ሲል፣ ቀበል አድርገው፣

"እኔ ድሮም ኪኒን ምናምን ብዙም አልወድ ለነገሩ። ግን ከጤና የሚበልጥ የለም። በርግጥ ትንሽ ማድከሙ አለ ... አሁን ግን ሰውነቴም ለመደው መሰል ብዙም አይረብሸኝ። ትንሽ ችግር የሆነብኝ ድንገት ሳላስበው ልቤ ትር ትር ትልና ካልወጣሁ ብላ ደረቴን እንዳንድ ነገር ቀስፎ ይይዘኛል። ከዛ ከላይ ከላይ እያስተነፈሰ ላብ በላብ ዘፍቆ የሚያፍነኝ ነገር ነው ... መላው የጠፋብኝ። በቃ እኮ ሰማይና ምድሩ ላዬ ላይ ሊደፋብኝ የደረሰ ነው የሚመስለኝ" አሉ፣ ነገሩን በትክክል ለመግለጽ እየተቸገሩ።

"የዚያ አይነት ስሜትን የሚፈጥረው፣ ባብዛኛው ፓኒክ የምንለው የጭንቀት ስሜት ሊሆን ይችላል። እርስዎ ግን ስኳር ሕመምም ስላለብዎ የስኳሩ መጠንም ዝቅ ሲልም የዛ ዓይነት ስሜት ሊፈጠር ይችላል። ስለዚህ እሱንም ማሰብና መጠንቀቅ አይርሱ። ቶሎ ቶሎ መተንፈሱ ደግሞ ደምዎ ውስጥ ያለውን የኦክሲጅንና ካርቦን ዳይኦክሳይድ መጠን ስለሚያዛባው ነው ሌሎቹ ምልክቶችም የሚታዩት።

"ይቺ ስስ ፌስታል አለች አይደል? ... ልክ ሲጀምርዎ ትንፋሽዎን ያዝ አድርገው ቀስ እያሉ ... በረጅሙ ... ፊስታሏ ውስጥ ... ወደ ውስጥና ወደ ውጪ መተንፈስ በጣም ይረዳል። እስኪ ይሞክሩትና ይንገሩኝ። ሲተነፍሱ አፍና አፍንጫዎን ሙሉ ለሙሉ ፌስታሉ ውስጥ አድርገው፣ የሚተንፍሱት አየር ከላስቲኩ ውስጥ ሳይወጣ ላንድ ደቂቃ እሱኑ ወደ ውጪና ወደ ውስጥ እየተነፈሱ ይሞክሩት። ልክ እንደዚህ ..." ብሎ፣ አተነፋፈሱን ሲያሳያቸው እንደ ተረዱት ጭንቅላታቸውን በመወዝወዝ አስረገጡ። "እሱ ካልሠራ ግን የመድኃኒቱን መጠን ላስተካክልልዎ እችላለሁ" አለና፣ ጥቂት እያሰበ ዝም አለ።

Brought to You by t.me/bookshelf99

"በቃ ዶክተር ... መሄጃህ ደረሰ ማለት ነው?" አሉ ፣ እዝን ባለ ድምፅ ።

"አዎን ፣ እንግዲህ ኑሮ አስቸጋሪ ነው ... ቤተሰቤም እዛው ስለሆነ ። ቀየት ብዬ ደግሞ ብቅ እል ይሆናል" አለ ፣ ለሚቀጥለው ወር የሚሆን መድኃኒት ማዘጋጀ እየጻፈላቸው ።

"አዎ ... እሱስ ልክ ነው ... ግን ለኛ እዚህ ብትሆንልን በማለት ነው እንጂ ... ሰው መቼም ራስ ወዳድ ነውና ። ሚሚዬም ስትነግረኝ ነበር ... ስለ ሚስትህና ስለ ልጆችህ መቼም አውርታም አትጠግብ ። በቀደም ለእራት ተገናኝታችሁ ነበር መሰል ሲስተር ቤት" ሲሉ ፣ በሩ ከውጪ ተንኳኳ ።

"ይግቡ..." አለ ፣ ሌላው ፊቱን ወደ በሩ ዞር አድርጎ ።

"ይቅርታ ፣ አሁን መግባት ይቻላል?" አለች ፣ ምስጢር አንገቷን አስገብታ ።

"ኦ-ህ ... ያ ...ያ ... ግቢ ግቢ ..." አለ ፣ ወንበሩ ላይ ወደ ኋላ ደገፍ ብሎ ። ገብታ ከእናቷ አጠገብ ተቀመጠችና ዓይን ዓይናቸውን እያየች ፣

"እንዴት ነው ... ፒስ ነው ማሚዬ ..." ስትል ፣

"ሁሉ ጥሩ ..." አሉ ፣ ግንባሯ ላይ የተበታተነውን ጸጉሯን በጃቸው እያስተካከሉላት ።

ከጥቂት ዝምታ በኋላ ፣ "ይቅርታ አቋረጥኳችሁ እንዴ?" ብላ ፣ ግራና ቀኝ ሁለቱንም አየት አደረገች ።

"አይ ጨርሰናል ...እንዲያው ዶክተርና ቤተሰቡ ስለ መሄዳቸው አንስተን ... ስናወራ ነው የመጣሽው" አሉ ።

ቀበል አድርጋ ፣ "ዶክተር ሌላ ... ትንሽ ልናዋራህ የፈለግነው ዋነኛው ምክንያት ለናቴ ስላደረክላት ሁሉ አብረን ልናመሰግንህ ነው ። ምናልባት መጀመሪያ ልታይህ ስትመጣና በዛሬው መካከል ያለውን ለውጥ አንተም ታየዋለህ ። ሌላው ደግሞ እኔንም አብሬህ ሆኜ ለፕራክቲከሜ የሚያስፈልገኝን ልምምድ እንዳገኝ ስለ ፈቀድክልኝ ለሱም ለማመስገን ነው ። በቅርብ ባለቤትህና ልጆችህ እንደሚሄዱና አንተም ጥቂት ጊዜ ነው የቀረህ ስላት ነው እናቴ እንዲያው በቅጡ እንኳ ሳናመሰግነው ..." ብላ ፣ እናቷን አየት አደረገቻቸው ።

"ልክ ነው ዶክተር ... እንዳንተ ዓይነት ሩኅሩኅና ሰውን ሁሉ በኩል ዓይን የሚያይ ... ደግሞም የሚሠራውን የሚያውቅ ብዙ ሰው ቢኖር ይሄ ሕዝብ እዝሎ የሚዞረውን መከራ ገና ድሮ በጣለ ነበር ። በውነት መድኃኒዓለም እሱ የሥራህን ፍሬ እንደሚሰጥህ አውቃለሁ ... አሁንም ሰጥቶሃል ። ግን በቃ እንድታውቀው ነው ... መቼም እኛ አገር ሰው ካልሄደና ካልሞተ አይመሰገንም አይደል?" አሉ ።

"እሺ ... እኔም በጣም አመሰግናለሁ ... ደግሞም እናንተን ማወቅና ከናንተም

Brought to You by t.me/bookshelf99

ጋር መሥራት ለኔ ትልቅ ደስታ ነው ። ከሁሉም በላይ ደግሞ እርስዎ ተሸሎዎት ማየቱ ነው የኔ ትልቁ ፍሬ ..." አለና ሌላ ምን ማለት እንዳለበት ስላላወቀ ዝም አለ ፣ የያዘውን እስክሪብቶ ካንድ እጁ ወደ ሌላው እያሸጋገረ ።

"ሌላው ግን በቀደም የሲስተር ባል ያነሣው ሐሳብ ትዝ ይልሃል? ስለ ክሊኒክ ምናምን ..." ስትል ፣ በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ ። "እና ፣ ነገሩን ከማሚ ጋር እቤት ስናወራ አንድ ሐሳብ መጣልን ። ማለቴ ሐሳብ ነው ፤ ግን ለማንኛውም አንተም ንጹሕም ከመሄዳችሁ በፊት ብንነግርህ ማን ያውቃል ብለን ነው ። " ብላ ትንሽ ዝም አለች ። ወደ እናቷ አየት አደረገችና ፣ "ሌላው አንድ አባቴ በውርስ ያገኘነው ትልቅ ግቢ ያለው ቪላ አለ ። እሚልህ ግቢው ብቻ ከሦስት ሺህ ካሬ ሜትር በላይ ነው ። በብዛት ጫካና ዛፍ ነው ። አከራይተነው የሆኑ ፈረንጆች ናቸው የሚኖሩበት ። ወደ ፈረንሳይ አካባቢ ሲሆን ፣ በጣም ጸጥ ያለ ሰፈር ነው ። የአእምሮ ሕክምና ማዕከል ቢሆን ብዙ ሥራ ሊሠራበት ይችላል ብለን አሰብን ። ምናልባት አንተም ሐሳቡ ጥሩ ከመሰለህ ..." ብላ የሚለውን ስትጠብቅ ፣ እናቷ ቀበል አድርገው ፣

"እኔ መቼም ከዚህም ለተሻለ ቅዱስ ተግባር ያ ቦታ ይውላል ብዬ አላስብም ። ደግሞ ካንተም የተሻለ ሰው ሊሰራበት ይችላል ብዬ አላምንም ። ሰዎቹም በዚህ ወር ስለሚለቁት ቦታውም ክፍት ይሆናል ። ግን ያው ሰው ይመኝ የለ ... እንዲያው ይሄ የኛ ምኞት ነው..." ብለው ፣ እሳቸውም ዝም አሉ ።

ከጥቂት ዝምታ በኋላ ፣ "በጣም ጥሩ ሐሳብ ነው ... የኔም አንዱ ሕልሜ ፣ ብዙ ሰው ሊረዳና ሊማር የሚችልበትን የሕክምና ማዕከል መክፈት ነው ። ቦታው ደግሞ ለዚህ የተመቸ ይመስላል ። እስኪ ስለ ጉዳዩ ከንጹሕ ጋር ልመካከር ፣ እኔም የበለጠ ላስብበት" አለ ። ውስጡ ደስ ቢለውም ፣ ብዙ ሊታዩና ሊታሰቡባቸው የሚገቡ ነገሮች መኖራቸውን አሰበ ።

"እርግጠኛ ነኝ ዶክተር ሌላ ... ቦታውን ስታየው ዋ--ው ፣ ነው የምትለው ። አንተም ንጹሕም እስከምታዩት አይ ካንት ዌይት ... እነ አርሴማ እንኳን ሳይቀሩ ነው አሜሪካ አንሄድም የሚሉት..." ብላ ፣ ስትሥቅ እናቷና ሌላሠውም አብረዋት ሣቁ ።

እነርሱ ከሄዱ በኋላ ሲጠብቁት የነበሩትን ጥቂት ሌሎች ሕመምተኞች አይቶ ሲወጣ ፣ በቀጥታ ፖስታ ቤት አካባቢ ሄዶ ንጹሕ እንዲገዛ የነገረችውን የስጦታ ዕቃዎች ገዛዝቶ ወደ ቤት አመራ ። ቤት እንደ ደረሰ የነበራቸው የምሳ ቀጠሮ ስለደረሰ ወዲያው ተያይዘው ወጡ ። ወደ አሜሪካ ከመመለሳቸው በፊት ልጆቹን ይዘው ወደ አዋሳ ለመውጣት ቢያስቡም ባለቀ ሰዓት እንዳይታመሙባቸው ስለፈሩ ሐሳባቸውን ቀይረው ሁለቱ ለብቻቸው ለመውጣት ነው ያቀዱት ። እነ ምስጢር የነገሩትን የክሊኒክ ጉዳይም እዛው ሊያነሣባት አቅዷል ። ንጹሕ ዝናሽን ለመጠየቅ ብታስብም ፣ ቀኑ ሳያስቡት አለቀ ። ጠዋት ከከተማ ከመውጣታቸው በፊት እግረ መንገዳቸውን አይተዋት ሊያልፉ ወሰኑ ።

Brought to You by t.me/bookshelf99

ጠዋት ላይ ልጆቹ ከእንቅልፍ ሳይነሱ ቀደም ብለው ከቤት ወጡ። የንጹሕን በልጆቿ ጉዳይ መጨነቅ ያወቁት የሌላሠው እናት፣ "ንጹሕ ወርቅዬ ... ካጠገቤ አይለዩም። ያክስታቸው ልጆችም እዚሁ ስለሚሆኑ ምንም አላብ አይግባሽ አትጨነቂ። ደግሞ ስትደርሱ ደዉሉ" አሉ፣ ከግቢ ሲወጡ። ሆስፒታል እንደደረሱ መኪናቸውን ግቢ ውስጥ አቁመው ወደ ሴቶቹ መኝታ ቤት እየሄዱ፣

"እኔ ምልህ ሌላዬ ... ስንት ሰዓት ይወስድብናል ከእዚህ ሀዋሳ?"

"ኧረ ኮርተን እንደርሳለን፣ ቢበዛ አራት ሰዓት ቢፈጅብን ነው። ይሄን ሆስፒታልም ስራ ተጀምሮ ግርግር ሳይበዛ አይተናት መውጣት ይኖርብናል። የማይገባ ነገር እየለፈለፈች በምትሥቅ ታማሚ አጠገብ ሲያልፉ፣ ንጹሕ በፍርሃ ክንዱን ጨምድዳ ያዘችው።

ወደ ሴቶች ክፍል ሲደርሱ ኃላፊ ነርሷን በር ላይ አገኟት። ከንጹሕ ጋር ካስተዋወቃቸው በኋላ አብረው ወደ ዝናሽ መኝታ እካባቢ ሄዱ። አልጋዋ ግራና ላይ ተቀምጣ ከሞኗ ካለችው ሕመምተኛ ጋር ስታወራ ደረሱ። ስታያቸው ብድግ አለች።

"ታዲያስ ዝናሽ ... እንዴ ነፍሰ ጡር እኮ አይነሣም፣ ቁጭ በይ ... ቁጭ በይ፣ እንዴት ከረምሽ?" አላት፣ ፈገግ ብሎ።

"በጣም ደህና ... ጥሩ ነው ..." አለች፣ አንገቷን እየደፋች።

"እሷ ባለቤቴ ናት ... ሁል ጊዜ ነው ስላንቺ የምትጠይቀኝ ..." ብሎ፣ ወደ ባለቤቱ ዞር አለና ፈገግ አለ።

ንጹሕ ልትጨብጣት እጇን ስትዘረጋላት ልስልስ ባለ ድምፅ፣ "አመሰግናለሁ" አለችና ጨበጠቻት።

"ይህችን ደግሞ ለመቀየሪያና ስትወልጂ ላንቺና ለልጅሽ እንድትሆንሽ" ብላ፣ የተጠቀለለ ነገር ሰጠቻት።

እፍረትና ፈገግታ በተሞላ ፊት፣ "ኧረ ይሄ ሁሉ ምን ያደርጋል ... ደክማችሁ እኮ። በጣም ነው የማመሰግነው" ብላ፣ አልጋው ላይ አስቀመጠችው። ትንሽ ዝምታ ከሰፈነ በኋላ ድንገት ፊቷ ብርት ብሎ፣ "ቀይ ላሳያችሁ ... ሲስተር እሱ ልጆቼን አስገብታልኝ እሑድ መጥተው ነበር" አለችና፣ ከትራሷ ሥር የሁለት ልጆቿን ፎቶ አውጥታ ለሌላሠው ሰጠችው። ወደ ኃላፊ ነርሷ ጠጋ ብላ እጇን እየያዘች "ሲስተርዬ ... በጣም ነው ውለታሽ ለኔ ... እሷ እመቤቴ ትስጥሽ ..." አለች ከራስጌዋ በላይ ወደ ተሰቀለው የማርያም ምስል ዞር ብላ።

ኃላፊ ነርሷም የዝናሽ ትክሻ ላይ እጇን ጣል አድርጋ፣ "ውይ ዶክተርዬ እንዴት እኮ የሚያማምሩ ማር የሆኑ ልጆች መስሉህ ..." አለች።

Brought to You by t.me/bookshelf99

"በጣም ቀንጅዬ ልጆች ናቸው ያሉሽ..." አለ፣ ፎቶውን ለንጹሕ እያቀበላት።

"እዎን ... ትልቁ እኮ አባቱን ቁጭ ነው፣ ምን ያደርጋል ብር ብቻ ... ደደብ አረብ ሆነ እንጂ ..." አለች፣ ፊቷ ልውጥውጥ ብሎ።

"አይዞሽ ዝናሽዬ፣ ዋናው ጤና ይሁኑልሽ ... አንቺ ደህና ከሆንሽ ሁሉም ይደርሳል ..." አለቻት፣ ኃላፊ ነርሷ ትከሻዋን እያባባሰች።

"ትንሿ ስንት ዓመቷ ነው?" አለች፣ ንጹሕም ወደ ዝናሽ እያየች።

"አራት ዓመት ሆናት መሰለኝ። ውይ ብታዩ እንዴት ዓይነት ሚጥሚጣ ሆናለች መሰለሽ ..." አለችና፣ ከንጹሕ የተቀበለችውን ፎቶ ሁለት ጊዜ ሳም ሳም አድርጋ ወደ ልቧ አስጠግታ ያዘችው።

ትንሽ አውርተዋት ከነርሷ ጋር ተከታትለው ሲወጡ፣ እንባ ባቀረሩ አይኖቿ ተከተለቻቸው። ሌሎቹንም ሕመምተኞች በጅምላው ሰላም እያሉ ሲወጡ፣ አንዳንዶቹ እየመጡ ለጥ ብለው እጅ እየነሡ ሰላም አሉት። ንጹሕም ፈራ ተባ እያለች እየጨበጠቻቸው ከክፍሉ ወጥተው ወደ ቢሮ ሲገቡ ነፍሷ ትንሽ መለስ አለችላት። ኃላፊ ነርሷን አመስግነው በዛው ጉዟቸውን ወደ ሐዋሳ ጀመሩ። ያየችው ነገር ስሜቷን የነካው ንጹሕ ለረጅም ደቂቃ ዝም ብላ ቀየች።

"ሌላዬ ... በየቀኑ እዚህ ውስጥ ነው የምትሠሩት? በጣም ነው እኮ የሚያሳዝኑት። እናንተ ግን እንዴት አትፈሩም? ሲስተርን እንዴት እንዳደነቅኋት። አቤት የሰው ሕይወት ፈተናው ብዛቱ ..." አለች፣ ሞንቅ ባለው ፊት።

"ይሄ እንዲያውም ያን ያህል ከባድ አይደለም ... አንዳንዴ ራስሽን ነው የሚያዞርሽ። እዚህ አገር በሚከፈላቸው ደሞዝና የሥራ ሁኔታ ይኼንን ሥራ የሚሰሩትን በተለይ ነርሶቹን በጣም ነው የማደንቃቸውና የማከብራቸው። አስቢው መመታት ሊኖር ይችላል ... መሰደብማ ተይው። በዛ ላይ አብዛኛው በጣም ደሃና ቤተሰቡም ምርር ብሎ የተወው ስለሆነ ሕመማቸውን ብቻ ሳይሆን ሥቃያቸውንና ተስፋ ቢስነታቸውንም ችለው ነው የሚሠሩት ..." ብሎ፣ መሪውን የያዘባቸውን ጣቶቹን ጠበቅ ላላ እያደረገ በረጅሙ ተነፈሰ። የትራፊክ ሞንቅንቁን እስኪ ወጡ ድረስ ጥቂት ዝም ብለው ነዱ።

"በናትህ የዝናሽ ልጆች እንዴት ያምራሉ ... የድሃ ልጅም አይመስሉ። የኔ እናት፣ ደግሞ አሁን ሌላ ልጅ ሊመጣ ነው። አባቷ በልመና ነው የሚተዳደሩት ነው ያልከኝ?"

"አዎን ... በዚያ ላይ ድክም ያሉ አዛውንት ናቸው። ምን ታደርጊዋለሽ እንግዲህ ... ስንት ሰው አለ መሰለሽ እንደሳቸው።"

Brought to You by t.me/bookshelf99

"ቀይ ግን አሁን የሷ ህመም ወደ ልጆቿ አይተላለፍም? ላይክ ... እንደ ስኳር ... ደም ግፊት፣ ማለቴ ነው።"

"እ ...ም የአእምሮ ሕመም ላይ ስትመጪ ነገሩ ትንሽ ውስብስብ ያለ ነው። ባጠቃላይ ከሌላው ሰው ይልቅ የበለጠ በሕመሙ የመያዝ ዕድሉ ሊኖራቸው ይችላል ... ግን ያን ያህል ላይሆን ይችላል። በተለይ ብዙ ጫና የሌለው ኑሮ ከኖሩና ከሱስ ምናምን ከራቁ ዕድሉ የጠበበ ነው።"

"እሷስ አሁን ከተሻላት በኋላ የመዳን ተስፋ አላት? ወይስ በቃ እንዲ ከታመምክ ምንም ተስፋ የለውም?"

"ባጠቃላይ ሁሉም ሰው ላይ የመዳን ዕድሉና ደረጃው አንድ አይደለም። ጥናቶች የሚያሳዩት አንድ ሦስተኛ አካባቢ የሚሆኑት ባይታከሙ እንኳ በጊዜ ብዛት ተሽሏቸው ደህና ሊሆኑ ይችላሉ። ሌላው አንድ ሦስተኛ ግድሙ ደግሞ በመታከም ብቻ ነው ሊረዱና ሊሻላቸው የሚችለው። የቀረው ግን መታከሙ ለራሳቸውም ለቤተሰብም ያለውን ጫና ከመቀነስ አንጻር ጥቅም ቢኖረው እንጂ፣ ብዙ እገዛ የሚያስፈልጋቸው የዕድሜ ልክ ሕመምተኛ መሆናቸውን አይቀይረውም። አንዳንድ ጠቋሚ ነገሮች ቢኖሩም ... ችግሩ ባጠቃላይ የትኛው ሰው በየቱ ምድብ ውስጥ ሊሆን እንደሚችል በትክክል ማወቅ አይቻልም" አለና፣ በረጅሙ ተነፈሰ።

በወሬው ተመስጦ ከመቶ ኪሎሜትር በሰዓት በላይ እየፈጠነ ስለነበር፣ "ቀስ ሌላዬ ... አውሮፕላን አደረከው እኮ ..." አለች፣ እጁን በጁ ላመል ያህል ያዝ አድርጋ። ከዚያም ቀጠል አድርጋ፣ "የሷስ እንዴት ይመስልሃል?" ስትለው፣ በየመንገዱ ዳር ቀመው ለሰላምታ እጃቸውን የሚያውለበልቡላቸውን ልጆች እጁን አውጥቶ ሰላም እያለ፣

"ደጋግማ ሆስፒታል መግባቷና ህመሙም ብዙ ስለቀየባት ምናልባት ዕድሜ ልኳን መድኃኒት መውሰድ ይኖርባታል። ግን አሁን በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ያሳየችው ከፍተኛ ለውጥና ሌሎችም ሁኔታዎች የሚጠቁሙት መድሃኒቷን በትክክል ከወሰደች ጤነኛ ኑሮ ለመኖር ጥሩ እድል እንዳላት ነው። ሴትነቷ፣ ስሜቷን የመግለጥ ችሎታዋ ሙሉ ለሙሉ አለመጥፋቱ፣ ከመታመሟ በፊት የነበራት ጥሩ የሰብእና ሁኔታ ሁሉ ተደማምሮ ጥሩ ተስፋ እንዳላት ነው የሚያሳየው" አለና፣ ከአጠገቡ ያለውን የላስቲክ ውሃ እንድትከፍትለት አቀበላት።

በዚህ መሃል በዛ ያሉ አስፋልቱን በቀስታ የሚያቋርጡ ከብቶች መንገዱን ስለዘጉት መኪናውን በረድ አድርጎ ቆመ። የከፈተችውን ውሃ ለራሷ ጎንጨት ብላ ስትሰጠው ተቀብሎ ግማሹን ባንድ ትንፋሽ አንደቀደቀውና "ኡፎይይይይ ... እንዴ በጥ ያቂ አድርቀሽኝ እኮ ... ማይ ጋድ ... ልትገድይኝ ..." ብሎ ሲሥቅ፣

"ዝም በል ... ሞዛዛ ... አሁን አንተ በእንቅልፍ ልብህስ ቢሆን ውሃ ካገኘህ ... ማን ይመልስሃል ..." ብላ እሷም ሣቀች።

Brought to You by t.me/bookshelf99

የውኃ ጠርሙሱን ተቀብላው እንደገና ጐንጨት ብላ አስቀመጠችውና፣ "ቆይ ደግሞ ሌላ ትዝ ያለኝ ... እዛ ወደ መውጫው ጥግ አካባቢ የነበረችው ዓይኗን አጉረጥርጣ ስትጮህና ስትሳደብ ... ዕቃ ስትወረውር የነበረችውስ? ... አሁን እሷምም ይሻላታል? ቆይ ግን ... ሰይጣን ይሁን የአእምሮ በሽታ መሆኑንስ እንዴት ነው የምታውቁት? ወይስ በእናንተ ሳይንስ ሰይጣን ምናምን የለም፣ ሁሉም በሽታ ነው ብላችሁ ነው የምታምኑት? ምክንያቱም አይ አም ሹር ቤተሰብ ቢሆን ጠበል ወይም ጸሎት ነበር የሚወስዷት፣ ወይም እስካሁንም ወስደዋታል ርግጠኛ ነኝ።"

በዚህ ደረጃ ተመስጣና ፍላጎት አድሮባት ስለ ሥራውም ሆነ በአእምሮ ሕመሞች ዙሪያ ጠይቃው ስለማታውቅ መገረምም ደስታም ተሰማው። "በቃ ኮ የአእምሮ ሐኪም መሆንሽ ነው። ምን ቀረሽ?" ብሎ፣ በስሱ ፈገግ ብሎ በጐን አየት አደረጋትና፣ "የትኛዋን እንዳልሽ ገብቶኛል። የሚገርምሽ ነገር ዝናሽን መጀመሪያ ከጻውሎስ ወደ አግኑኤል ሳመጣት ትዝ ይልሻል እንኳን አገትሽ ቤት ምሳ ግብግ የነበረ ጊዜ። አሁን ካልሻት ሴት በብዙ እጥፍ የባሰች ነበረች። እንዳንዷ በሚገርምሽ ፍጥነትና ሁኔታ ሊሻላቸው ይችላል። ደግሞ የፈለግሽውን ብታደርጊም ብዙም ለውጥ ላያሳዩ ይችላሉ።

"ሰይጣን ላልሽኝ ግን ... በጣም አከራካሪ የሆኑ ብዙ ነገሮች አሉ። በመጀመሪያ መንፈሳዊ ዓለም አለ ወይ? ሰውስ መንፈሳዊ ፍጥረት ነው ወይ? ሰይጣን ወይም ጋኔን አለ ወይ? ያዘው ስንልስ ምን ማለታችን ነው? በምንስ እናውቃለን? መንፈሳዊ ባልሆኑ ምክንያቶች የሰው አእምሮ ሊታመም አይችልም ወይ? ለምሳሌ፣ የተለያዩ ዕፆችና በአእምሮ ላይ ተጽዕኖ ሊያደርጉ በሚችሉ ንጥረ ነገሮች ቁጥጥር ውስጥ ያለ አእምሮ ልክ ጋኔን እንዳደረበት ሰው ያለ ባሕርይ ሊያሳይ ይችላል። በግዜርም ሆነ በመንፈሳዊ ዓለም መኖር በማያምነው ጐራ እንደሆኑ ራሳቸውን የሚፈርጁ ሰዎች፣ መንፈሳዊ እውነታን እንደምታምኚ ሲያውቁ እንደ ሞኝ ነው የሚሥቁብሽ ወይም እንደ ምስኪን ነው የሚያዩሽ። በእነርሱ እይታ ሁሉም ነገር ከአንጐልና ከሰው አእምሮ መዛባት አንጻር ብቻ ነው የሚታየው።

"በሌላ በኩል ደግሞ ማንኛውም የባሕሪይና የሥነልቦና ቀውስ የሚታይበትን ሰው ሁሉ በርኩስ መንፈስ እንደ ተያዘና በሰይጣን እንደ ተለከፈ የሚያምኑ ብዙ ሰዎች አሉ። በተለይ እዚህ እኛ አገርና ባጠቃላይ አፍሪካው-ያን ወደዚህኛው ምድብ ሳናደላ አንቀርም። ለእኔ ግን ሰው ማለት በመንፈሳዊው አለምና እውነታ ውስጥ የሚኖር አካላዊና አእምሯዊ ማንነት ያለው ፍጥረት ነው። ስለዚህም የመንፈሳዊ ቀውስም ሆነ የአካላዊና አእምሯዊ ችግሮች በጥንቃቄ ካላዩዋቸው ሊያምታቱ የሚችሉ ተመሳሳይ ባህርያት አላቸው።

"መፈሳዊው አለም ስለካድነው የለም ማለት አይደለም። ሳይንስ ደግሞ መንፈሳዊውን እውነታ እንደቁሳዊው ነገር መለካትና ማረጋገጥ የሚችል መሣሪያም አቅምም አለው ብዬ አላምንም። ደግሞ ሁሉንም ነገር በማመናፈስና ያልገባንን ነገር

Brought to You by t.me/bookshelf99

ሁሉ በሠይጣን በማላከክ ችግሩን መፍታት ሳይሆን፣ ትርፉ ይባስ ማወሳሰብ ሊሆን ይችላል። ሚዛናዊነት አስፈላጊ ነው" አለና፣ እሷ ምላሽ በመጠበቅ የመንገዱን ግራና ቀኝ እያየ ዝም አለ።

በዚህና በመሰል ጉዳዮች ላይ ስትጠይቀውና ሲያወሩ ሳይሰለቻቸው ነበር ቡታጅራ መታጠፊያ ላይ ደረሱ። "ቡታጅራ አካባቢ ደረስን ማለት ነው። ማኪያቶ ነገር ... እንዴት ነው?" አላት፣ ለማኪያቶ ያላትን ፍቅር ስለሚያውቅ።

"ያ ... ጊዜ ካለን ነዳ ነዳ እያደረግንም ከተማው ብናየው ደስ ይለኛል። ማኪያቶም ሁሌም ጥሩ ሐሳብ ነው።" ተቀምጠው ማኪያቶ ካዘዙ በኋላ፣ "ሌላዬ ... ልጆቹ አታቲን አስቸግረዋት እንዳይሆን፣ እስኪ ቤት ደውል" ብላ፣ ተንጠራራች። ልጆቹንና እናቱን አዋርተው መንገዳቸውን ለመቀጠል ተነሱ። አስፋልቱን ተከትለው ከተማይቱን አየት አየት አደረጉና ከተማይቱ መግቢያ ከመንገድ ዳር ካለ ትልቅ ሆቴል ገቡና ማኪያቶ አዘው ቁጭ አሉ።

Brought to You by t.me/bookshelf99